## P

**pace** (v.) ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አለ
He paced the room nervously. ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ በመጨነቅ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አለ

**pace off** በእርምጃ ፡ ለካ
He paced off on the ground the area he wanted plowed. እንዲታረስ ፡ የሚፈልገውን ፡ መሬት ፡ በእርምጃ ፡ ለካ

**pace** (n.) እርምጃ
Walk ten paces to the north! ዐሥር ፡ እርምጃ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ተራመድ
*He hikes at a pace of three miles an hour. በሰዓት ፡ ሦስት ፡ ማይል ፡ ይሄዳል

**keep pace with someone** ከሱ ፡ ጋር ፡ እኩል ፡ ተራመደ
I can't keep pace with him; he walks too fast. ከሱ ፡ ጋር ፡ እኩል ፡ ልራመድ ፡ አልችልም ። በጣም ፡ በፍጥነት ፡ ይራመዳል

**set a fast pace**
*He sets a fast pace for walking. ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ ስለሚራመድ ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ መሄድ ፡ አዳጋች ፡ ነው

**set the pace** ምሳሌ ፡ ነው
He sets the pace for everybody else in our class. በክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ላሉት ፡ ተማሪዎች ፡ ሁሉ ፡ ምሳሌ ፡ ነው
[See also 'easy, slack, smart']

**pacific**
1. ሰላምን ፡ የሚወድ. Those pacific people are not inclined to make war. እነዚያ ፡ ሰላምን ፡ የሚወዱ ፡ ሰዎች ፡ ጦርነት ፡ ለማድረግ ፡ አይሹም
2. የሰላም. The last century was a pacific era in history. ያለፈው ፡ ዘመን ፡ በታሪክ ፡ ውስጥ ፡ የሰላም ፡ ዘመን ፡ ነበር

**make pacific advances** በሰላም ፡ ቀረበ
The traders made pacific advances toward the Indians. ነጋዴዎቹ ፡ ህንዶችን ፡ በሰላም ፡ ቀረቧቸው

**pacification** (= verbal noun) ማረጋጋት
The pacification of the occupied city did not succeed. የተያዘውን ፡ ከተማ ፡ ለማረጋጋት ፡ የተደረገው ፡ ሙከራ ፡ አልተሳካም

**pacify** (pacified)
1. አባበለ. I tried to pacify her with promises but failed. ቃል ፡ በመግባት ፡ ላባብላት ፡ሞክሬ ፡ ነበር ፡ ግን ፡ አልተሳካልኝም
2. አረጋጋ. The troops are trying to pacify the city. ወታደሮቹ ፡ ከተማውን ፡ ለማረጋጋት ፡ በመሞከር ፡ ላይ ፡ ናቸው

**pack** (vt.)
1. እቃ ፡ ከተተ. Have you packed your trunk yet? እቃህን ፡ በሻንጣህ ፡ ውስጥ ፡ ከተሃል ?
2. ከተተ. I packed two shirts and some socks in my valise. ሁለት ፡ ሸሚዞችና ፡ ጥቂት ፡ የእግር ፡ ሹራቦች ፡ ሻንጣዬ ፡ ውስጥ ፡ ከተትኩ
3. አደራጅቶ ፡ አስቀመጠ. Pack your books in this box! መጻሕፍትህን ፡ እዚህ ፡ ሣጥን ፡ ውስጥ ፡ አደራጅተህ ፡ አስቀምጥ
4. ሞላ. He packed his suitcase with clothes. ሻንጣውን ፡ ልብስ ፡ ሞላው
5. አሰረ. He packed his bags in feverish haste. ሻንጣውን ፡ አቻኩሎ ፡ አሰረ
6. ጫነ. We packed the mules and then set off for the lake. በቅሎዎቹን ፡ ጭነን ፡ ወደ ፡ ሐይቁ ፡ ለመሄድ ፡ ተነሣን
7. ግጥም ፡ አለ(በት). +People packed the theatre. ቲያትር ፡ ቤቱ ፡ ሰው ፡ ግጥም ፡ ብሎበታል
8. አጨቀ(ታጨቀ). They shouldn't pack us into the train this way. ባቡር ፡ ውስጥ ፡ እንደዚህ ፡ ሊያጭቁን ፡ አይገባም
The farmer shook down the sack of grain until it was firmly packed. እህሉ ፡ በደንብ ፡ እስኪታጨቅ ፡ ገበሬው ፡ ጆንያውን ፡ ጠቀጠቀው

**pack** (vi.) እቃውን ፡ አዘጋጀ
We packed last night and are ready to go. እቃችንን ፡ ባለፈው ፡ ሌሊት ፡ ስላዘጋጀን ፡ ለመሄድ ፡ ተዘጋጅተናል

**pack away** አስቀመጠ
Pack these clothes away in a large trunk! እነዚህን ፡ ልብሶች ፡ በትልቅ ፡ ሣጥን ፡ ውስጥ ፡ አስቀምጥ

**pack off** መልሶ ፡ ላከ
We packed her off to her mother because she could not follow the rules. ትእዛዝ ፡ ለመጠበቅ ፡ ስላልቻለች ፡ ወደ ፡ እናቷ ፡ መልሰን ፡ ላክናት

**pack up** (vt.) ጠቀለለ
He packed up his things and left. ጓዙን ፡ ጠቅልሎ ፡ ሄደ

**pack up** (vi.) እቃ ፡ ጠቀለለ
It's time to pack up and leave this place. እቃችንን ፡ ጠቅልለን ፡ ከዚህ ፡ ቦታ ፡ መሄድ ፡ አለብን

## pack (n.)
1. ጭነት. The donkeys were loaded down with heavy packs. አህዮቹ ፡ ከባድ ፡ ጭነት ፡ ተጭነው ፡ ነበር
2. ፓኬት. Give me a pack of cigarettes! አንድ ፡ ፓኬት ፡ ሲጃራ ፡ ስጠኝ

**pack of thieves** የሌባ ፡ ዋሻ
This company is nothing but a pack of thieves. ይህ ፡ ኩባንያ ፡ የሌባ ፡ ዋሻ ፡ ነው

**in packs** በብዛት
Hyenas hunt in packs; lions hunt alone. ጅቦች ፡ የሚያድኑት ፡ በብዛት ፡ ሲሆን ፡ አንበሳ ፡ ግን ፡ ብቻውን ፡ ነው

## package
1. ጥቅል. The mailman brought a package for you. ፖስተኛው ፡ አንድ ፡ ጥቅል ፡ አመጣልህ
2. መጠቅለያ. Use thick cardboard for the package! ለመጠቅለያው ፡ በወፍራም ፡ ካርቶን ፡ ተጠቀም

## pack animal የጭነት ፡ ከብት
Renting pack animals will cost a lot of money. የጭነት ፡ ከብት ፡ መከራየት ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ይጠይቃል

## packhorse አጋሰስ
I have hired three packhorses to carry my stuff. እቃዬን ፡ የምጭንባቸው ፡ ሦስት ፡ አጋሰሶች ፡ ተከራይቻለሁ

## pact ውል
They made a pact to permit free trade. ከቀረጥ ፡ ነጻ ፡ የሆነ ፡ ንግድ ፡ ለመፍቀድ ፡ ውል ፡ አደረጉ

## pad (padded)
1. አስደረተ. I padded my coat so it would be warmer. ይበልጥ ፡ እንዲሞቀኝ ፡ ኮቴን ፡ አስደረትኩት
2. ሞላ. He padded his story with unnecessary details. በማያስፈልጉ ፡ ዝርዝሮች ፡ ታሪኩን ፡ ሞላው

## pad (n.)
1. ፍራሽ. The baby's carriage has a pad made to fit it. የሕፃኑ ፡ አልጋ ፡ በልኩ ፡ የተሠራ ፡ ፍራሽ ፡ አለው
2. ድብዳብ ፡ መሳይ. He put a pad on the horse's back to keep it from being chafed. የፈረሱ ፡ ጀርባ ፡ እንዳይላጥ ፡ ድብዳብ ፡ መሳይ ፡ ጣለበት

**pad of paper**
I need a pad of paper. ጥቂት ፡ የማስታወሻ ፡ ደብተር ፡ ያስፈልገኛል

## paddle (v.) ቀዘፈ
He paddled the canoe across the lake. ታንኳውን ፡ እየቀዘፈ ፡ ሐይቁን ፡ አቋረጠ

## paddle (n.) መቅዘፊያ
He lost one of the two paddles. ከሁለቱ ፡ መቅዘፊያ ፡ አንዱ ፡ ጠፋበት

## pagan (n.) አረማዊ
Pagans are still found in certain parts of the world. አሁንም ፡ ባንዳንድ ፡ የዓለም ፡ ክፍሎች ፡ አረማውያን ፡ ይገኛሉ

**pagan** (adj.) የአረማውያን
There are still pagan ceremonies in some regions. ባንዳንድ ፡ ቦታዎች ፡ ዛሬም ፡ የአረማውያን ፡ ሥርዓቶች ፡ ይገኛሉ

## paganism ጣዖት ፡ ማምለክ
The tribe relapsed into paganism. ነገዱ ፡ ጣዖት ፡ ወደ ፡ ማምለክ ፡ ተመለሰ

## page (v.) አስጠራ
I asked him to page my brother in the hotel lobby. በሆቴል ፡ ሳሎን ፡ ውስጥ ፡ ወንድሜን ፡ እንዲያስጠራው ፡ ጠየቅሁት

## page (n.)
1. ገጽ. The book is two hundred pages long. መጽሐፉ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ገጽ ፡ አለው
2. ምዕራፍ. The settling of the West is an exciting page in our history. የሕዝብ ፡ በምዕራብ ፡ መስፈር ፡ በታሪካችን ፡ ውስጥ ፡ ትልቅ ፡ ምዕራፍ ፡ ነው
3. ተላላኪ. I sent the page for the newspaper. ጋዜጣ ፡ እንዲያመጣልኝ ፡ ተላላኪውን ፡ ላክሁት

## pageant ሥነ ፡ ሥርዓት
The coronation of the king was a splendid pageant. የንጉሡ ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ አከባበር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በጣም ፡ የደመቀ ፡ ነበር

## pagination የገጽ ፡ ቁጥር
The pagination of this book is not in order. የዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ የገጽ ፡ ቁጥር ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ ትክክል ፡ አይደለም

## pail ባልዲ
Fill the pail with water! ባልዲውን ፡ ውኃ ፡ ሙላው
[See also 'garbage']

**pain** (v.) አመመ(ው)
Does your tooth pain you? ጥርስህን ፡ ያምሃል ?

**pain** (n.)
1. ውጋት. I feel a sharp pain in my back. ጀርባዬን ፡ ኀይለኛ ፡ ውጋት ፡ ይሰማኛል
2. ሥቃይ. A toothache is a pain. የጥርስ ፡ ሕመም ፡ ሥቃይ ፡ ነው

**pains** ድካም
Great pains have been taken to finish the project. እቅዱን ፡ ለመጨረስ ፡ ታላቅ ፡ ድካም ፡ አድርጓል

**feel a dull pain in** ተወጋጋ(ው)
+I feel a dull pain in my side. ጐኔን ፡ ይወጋጋኛል

**feel (a) pain in**
1. አመመ(ው). +Do you feel pain in the tooth? ጥርስህን ፡ ያምሃል ?
2. ውጋት ፡ ተሰማ(ው). +All of a sudden, I felt a sharp pain in my back. በድንገት ፡ ጀርባዬ ፡ ላይ ፡ ኀይለኛ ፡ ውጋት ፡ ተሰማኝ

**have a pain in** አመመ(ው)
+I have a pain in my knee. ጉልበቴን ፡ ያመኛል

**take pains**
1. ብዙ ፡ ደከመ. He took pains to have the place neat and clean. ቦታውን ፡ ለማጽዳት ፡ ብዙ ፡ ደከመ
2. ተጨነቀ. He takes great pains to please his employer. ቀጣሪውን ፡ ለማስደሰት ፡ ብዙ ፡ ይጨነቃል
[See also 'free, inflict, stab, throb']

**(be) painful**
1. አመመ. Was the operation very painful? ቀዶ ፡ ጥገናው ፡ በጣም ፡ ያም ፡ ነበር ?
2. አስቀጠጠ. It is painful to see him suffer. ሲሠቃይ ፡ ማየቱ ፡ ያስቀጥጣል
3. ሥቃይ ፡ ነው. Childbirth is painful for women. ልጅ ፡ መውለድ ፡ ለሴቶች ፡ ሥቃይ ፡ ነው

**painless** ያለምንም ፡ ሥቃይ
This treatment is a painless cure for cancer. ይህ ፡ ሕክምና ፡ ከካንሰር ፡ በሽታ ፡ ያለምንም ፡ ሥቃይ ፡ የሚፈውስ ፡ ነው

**painstaking** ታላቅ
He repaired the damaged car with painstaking care. የተበላሸውን ፡ መኪና ፡ በታላቅ ፡ ጥንቃቄ ፡ ጠገነው

**paint** (vt.)
1. ቀባ. He painted the house light blue. ቤቱን ፡ ውኃ ፡ ሰማያዊ ፡ ቀለም ፡ ቀባ
2. ሣለ. Who painted this portrait? ይህን ፡ የሰው ፡ ሥዕል ፡ ማን ፡ ሣለው ?
3. ገለጸ. He painted an exciting story of his travels. የጉዞውን ፡ ታሪክ ፡ በሚያስደንቅ ፡ አኳኋን ፡ ገለጸው

**paint** (vi.) ሣለ
She paints in oils. በዘይት ፡ ቀለም ፡ ትሥላለች

**paint** (n.) ቀለም
The paint is still wet. ቀለሙ ፡ አሁንም ፡ እርጥብ ፡ ነው

**paintbrush** የቀለም ፡ ብሩሽ
The paintbrush is dry. የቀለሙ ፡ ብሩሽ ፡ ደርቋል

**painter**
1. ሠዓሊ. A famous painter is going to visit our country. ዝነኛ ፡ ሠዓሊ ፡ አገራችንን ፡ ሊጐበኝ ፡ ነው
2. ቀለም ፡ ቀቢ. The painter distributed the paint evenly over the wall. ቀለም ፡ ቀቢው ፡ ግድግዳውን ፡ አስተካክሎ ፡ ቀባው

**painting** ሥዕል
That's a beautiful painting. ያ ፡ ውብ ፡ ሥዕል ፡ ነው

**pair** (v.), ~ **off** ሁለት ፡ ሁለት ፡ ሆነው ፡ ሄዱ
The boys and girls paired off. ወንዶቹና ፡ ልጃገረዶቹ ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ ሆነው ፡ ሄዱ

**be paired** በጥንድ ፡ በጥንድ ፡ ተደረደረ
Her gloves were neatly paired in a drawer. የእጅ ፡ ሹራቦቿ ፡ መሳቢያው ፡ ውስጥ ፡ በጥንቃቄ ፡ በጥንድ ፡ በጥንድ ፡ ተደርድረዋል

**pair** (n.)
1. ጥምድ ፤ ጥንድ. Many articles like shoes are sold in pairs. እንደጫማ ፡ ያሉ ፡ ብዙ ፡ ነገሮች ፡ የሚሸጡት ፡ በጥንድ ፡ ነው
A pair of oxen pulls the plow. አንድ ፡ ጥንድ ፡ በሬ ፡ ሞፈር ፡ ይጐትታል
2. ሁለት. The pair danced alone on the dance floor. ሁለቱ ፡ በዳንሱ ፡ ወለል ፡ ላይ ፡ ብቻቸውን ፡ ደነሱ

**pairs** ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ጥንድ ፡ ጥንድ ፡ እየሆኑ
Many happy pairs were waltzing on the dance floor. በዳንስ ፡ ወለል ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ የተደሰቱ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ጥንድ ፡ ጥንድ ፡ እየሆኑ ፡ ይደንሱ ፡ ነበር
[See also 'glove, trousers']

**pajamas** ፒጃማ
Pajamas are worn during bedtime hours. ፒጃማ ፡ የሚለበሰው ፡ በመኝታ ፡ ጊዜ ፡ ነው

**palace** ቤተ ፡ መንግሥት
The palace was built last year. ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ የተሠራው ፡ ዓምና ፡ ነው
[See also 'jubilee']

**(be) palatable** ጣዕም ፡ አለው
This food is not palatable. ይህ ፡ ምግብ ፡ ጣዕም ፡ የለውም

**palate** ላንቃ
I have a sore on my palate. ላንቃዬ ፡ ቆስሏል

**palatial** ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የመሰለ
His palatial house was destroyed by the rebels. ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የመሰለ ፡ ቤቱን ፡ ዐመፀኞቹ ፡ አፈረሱበት

**pale** (v.) አመድ ፡ መሰለ
His face paled at the bad news. መጥፎ ፡ ወሬ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ፊቱ ፡ አመድ ፡ መሰለ

**pale** (n.) ዕንጨት
Some pales of the fence are broken. ያጥሩ ፡ አንዳንድ ፡ ዕንጨቶች ፡ ተሰብረዋል

**outside the pale**
*Murderers are outside the pale of civilized society. ነፍስ ፡ ገዳይ ፡ እንደሠለጠነ ፡ ሰው ፡ አይቈጠርም

**pale** (adj.)
1. የገረጣ. Sick people often have pale faces. የታመሙ ፡ ሰዎች ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የገረጣ ፡ መልክ ፡ አላቸው
2. ደብዘዝ ፡ ያለ. The bright stars are surrounded by pale ones. በብሩሆች ፡ ኮከቦች ፡ ዙሪያ ፡ ደብዘዝ ፡ ያሉ ፡ ኮከቦች ፡ አሉ

**be pale** ገረጣ
When you have been ill, your face is sometimes pale. ሰው ፡ ሲታመም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ፊቱ ፡ ይገረጣል

**turn pale** ፊቱ ፡ አመዱ ፡ ቡን ፡ አለ
When he heard that, he turned pale. ይህን ፡ ሲሰማ ፡ ፊቱ ፡ አመዱ ፡ ቡን ፡ አለ

**palisade** አጥር
The bull broke through the palisades of the cattle pen. ወይፈኑ ፡ ከጋጣ ፡ ውስጥ ፡ አጥሩን ፡ ሰብሮ ፡ ወጣ

**palliate**
1. አስታገሠ. The medicine palliates a fever. መድኃኒቱ ፡ ትኩሳትን ፡ ያስታግሣል
2. አድበሰበሰ. He attempted to palliate the crime by paying back the stolen money. የሰረቀውን ፡ ገንዘብ ፡ በመመለስ ፡ ወንጀሉን ፡ ሊያድበሰብስ ፡ ሞከረ

**pallid** የገረጣ
His pallid face shows the severity of the fever. የገረጣው ፡ ፊቱ ፡ የትኩሳትን ፡ ኀይለኛነት ፡ ያመለክታል

**pallor** መገርጣት
The pallor showed that he was ill. መገርጣቱ ፡ ታሞ ፡ እንደነበረ ፡ ያሳያል

**palm**
1. ዘምባባ. These palms are thirty feet high. እነዚህ ፡ ዘምባባዎች ፡ ሠላሳ ፡ ጫማ ፡ ይረዝማሉ
2. መዳፍ. His palm is callused from digging a lot. ብዙ ፡ በመቈፈሩ ፡ የተነሣ ፡ መዳፉ ፡ ሻክሯል

**Palm Sunday** የሆሣዕና ፡ ዕለት
Our Lord Jesus Christ went to Jerusalem on Palm Sunday. የሆሣዕና ፡ ዕለት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ገባ

**palpable**
1. ሊዳሰስ ፡ የሚችል. There was a palpable bump on his head. በራሱ ፡ ላይ ፡ ሊዳሰስ ፡ የሚችል ፡ እብጠት ፡ ነበር
2. ጉልህ. His writing his name on the check was a palpable error. በቼኩ ፡ ላይ ፡ ስሙን ፡ መጻፉ ፡ ጉልህ ፡ ስሕተት ፡ ነበር

**palpate** ደባበሰ
The doctor palpated my abdomen to see if I had an appendicitis. ሐኪሙ ፡ የትርፍ ፡ አንጀት ፡ በሽታ ፡ እንዳለብኝ ፡ ለማወቅ ፡ ሆዴን ፡ ደባበሰ

**palpitate**
1. ከበሮ ፡ መታ. The boy's heart palpitated with fear. ከፍርሀት ፡ የተነሣ ፡ የልጁ ፡ ልብ ፡ ከበሮ ፡ መታ
2. ተንዘፈዘፈ. His body palpitated with terror. በፍርሀት ፡ ሰውነቱ ፡ ተንዘፈዘፈ

**pamper** አሞላቀቀ
She pampered her child by giving him everything he wanted. ለልጇ ፡ የፈለገውን ፡ እየሰጠች ፡ አሞላቀቀችው

**pamphlet** አነስተኛ ፡ መጽሔት
He published a pamphlet on public health. ስለ ፡ ጤና ፡ ጥበቃ ፡ አነስተኛ ፡ መጽሔት ፡ አወጣ

**pan** መጥበሻ
Give me a pan to cook this meat in! ይህን ፡ ሥጋ ፡ የምጠብስበት ፡ መጥበሻ ፡ ስጠኝ

**pancake** [ከቂጣ ፡ ሳሳ ፡ ያለ ፡ ከእንጀራ ፡ ወፈር ፡ ያለ ፡ ከስንዴ ፡ ዱቄት ፡ የሚሠራ ፡ ዳቤ ፡ የመሰለ ፡ ኬክ]

**pane** መስታወት
The boy threw a stone at the windowpane. ልጁ ፡ መስኮቱ ፡ መስታወት ፡ ላይ ፡ ድንጋይ ፡ ወረወረ

**panel**
1. ክፍል. A panel was knocked out of the door. ከመዝጊያው ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ ወልቋል
2. ጓድ. He is a member of a special panel for studying crime. ወንጀል ፡ የሚያጠና ፡ ያንድ ፡ ልዩ ፡ ጓድ ፡ አባል ፡ ነው

**(be) paneled** ተለበደ
The room is paneled in cedar. ግድግዳው ፡ በጥድ ፡ ተለብዷል

**pang**
*Pangs of hunger did not let him study. ረኃብ ፡ እየሞረሞረ ፡ አላስጠና ፡ አለው
[See also 'sorrow']

**panic** (panicked), vt.
1. አስፈራራ ፤ አስደነገጠ. He tried to panic the child by making fierce noises. የሚያስፈራ ፡ ድምፅ ፡ በማሰማት ፡ ሕፃኑን ፡ ሊያስፈራራ ፡ (ሊያስደነግጥ) ፡ ሞከረ
2. አሸበረ. The fearful storm panicked the children. አስፈሪው ፡ ዝናብ ፡ ልጆቹን ፡ አሸበራቸው

**panic** (vi.) ተሸበረ
The soldiers panicked because of the bombing. ከቦምቡ ፡ ድብደባ ፡ የተነሣ ፡ ወታደሮቹ ፡ ተሸበሩ

**panic** (n.) ሽብር
There was a panic when fire started in the movie. በሲኒማ ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ እሳት ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ሽብር ፡ ሆነ
*Panic seized the crowd. ሕዝቡ ፡ ተደናገጠ

**panicked, see panic**

**(be) panic-stricken** በፍርሃት ፡ ተርበደበደ ፤ ተሸበረ
The children were panic-stricken when the fire broke out. ቃጠሎ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ልጆቹ ፡ በፍርሃት ፡ ተርበደበዱ ፡ (ተሸበሩ)

**panorama**
*The panorama of the city can be seen from the top of the mountain. ከተራራው ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ከተማው ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ ይታያል

**pant**
1. ቁና ፡ ቁና ፡ ተነፈሰ. The load was heavy, and he came panting up the stairs. ሸክሙ ፡ ስለከበደው ፡ ቁና ፡ ቁና ፡ እየተነፈሰ ፡ ደረጃውን ፡ ወጣ
2. ትንፋሹ ፡ ቁርጥ ፡ ቁርጥ ፡ አለ. "Come quick, come quick!" panted John. ጆን ፡ ትንፋሹ ፡ ቁርጥ ፡ ቁርጥ ፡ እያለ ፡ « ቶሎ ፡ ና ፤ ቶሎ ፡ ና » ፡ አለ
3. በጣም ፡ ተጣጣረ. The director panted after fame and fortune. ሥራ ፡ መሪው ፡ ለዝናና ፡ ለሀብት ፡ በጣም ፡ ተጣጣረ

**panther** አነር
Are there panthers in Ethiopia? በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ አነሮች ፡ አሉ ?

**pantomime** እንቅስቃሴ ፡ ብቻ
He acted out the play in pantomime. በንቅስቃሴ ፡ ብቻ ፡ ቲያትሩን ፡ ሠራ

**pantry** (pantries) ጓዳ
The dishes are kept in a pantry. ሳሕኖቹ ፡ ጓዳ ፡ ናቸው

**pants** ሱሪ
His pants are dark. ሱሪው ፡ ጥቁር ፡ ነው

**pair of pants** ሱሪ
I bought a suit with two pairs of pants. አንድ ፡ ሙሉ ፡ ልብስ ፡ ከሁለት ፡ ሱሪ ፡ ጋር ፡ ገዛሁ

**papa!** አባባ
She saw her father and cried out, "Papa!". አባቷን ፡ አይታ ፡ « አባባ » ፡ ብላ ፡ ተጣራች

**papaya** ፓፓያ
Papaya is a fruit that is grown in the Awash Valley. ፓፓያ ፡ በአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ የሚበቅል ፡ ፍሬ ፡ ነው

**paper** (v.) የግድግዳ ፡ ወረቀት ፡ ለጠፈ(በት)
He has not papered the room for five years. አምስት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ቤቱን ፡ የግድግዳ ፡ ወረቀት ፡ አልለጠፈበትም

**paper** (n .)
1. ወረቀት. The paper in this notebook is dirty. የዚህ ፡ ደብተር ፡ ወረቀት ፡ ቆሻሻ ፡ ነው
2. ጋዜጣ. I read the story in today's paper. ወሬውን ፡ ያነበብኩት ፡ ከዛሬው ፡ ጋዜጣ ፡ ላይ ፡ ነው
3. ሰነድ. Some important papers are missing. አንዳንድ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑ ፡ ሰነዶች ፡ ጠፍተዋል
4. ጽሑፍ. He read a paper on the Amharic verb at the meeting. በስብሰባው ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ አማርኛ ፡ ግስ ፡ የተጻፈ ፡ አንድ ፡ ጽሑፍ ፡ አነበበ

Let's have this contract on paper! ይህንን ፡ ውል ፡ በጽሑፍ ፡ እናድርገው
5. ድርሰት. My history paper is due tomorrow. ለታሪክ ፡ ትምህርት ፡ የጻፍኩትን ፡ ድርሰት ፡ የማስረከቢያው ፡ ቀን ፡ ነገ ፡ ነው

**sheet of paper** ወረቀት I ቅጠል ፡ ወረቀት
The envelope contained only a blank sheet of paper. ኤንቬሎፑ ፡ ባዶ ፡ ወረቀት ፡ ብቻ ፡ ይዟል
Give me two sheets of paper. ሁለት ፡ ቅጠል ፡ ወረቀት ፡ ስጠኝ

**paperback** የወረቀት ፡ ጥራዝ
This book has come out in paperback. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ በወረቀት ፡ ጥራዝ ፡ ታትሞ ፡ ወጣ

**paper boy** ጋዜጣ ፡ ሻጭ
The paper boy wants his money. ጋዜጣ ፡ ሻጩ ፡ ገንዘቡን ፡ ይፈልጋል

**paperwork** የጽሑፍ ፡ ሥራ
My job requires a lot of paperwork. ሥራዬ ፡ ብዙ ፡ የጽሑፍ ፡ ሥራ ፡ ይጠይቃል

**par, be on a ~** እኩል ፡ ነው
He is on a par with his brother in intelligence. በብልህነት ፡ ከወንድሙ ፡ ጋር ፡ እኩል ፡ ነው

**up to par** እንደወትሮ
With his injured knee, Abraham's running is not up to par. ጉልበቱን ፡ ስለታመመ ፡ የአብርሃም ፡ ሩጫ ፡ እንደወትሮው ፡ አይደለም

**parable** ምሳሌ
Jesus spoke in parables. ኢየሱስ ፡ በምሳሌ ፡ ይናገር ፡ ነበር

**parachute** ጃንጥላ
The paratroopers dropped from the plane in parachutes. ያየር ፡ ወለድ ፡ ወታደሮች ፡ ከአውሮፕላኑ ፡ ላይ ፡ በጃንጥላ ፡ ወረዱ

**parade** (v.) በሰልፍ ፡ ተዘዋወረ
The army paraded through the town. ሰራዊቱ ፡ በከተማው ፡ ውስጥ ፡ በሰልፍ ፡ ተዘዋወረ

**parade** (n.)
1. ሰልፍ. He marched at the head of the parade. ሰልፉን ፡ መራ
2. ሰልፈኞች. When he looked out of the window, he saw a parade passing by. በመስኮት ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ሲመለከት ፡ ሰልፈኞቹ ፡ ሲያልፉ ፡ አየ

**make a parade of** እዩልኝ ፡ አለ
A modest man does not make a parade of his wealth. ትሑት ፡ ሰው ፡ ሀብቱን ፡ እዩልኝ ፡ አይልም

**paradigm** እርባታ
These students can recite Amharic nouns and verb paradigms. እነዚህ ፡ ተማሪዎች ፡ ያማርኛን ፡ ስምና ፡ ግስ ፡ እርባታ ፡ ሊሰጡ ፡ ይችላሉ

**paradise** ገነት
His garden is a veritable paradise. ያትክልቱ ፡ ቦታ ፡ በእውነት ፡ ገነት ፡ ነው

**paradox** ተፃራሪ ፡ አባባል
'Make haste slowly' is a paradox. በዝግታ ፡ ተፍጠን ፡ ማለት ፡ ተፃራሪ ፡ አባባል ፡ ይመስላል

**paragraph** አንቀጽ
This is the beginning of a new paragraph. ይህ ፡ ያዲስ ፡ አንቀጽ ፡ መጀመሪያ ፡ ነው
The student condensed the long speech to a paragraph. ተማሪው ፡ ረጅሙን ፡ ንግግር ፡ ባንድ ፡ አንቀጽ ፡ አሳጠረው

**parakeet** በቅበቃ
Parakeets mimic human voices. በቅበቃ ፡ የሰውን ፡ ድምፅ ፡ ይቀዳል

**parallel** (v.)
1. ተከትሎ ፡ ሄደ. The roads parallel the river. መንገዶቹ ፡ ወንዙን ፡ ተከትለው ፡ ይሄዳሉ
2. ተመሳሰለ. Your experience parallels mine. ያጋጠመህ ፡ ነገር ፡ እኔን ፡ ካጋጠመኝ ፡ ይመሳሰላል

**parallel** (n.)
1. አጓዳኝ ፡ መሥመር. Draw a parallel to this line! ለዚህ ፡ መሥመር ፡ አጓዳኝ ፡ መሥመር ፡ አሥምር
2. ተመሳሳይ. This story is without a known parallel. ታሪኩ ፡ ተመሳሳይ ፡ የሌለው ፡ ነው

**be a parallel** ተመሳሰለ
Her experience was an interesting parallel to ours. ያጋጠማት ፡ ነገር ፡ እኛን ፡ ካጋጠመን ፡ ጋር ፡ በጣም ፡ የሚመሳሰል ፡ ነበር

**draw a parallel** አነጻጸረ
He drew a parallel between this rainy season and last rainy season. የዘንድሮውንና ፡ ያምናውን ፡ ክረምት ፡ አነጻጸረ

**parallel** (adj.)
1. አጓዳኝ. Rails of a railway track are parallel. የባቡሩ ፡ ሐዲድ ፡ መሥመሮች ፡ አጓዳኝ ፡ ናቸው
2. የሚመሳሰል. The scholar found parallel customs in different countries. ምሁሩ ፡ በተለያዩ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ የሚመሳሰሉ ፡ ልማዶች ፡ እንዳሉ ፡ ተመለከተ

**be parallel** ተመሳሰለ
Your training is parallel to mine. የኔና ፡ ያንተ ፡ ትምህርት ፡ ይመሳሰላል

**parallelism** ተመሳሳይነት
There is little parallelism between human and animal language. በሰውና ፡ በእንስሳት ፡ ቋንቋ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ተመሳሳይነት ፡ እምብዛም ፡ ነው

**paralysis** መስለል ፤ የሰውነት ፡ መስለል
Paralysis of the arm resulted in the atrophy of the muscles. የክንዱ ፡ መስለል ፡ የጡንቻዎችን ፡ መመንመን ፡ አስከተለ
His paralysis forces him to rest several hours a day. የሰውነቱ ፡ መስለል ፡ በቀን ፡ ለብዙ ፡ ሰዓት ፡ እንዲያርፍ ፡ ያደርገዋል

**cause a paralysis of** (= intr.) ቆመ
*The war caused a paralysis of trade. ከጦርነቱ ፡ የተነሣ ፡ ንግድ ፡ ቆሟል

**paralyze**
1. ሽባ ፡ አደረገ. Polio may paralyze people. ፖሊዮ ፡ ሰዎችን ፡ ሽባ ፡ ሊያደርግ ፡ ይችላል
2. ዘጋ. The flood paralyzed transportation. ጐርፉ ፡ መመላለሻውን ፡ ዘጋው

**be paralyzed**
1. ሽባ ፡ ሆነ. She has been paralyzed ever since she has had that disease. ያ ፡ ሕመም ፡ ካደረባት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ሽባ ፡ ሆናለች
His hand was paralyzed, and he could not move it. እጁ ፡ ሽባ ፡ ስለሆነ ፡ ሊያንቀሳቅሰው ፡ አልቻለም
2. ተዘጋ. The traffic was completely paralyzed. በመኪና ፡ ብዛት ፡ ትራፊክ ፡ በፍጹም ፡ ተዘግቶ ፡ ነበር
3. በድን ፡ ሆነ. I was paralyzed with fear. በፍርሀት ፡ በድን ፡ ሆንኩ

**leave paralyzed** አሰለለ
The stroke left the governor paralyzed on one side of his body. የደም ፡ መርጋት ፡ በሽታ ፡ የእንደራሴውን ፡ ግማሽ ፡ ጐን ፡ አሰለለው

**paramount** ዋና
Her family was her paramount concern. ዋና ፡ ሐሳቧ ፡ ለቤተሰቦቿ ፡ ነበር

**be of paramount importance** ከሁሉም ፡ ነገር ፡ ቀዳሚነት ፡ አለው
The country's welfare is of paramount importance. የሀገሪቱ ፡ ደኅንነት ፡ ከሁሉም ፡ ነገር ፡ ቀዳሚነት ፡ ያለው ፡ ነው

**paraphrase** [ያንድ ፡ ምንባብን ፡ ይዘታ ፡ በራስ ፡ አገላለጽ ፡ አስረዳ]

**parasite**
1. ጥገኛ ፡ ነፍሳት. Ticks are parasites that carry various diseases. መዥገር ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ በሽታዎችን ፡ የሚያመጣ ፡ ጥገኛ ፡ ነፍሳት ፡ ነው
2. በሰው ፡ ትከሻ ፡ የሚኖር. He is a parasite; he gets everything he needs from his relatives and friends. በሰው ፡ ትከሻ ፡ የሚኖር ፡ ስለሆነ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ሁሉ ፡ ከዘመዶቹና ፡ ከወዳጆቹ ፡ ያገኛል

**parasol** ጃንጥላ
Men and women carry parasols. ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ጃንጥላ ፡ ይይዛሉ

**paratrooper** ያየር ፡ ወለድ ፡ ወታደር
The paratrooper receives special training. ያየር ፡ ወለድ ፡ ወታደሩ ፡ ልዩ ፡ ትምህርት ፡ ይሰጠዋል

**parcel** (v.), ~ **out** ሸንሽኖ ፡ አከፋፈለ
The government parceled out land to settlers. መንግሥቱ ፡ አዲስ ፡ ለሰፈሩት ፡ ሰዎች ፡ መሬት ፡ ሸንሽኖ ፡ አከፋፈለ

**parcel** (n.)
1. የተጠቀለለ ፡ እቃ. You forgot your parcels. የተጠቀለሉትን ፡ እቃዎችህን ፡ ረስተሃል
2. ጥቅል. This parcel was not properly tied for mailing. ይህ ፡ ጥቅል ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ለመላክ ፡ በሚገባ ፡ አልታሰረም ፡ ነበር
3. ቁራጭ. I bought a parcel of land in the mountains. በተራራዎቹ ፡ ውስጥ ፡ አንዲት ፡ ቁራጭ ፡ መሬት ፡ ገዛሁ
[See also 'part']

**parcel post** በፖስታ ፡ የሚላክ
Parcel post rates are very low in this country. እዚህ ፡ አገር ፡ እቃ ፡ በፖስታ ፡ የሚላክበት ፡ ዋጋ ፡ ርካሽ ፡ ነው

**by parcel post** በፖስታ ፡ ቤት ፡ በኩል
We sent the coat by parcel post. ኮቱን ፡ በፖስታ ፡ ቤት ፡ በኩል ፡ ላክን

**parch** (vt.)
1. ቆላ. We parch wheat and eat it. ስንዴ ፡ ቆልተን ፡ እንበላለን
2. አደረቀ. The hot sun parched the soil. የገረረው ፡ ፀሐይ ፡ መሬቱን ፡ አደረቀው

**parch** (vi.) ደረቀ
The land parched under the hot sun. መሬቱ ፡ በፀሐይ ፡ሙቀት ፡ ምክንያት ፡ ደረቀ

**parched** (adj.) ደርቆ ፡ የተሰነጣጠቀ
Nothing could grow in the parched ground. ደርቆ ፡ በተሰነጣጠቀው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ አይበቅልም

**parched corn** የተቆላ ፡ በቆሎ
Have you any parched corn left? የተቆላ ፡ በቆሎ ፡ ተርፎሃል ?

**parched grain** ቆሎ
He is munching on parched grain. ቆሎ ፡ ይቈረጥማል

**parchment** ብራና
Old books are written on parchment. የጥንት ፡ መጽሐፎች ፡ የተጻፉት ፡ በብራና ፡ ነው

**pardon** (v.)
1. ምሕረት ፡ አደረገ(ለት) ፤ ማረ. The President pardoned him at the last moment. ፕሬዚዳንቱ ፡ በመጨረሻው ፡ ላይ ፡ ምሕረት ፡ አደረገለት
Most governors have the prerogative of pardoning prisoners. ብዙ ፡ ገዢዎች ፡ እስረኞችን ፡ የመማር ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው
2. ይቅር ፡ አለ. Please pardon my mistake! ስሕተቴን ፡ ይቅር ፡ በለኝ

**pardon** (n.) ምሕረት
He was refused a pardon. ምሕረት ፡ ተከለከለ
*I beg your pardon. Where is Churchill Avenue? እባክዎ ፤ የቸርቺል ፡ ጐዳና ፡ ወዴት ፡ ነው ?

**ask (someone's) pardon** ይቅርታ ፡ ጠየቀ
The shamefaced boy asked the teacher's pardon for having insulted him. ዓይን ፡ አፋሩ ፡ ልጅ ፡ አስተማሪውን ፡ በመዝለፉ ፡ ይቅርታ ፡ ጠየቀ

**pare**
1. ላጠ. The mother pared the apple for the child. እናትዮዋ ፡ ቱፋውን ፡ ለልጁ ፡ ላጠችለት
2. ቀነሰ. We must pare our expenses until we pay off our debt. ዕዳችንን ፡ እስክንከፍል ፡ ድረስ ፡ ወጪያችንን ፡ መቀነስ ፡ አለብን

**parent**
1. ወላጅ. A parent should teach his children. ወላጅ ፡ ልጁን ፡ ማስተማር ፡ አለበት
2. ምንጭ. Latin is the parent of various languages. ላቲን ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋዎች ፡ ምንጭ ፡ ነው

**parents**
1. ወላጆች. We must honor our parents. ወላጆቻችንን ፡ ማክበር ፡ አለብን
2. ቤቶች. She can always move back with her parents. ከፈለገች ፡ ቤቶቿ ፡ ዘንድ ፡ ለመመለስ ፡ ትችላለች

**parentage** ቤተሰብ
Even though he is of humble parentage, he reached a high position. ከድኻ ፡ ቤተሰብ ፡ የመጣ ፡ ቢሆንም ፡ ከታላቅ ፡ ማዕረግ ፡ ላይ ፡ ደርሷል

**parental** የወላጅ
The boy listens to parental advice. ልጁ ፡ የወላጅን ፡ ምክር ፡ ይቀበላል

**parenthesis** ቅንፍ
He wrote the translation in parenthesis. ትርጉሙን ፡ በቅንፍ ፡ ውስጥ ፡ ጻፈው

**parenthood**
1. ወላጅ ፡ መሆን. Parenthood requires patience and understanding. ወላጅ ፡ መሆን ፡ ታጋሽነትንና ፡ አድማጭነትን ፡ ይጠይቃል
2. ወላጅ. Poor parenthood results in unruly children. መጥፎ ፡ ወላጅ ፡ የማይታዘዙ ፡ ልጆች ፡ ያወጣል

**parings** ልጣጭ
He threw away the parings of the apple. የቱፋውን ፡ ልጣጭ ፡ ጣለው

**parish**
1. ደብር. This parish is very small in comparison with others. ይህ ፡ ደብር ፡ ከሌሎች ፡ ጋር ፡ ሲመዛዘን ፡ አነስተኛ ፡ ነው
2. የደብር ፡ ሕዝብ. The parish voted to repair the church. የደብሩ ፡ ሕዝብ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ መታደስ ፡ ደገፈ

**parishoners** የደብር ፡ ሕዝብ
The parishoners celebrate the festival of St. Mary every month. የደብሩ ፡ ሕዝብ ፡ የቅድስት ፡ ማርያምን ፡ በዓል ፡ በየወሩ ፡ ያከብራሉ

**parity** በሰው ፡ ልጅ ፡ መካከል ፡ እኩልነት
Parity is difficult to achieve. በሰው ፡ ልጅ ፡ መካከል ፡ እኩልነት ፡ ማግኘት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**reach parity** በዋጋ ፡ ተመጣጠነ
The two currencies have now reached parity. የሁለቱ ፡ አገሮች ፡ ገንዘብ ፡ አሁን ፡ በዋጋ ፡ ተመጣጥኗል

**park** (vt.) አቆመ
Where can I park my car? መኪናዬን ፡ የት ፡ ላቆም ፡ እችላለሁ ?

**park** (vi.) አቆመ
He parked in a busy street. ትራፊክ ፡ አበዛበት ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ አቆመ

**park** (n.) መናፈሻ ፡ ቦታ
There is a beautiful park in the center of the city. በከተማው ፡ መሀከል ፡ አንድ ፡ ጥሩ ፡ መናፈሻ ፡ ቦታ ፡ አለ

**parking place** መኪና ፡ ማቆሚያ ፡ ስፍራ
This is a public parking place. ይህ ፡ ለሕዝቡ ፡ የተሠራ ፡ መኪና ፡ ማቆሚያ ፡ ስፍራ ፡ ነው

**parkway** አውራ ፡ ጐዳና
A parkway is safe and enjoyable to drive along.

አውራ ፡ ጐዳና ፡ ሰላምና ፡ ለመንዳትም ፡ የሚያስደስት ፡ ነው

**parley** ስብሰባ
The opposing generals met in a parley to discuss the exchange of prisoners. እስረኞችን ፡ ስለ ፡ መለዋወጥ ፡ ጉዳይ ፡ ለመነጋገር ፡ የሁለቱም ፡ ጦር ፡ ጄኔራሎች ፡ ስብሰባ ፡ አደረጉ

**parliament** ምክር ፡ ቤት ፤ ፓርላማ
The Ethiopian parliament has two houses. የኢትዮጵያ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ (ፓርላማ) ፡ ሁለት ፡ ክፍሎች ፡ አሉት

**parliamentarian** የሕጉን ፡ ሥርዓት ፡ ዐዋቂ
The parliamentarian interprets the rules of order. የሕጉን ፡ ሥርዓት ፡ ዐዋቂው ፡ ደንቡን ፡ ያስረዳል

**parliamentary** የፓርላሜንት
The meeting was conducted strictly by parliamentary procedure. ስብሰባው ፡ የፓርላሜንትን ፡ ሥርዓት ፡ ተከትሎ ፡ ተካሄደ

**parlor** ማረፊያ ፡ ክፍል
The servant let me in to the parlor. አሽከሩ ፡ ወደ ፡ ማረፊያው ፡ ክፍል ፡ አስገባኝ
[See also 'beauty parlor']

**parochial**
1. የቤተ ፡ ክህነት. Both parochial and public education receive government support. የቤተ ፡ ክህነትና ፡ የመንግሥት ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ከመንግሥት ፡ እርዳታ ፡ ያገኛሉ
2. በጣም ፡ የተወሰነ. He has lived in one place so long that his ideas are parochial. ባንድ ፡ ቦታ ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ ስለኖረ ፡ አስተሳሰቡ ፡ በጣም ፡ የተወሰነ ፡ ነው

**parody** [ቁም ፡ ነገር ፡ ጽሑፍ ፡ አሥቂኝ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ጽፎ ፡ ማቅረብ]

**parole**
*The convict is now free on parole. እስረኛው ፡ በየጊዜው ፡ ባለሥልጣን ፡ ፊት ፡ መቅረብ ፡ ቢኖርበትም ፡ በነጻ ፡ ተለቋል

**parrot** (v.) አስተጋባ
He parrots his employer's words. የቀጣሪውን ፡ ቃል ፡ ያስተጋባል

**parrot** (n.) በቀቀን
The parrot repeats what anybody says. በቀቀን ፡ ሰው ፡ የሚናገረውን ፡ መልሳ ፡ ትናገራለች

**parry** (parried)
1. መከተ. He parried the sword with his staff. ጐራዴውን ፡ በዘንግ ፡ መከተ
2. ለመመለስ ፡ ሞከረ. She parried our question by asking us one. ጥያቄያችንን ፡ በጥያቄ ፡ ለመመለስ ፡ ሞከረች

**parse** ተነተነ
The advanced students parse the most complex sentences. የገፉት ፡ ተማሪዎች ፡ በጣም ፡ የተወሳሰቡ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገሮችን ፡ ይተነትናሉ

**parsimonious** ቆጥቋጣ
He is so parsimonious, he won't spend money on good food. በጣም ፡ ቆጥቋጣ ፡ ስለሆነ ፡ ለጥሩ ፡ ምግብ ፡ ገንዘብ ፡ አያወጣም

**parsimony** ሥሥታምነት
His parsimony is well known to everybody. ሥሥታምነቱ ፡ በሁሉም ፡ ዘንድ ፡ ታውቋል

**parson** የደብር ፡ አለቃ
The parson was educated in Gondar. የደብሩ ፡ አለቃ ፡ ጐንደር ፡ ነው ፡ የተማሩት

**part** (vt.)
1. መንገድ ፡ አስለቀቀ. The police parted the crowd to let the dignitaries pass. ታላላቆቹ ፡ ሰዎች ፡ እንዲያልፉ ፡ ፖሊሶች ፡ ሕዝቡን ፡ መንገድ ፡ አስለቀቁት
2. አለያየ. A misunderstanding parted them. አለመግባባት ፡ አለያያቸው
3. ከፈለ. On which side do you part your hair? ጸጉርህን ፡ የምትከፍለው ፡ በየት ፡ በኩል ፡ ነው ?
4. ገለጠ. She parted the curtains to look out. ወደ ፡ ውጭ ፡ ለማየት ፡ መጋረጃዎቹን ፡ ገለጠች

**part** (vi.)
1. መንገድ ፡ ለቀቀ(ለት). The crowd parted to let us through. እንድናልፍ ፡ ሕዝቡ ፡ መንገድ ፡ ለቀቀልን
2. ተለያየ. She parted from her friends in tears. ከጓደኞቿ ፡ በእንባ ፡ ተለያየች
We parted at the corner. መታጠፊያው ፡ ላይ ፡ ተለያየን
3. ተበጠሰ. The rope parted in the middle. ገመዱ ፡ መሀሉ ፡ ላይ ፡ ተበጠሰ
4. ገለጠ. The clouds parted, revealing the sun. ደመናው ፡ ስለገለጠ ፡ ፀሐይዋ ፡ ታየች

**part with**
1. አወጣ. He hates to part with his money. ገንዘብ ፡ ማውጣት ፡ አይወድም
2. ከእጅ ፡ አወጣ. I wouldn't part with that book for any price. ያንን ፡ መጽሐፍ ፡ በምንም ፡ ዓይነት ፡ ከእጄ ፡ አላወጣውም
[See also 'company']

**part** (n.)

1. ክፍል. That part of the work isn't finished yet. ከሥራው ፡ ያኛው ፡ ክፍል ፡ ገና ፡ አላለቀም
The western part of Ethiopia is very hot. የኢትዮጵያ ፡ ምዕራባዊ ፡ ክፍል ፡ በጣም ፡ ሞቃት ፡ ነው
2. ድርሻ. Everyone must do his part. ሁሉም ፡ ሰው ፡ ድርሻውን ፡ መሥራት ፡ አለበት
3. ግማሽ. The fence is part wood and part stone. አጥሩ ፡ ግማሹ ፡ ዕንጨት ፡ ግማሹ ፡ ግምብ ፡ ነው
4. ቦታ. I have a good part in the play. ቲያትሩ ፡ ውስጥ ፡ ጥሩ ፡ ቦታ ፡ ተሰጥቶኛል
5. ኀላፊነት. He plays a minor part in the government. በመንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ኀላፊነት ፡ ዝቅተኛ ፡ ነው
6. ፈንታ. The detective's part was to find the criminal. የወንጀል ፡ መርማሪ ፡ ፈንታ ፡ ወንጀለኛውን ፡ ማግኘት ፡ ነበር
7. አባል. He felt himself to be a part of the gang. የጓዱ ፡ አባል ፡ እንደሆነ ፡ ተሰማው
*He's part Indian. የህንድ ፡ ክልስ ፡ ነው

**parts**

1. አገር. Are you from these parts? የዚህ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ነህ ?
2. ግድም. I haven't traveled much in these parts. በዚህ ፡ ግድም ፡ ብዙ ፡ አልተዘዋወርኩም

**part and parcel** መሠረታዊ ፡ ክፍል

The guarantee was part and parcel of the bargain. ዋስትናው ፡ የግዢው ፡ መሠረታዊ ፡ ክፍል ፡ ነበር
*Her love for her child was part and parcel of her life. ሕይወቷ ፡ የተመሠረተው ፡ በልጇ ፡ ፍቅር ፡ ላይ ፡ ነው

**for my part** በኔ ፡ በኩል ፤ በበኩሌ

For my part, I can let you have the book. በኔ ፡ በኩል ፡ መጽሐፉን ፡ ላውስህ ፡ እችላለሁ
For my part, I feel that it is advisable to do so. በበኩሌ ፡ ይህን ፡ ማድረግ ፡ የሚያዋጣ ፡ ይመስለኛል

**for the most part**

1. አብዛኞቹ. His company is made up for the most part of volunteers. የሱ ፡ ሰዎች ፡ አብዛኞቹ ፡ ወዶ ፡ ዘማቾች ፡ ናቸው
2. አብዛኛውን ፡ ጊዜ. For the most part, the weather has been nice this summer. በዚህ ፡ በጋ ፡ አየሩ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ጥሩ ፡ ነው
3. በብዙ ፡ በኩል. For the most part, I agree with him. በብዙ ፡ በኩል ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ እስማማለሁ

**foreign parts** ውጭ ፡ አገር

He has traveled much in foreign parts. ውጭ ፡ አገር ፡ ብዙ ፡ ዞሯል

**have part in** ነበረ(በት)

He had no part in the robbery. በዝርፊያው ፡ ውስጥ ፡ አልነበረበትም

**in good part**

1. በወዳጅነት ፡ መልክ. He took the joke in good part. ቀልዱን ፡ በወዳጅነት ፡ መልክ ፡ ተቀበለው
2. አብዛኛው. His success is in good part ascribable to dogged determination. ካሰበው ፡ መድረሱ ፡ አብዛኛው ፡ ከጠንካራ ፡ መንፈሱ ፡ የተነሣ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል

**in part** በከፊል

I agree with you in part. በከፊል ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ እስማማለሁ

**on my part** በበኩሌ

On my part, I cannot understand his English. በበኩሌ ፡ የሱ ፡ እንግሊዝኛ ፡ አይገባኝም

**play a part** ቦታ ፡ ያዘ

Private enterprise plays a small part in Ethiopia's development. በኢትዮጵያ ፡ ልማት ፡ ውስጥ ፡ የግል ፡ ንግድ ፡ የያዘው ፡ ቦታ ፡ አነስተኛ ፡ ነው

**take part**

1. ተካፈለ. He took part in the African campaign. በአፍሪካ ፡ ዘመቻ ፡ ተካፍሏል
2. ተካፋይ ፡ ሆነ. Are you going to take part in the discussion? በውይይቱ ፡ ተካፋይ ፡ ትሆናለህ ?

**take someone's part** ደገፈ

He always takes his brother's part. ሁልጊዜ ፡ ወንድሙን ፡ ይደግፋል
[See also 'early, spare']

**partake**

1. ከሱ ፡ ጋር ፡ ተሳተፈ. Will you partake of this humble meal? ይችን ፡ ተራ ፡ ምግብ ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ልትሳተፍ ፡ ትፈቅዳለህ ?
2. ተካፈለ. He is still convalescent and cannot partake in sports. አሁንም ፡ ገመምተኛ ፡ ስለሆነ ፡ በእስፖርት ፡ ሊካፈል ፡ አይችልም

**partial** ከፊል

That is only partial payment of what you owe. ላለብህ ፡ ዕዳ ፡ ይህ ፡ ከፊል ፡ ክፍያ ፡ ነው

**be partial to**

1. አደላ. He has always been partial to his youngest daughter. ለትንሿ ፡ ልጁ ፡ ዘወትር ፡ ያደላል
2. ወደደ. He is partial to French cooking. የፈረንሳይን ፡ ምግብ ፡ ይወዳል

**partiality** ዝንባሌ

His son shows a strong partiality for history

books. ልጁ ፡ ለታሪክ ፡ መጻሕፍት ፡ የተለየ ፡ ዝንባሌ ፡ አለው

**partially** በከፊል
You are partially right. በከፊል ፡ ልክ ፡ ነህ

**participant** ተካፋይ
I was a participant in the Olympic Games once. በኦሊምፒክ ፡ ውድድር ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ተካፋይ ፡ ነበርኩ

**participate** ተካፋይ ፡ ሆነ
How many will participate in the meeting? በስብሰባው ፡ ላይ ፡ ስንት ፡ ሰዎች ፡ ተካፋይ ፡ ይሆናሉ ?

**participation** ተካፋይ ፡ መሆን
Participation of student groups in running the university is a new idea. በዩኒቨርሲቲው ፡ አስተዳደር ፡ ውስጥ ፡ ተማሪዎችም ፡ ተካፋይ ፡ መሆናቸው ፡ አዲስ ፡ የመጣ ፡ ሐሳብ ፡ ነው

**participle** ቦዝ ፡ አንቀጽ
The Amharic participle has a special form. በአማርኛ ፡ ቦዝ ፡ አንቀጽ ፡ የተለየ ፡ መልክ ፡ አለው

**particle** ቅንጣት
There is not a particle of truth in that story. በዚያ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ የእውነት ፡ ቅንጣት ፡ የለበትም
*I got a particle of dust in my eye. ዓይኔ ፡ ውስጥ ፡ አቧራ ፡ ገባ

**particular** (n.) ረገድ
The work is complete in every particular. ሥራው ፡ በማንኛውም ፡ ረገድ ፡ ተጠናቋል

**particulars** ዝርዝር
For further particulars, write to the publishers. ተጨማሪውን ፡ ዝርዝር ፡ አታሚውን ፡ በጽሑፍ ፡ ጠይቅ

**particular** (adj.)
1. የተለየ. Is he a particular friend of yours? የተለየ ፡ ጓደኛህ ፡ ነው ?
I went on a walk for no particular reason. ምንም ፡ የተለየ ፡ ዓላማ ፡ ሳይኖረኝ ፡ ልንሸራሸር ፡ ወጣሁ
2. ልዩ. His particular task is to care for the dog. ልዩ ፡ ሥራው ፡ ውሻውን ፡ ማንከባከብ ፡ ነው
3. ራሱ. The table I want is this particular one. የምፈልገው ፡ ጠረጴዛ ፡ ይህ ፡ ራሱ ፡ ነው
4. (= adv.) በተለይ. Pay particular attention to what the teacher says. አስተማሪው ፡ የሚለውን ፡ በተለይ ፡ ልብ ፡ ብለህ ፡ አድምጥ

**be particular** ተጠነቀቀ
My husband is very particular about his food. ባለቤቴ ፡ ስለ ፡ ምግቡ ፡ እጅግ ፡ ይጠነቀቃል

**in particular** በተለይ
I remember one of them in particular. አንደኛውን ፡ በተለይ ፡ አስታውሰዋለሁ

**this particular** ይህኛው
This particular dress costs more. ይህኛው ፡ ልብስ ፡ ይበልጥ ፡ ያወጣል

**particularity** (particularities) የተለየ ፡ ጠባይ
A particularity of his is great attention to detail. ዝርዝር ፡ ጉዳዮችን ፡ አጥብቆ ፡ መመርመር ፡ የተለየ ፡ ጠባዩ ፡ ነው

**particularly**
1. በተለይ. He is particularly interested in science. በተለይ ፡ የሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ዝንባሌ ፡ አለው
2. በጥንቃቄ. The inspector examined the machine particularly. ተቆጣጣሪው ፡ መኪናውን ፡ በጥንቃቄ ፡ መረመረ

**parting** (n.) መለያየት
The parting of friends is sad. የወዳጆች ፡ መለያየት ፡ አሳዛኝ ፡ ነው

**parting** (adj.)
*The thieves fired a parting shot at us. ሌቦቹ ፡ ሲሸሹ ፡ ተኰሱብን

**partisan**
1. የደፈጣ ፡ ተዋጊ. The partisans attacked the village. የደፈጣ ፡ ተዋጊዎች ፡ መንደሩን ፡ አጠቁ
2. ደጋፊ. Party partisans voted against the passage of the bill. የፓርቲው ፡ ደጋፊዎች ፡ የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ እንዳያልፍ ፡ ድምፃቸውን ፡ ሰጡ

**partition** (v.) ከፋፈለ
They partitioned the room and made several small rooms out of it. ክፍሉን ፡ ከፋፍለው ፡ ብዙ ፡ ትናንሽ ፡ ክፍሎች ፡ ሠሩ

**partition** (n.)
1. መከፋፈል. The partition of India resulted in two new countries. የህንድ ፡ መከፋፈል ፡ ለሁለት ፡ አዲስ ፡ አገሮች ፡ መፈጠር ፡ ምክንያት ፡ ሆነ
2. የቤት ፡ አካፋይ. I made a hole in the partition. በቤቱ ፡ አካፋይ ፡ ውስጥ ፡ ቀዳዳ ፡ አበጀሁ
3. የሚከፋፍል ፡ አነስተኛ ፡ ግድግዳ. The desks in the office were separated by partitions. ቢሮው ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ጠረጴዛዎች ፡ በሚከፋፍል ፡ አነስተኛ ፡ ግድግዳ ፡ ተለያይተዋል

**partly** ግማሹ
The house is only partly rented. ቤቱ ፡ ግማ ሹ ፡ ብቻ ፡ ተከራይቷል

**partner**
1. ሽርካ ፤ ሸሪክ. My partner is coming back tomorrow. ሽርካዬ ፡ (ሸሪኬ) ፡ ነገ ፡ ይመለሳል
2. ባለጥቅም ፤ ማኅበርተኛ. The division of profits among the partners was equitable. የባለጥቅ ሞቹ ፡ የትርፍ ፡ አከፋፈል ፡ ተገቢ ፡ ነበር
He apportioned the profits among the partners. ትርፉን ፡ ለማኅበርተኞቹ ፡ አከፋፈለ
*I was his tennis partner once a week. በሳምን ት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ባንድ ፡ ቡድን ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ ቴ ኒስ ፡ እንጫወት ፡ ነበር

**partner in crime** ግብረ ፡ አበር
His partner in crime was later arrested by the police. ግብረ ፡ አበሩ ፡ ቆይቶ ፡ በፖሊስ ፡ ተያዘ
[See also 'silent']

**partnership** ሽርክና
The partnership was broken up by the death of the younger one. በታናሽዬው ፡ ሞት ፡ ምክን ያት ፡ ሽርክናው ፡ ፈረሰ

**partook,** see **partake**

**partridge** ቆቅ
Some of my friends hunt partridge. አንዳንድ ፡ ጓደኞቼ ፡ ቆቅ ፡ ያድናሉ

**part-time** የትርፍ ፡ ሰዓት
I am looking for a part-time job. የትርፍ ፡ ሰ ዓት ፡ ሥራ ፡ በመፈለግ ፡ ላይ ፡ ነኝ

**party** (parties)
1. ግብዣ. She likes to give big parties. ትልቅ ፡ ግብዣ ፡ ማድረግ ፡ ትወዳለች
2. የፖለቲካ ፡ ቡድን. What party do you belong to? የየትኛው ፡ የፖለቲካ ፡ ቡድን ፡ አባል ፡ ነህ ?
3. ሰው. The party you were calling is on the telephone now. በስልክ ፡ የምትፈልገው ፡ ሰው ፡ ቀርቧል
4. ነገረተኛ. Neither of the two parties appeared at the trial. ከነገረተኞቹ ፡ አንዱም ፡ ፍ ርድ ፡ ቤት ፡ አልቀረበም
5. ጓድ. A search party set out to find the missing boy. የጠፋውን ፡ ልጅ ፡ ለመፈለግ ፡ የ ፈላጊዎች ፡ ጓድ ፡ ተሰማራ
6. ወገን. He served as a go-between, but was unable to reconcile the two parties. እንደ ፡ አ ስታራቂ ፡ ሆኖ ፡ ቢያገላግልም ፡ ሁለቱን ፡ ወገኖ ች ፡ ለማስታረቅ ፡ አልቻለም

**be a party to** ተካፋይ ፡ ሆነ
I don't want to be a party to any conspiracy. በማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ አድማ ፡ ተካፋይ ፡ ለመሆን ፡ አልፈልግም

**throw a party** ፓርቲ ፡ አደረገ
He threw a party to welcome the returning students. ከውጭ ፡ አገር ፡ የተመለሱትን ፡ ተማሪ ዎች ፡ ለመቀበል ፡ ፓርቲ ፡ አደረገ

**paschal** የፋሲካ
The paschal lamb is expensive. የፋሲካ ፡ በግ ፡ ውድ ፡ ነው

**pass** (vt.)
1. አለፈ. I pass this bank building every day. ሁል ፡ ቀን ፡ በዚህ ፡ ባንክ ፡ በኩል ፡ አልፋለሁ
Did you pass your examination? ፈተናህን ፡ አ ለፍክ ?
2. አሳለፈ. He passed most of the time reading. ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ በማንበብ ፡ አሳለፈ
After much deliberation, they passed the bill. ብዙ ፡ ከተነጋገሩበት ፡ በኋላ ፡ የሕጉን ፡ ረቂቅ ፡ አሳለፉ
The teacher passed the whole class this term. በዚህ ፡ ተርም ፡ አስተማሪው ፡ ተማሪዎቹን ፡ ሁ ሉ ፡ አሳለፈ
3. ቀደመ. An express bus passed the local bus. በራሪ ፡ አውቶቡስ ፡ የከተማውን ፡ አውቶቡስ ፡ ቀ ደመው
4. አቀበለ. Will you please pass the bread? እስቲ ፡ ዳቦውን ፡ አቀብለኝ
Will you pass me the sugar, please! ስኳሩን ፡ ታቀብለኝ
5. አስገባ. The sentry passed the returning soldiers. ዘቡ ፡ ተመላሾቹን ፡ ወታደሮች ፡ አስገ ባቸው
6. ለሰው ፡ ሰጠ. He was in prison for passing bad checks. የሐሰት ፡ ቼክ ፡ ለሰው ፡ በመስጠቱ ፡ እስር ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ ነበር
7. ሰጠ. I can't pass an opinion on your work before seeing it. ሥራህን ፡ ሳላይ ፡ ስለ ፡ ሥራህ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ አስተያየት ፡ ልሰጥ ፡ አልችልም
The judge will pass sentence today. ዳኛው ፡ ዛ ሬ ፡ ፍርድ ፡ ይሰጣል
8. ጣሰ. You passed the red light. ቀይ ፡ መብራ ት ፡ ጣስክ

**pass** (vi.)
1. አለፈ. The days pass quickly when you are busy. ሥራ ፡ ሲይዙ ፡ ቀኑ ፡ ቶሎ ፡ ያልፋል
2. ተላለፈ. The land passes from father to son. ርስቱ ፡ ከአባት ፡ ወደ ፡ ልጅ ፡ ይተላለፋል
3. ሆነ. Tell me everything that passed be-

tween you. በሁለታችሁ ፡ መካከል ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ንገረኝ

4. ተለወጠ. Water passes to a solid state when it freezes. ውኃ ፡ ሲረጋ ፡ ወደ ፡ በረዶነት ፡ ይለወጣል

5. ጸደቀ ፤ አለፈ. The new tax bill quickly passed. አዲሱ ፡ የግብር ፡ ሕግ ፡ በቶሎ ፡ ጸደቀ ፡ (አለፈ)

**pass across each other** ተሳለፈ

The two lines pass across each other. ሁለቱ ፡ መሥመሮች ፡ ይተሳለፋሉ

**pass around**

1. አስተላለፈ. Pass the bottle around! ጠርሙሱን ፡ አስተላልፍ

2. አሰረ. He passed a rope around the barrel. በርሜሉ ፡ ዙሪያ ፡ ገመድ ፡ አሰረ

**pass away**

1. አረፈ. Her mother passed away last week. እናቷ ፡ ባለፈው ፡ ሳምንት ፡ አረፉ

2. አለፈ. All this trouble will pass away. ይህ ፡ ሁሉ ፡ ችግር ፡ ያልፋል

**pass for**

1. ተቈጠረ ፤ ታየ. He passes for a learned man in this small village. በዚህ ፡ ትንሽ ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ እንደተማረ ፡ ሰው ፡ ይቈጠራል ፡ (ይታያል)

2. መስሎ ፡ አሳሳተ. They look so much alike that they could pass for brothers. በመልክ ፡ አንድ ፡ ስለሆኑ ፡ ወንድማማቾች ፡ መስለው ፡ ያሳስታሉ

**pass in review** (tr.) ሰልፍ ፡ ጐበኘ

The general passed the troops in review. ጄኔራሉ ፡ የወታደሩን ፡ ሰልፍ ፡ ጐበኘ

**pass in review** (intr.) በሰልፍ ፡ አለፈ

The troops passed in review before the Emperor. ወታደሮቹ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ፊት ፡ በሰልፍ ፡ አለፉ

**pass off** (vi.)

1. ተከናወነ. The strike meeting passed off quietly. ሥራ ፡ ለማቆም ፡ የተደረገው ፡ ስብሰባ ፡ በጸጥታ ፡ ተከናወነ

2. (= tr.) ተወ. The headache passed off in the late afternoon. ራስ ፡ ምታቴ ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ቆየት ፡ ብሎ ፡ ተወኝ

**pass oneself off as**

He passed himself off as a doctor. በሐሰት ፡ ሐኪም ፡ ነኝ ፡ አለ

**pass out** (vt.) ዐደለ

They passed out pamphlets at the meeting. በስብሰባው ፡ ላይ ፡ አነስተኛ ፡ መጽሔት ፡ ዐደሉ

**pass out** (vi.) ነፍሱን ፡ ሳተ

Several people passed out from the heat. ከሙቀቱ ፡ የተነሣ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ነፍሳቸውን ፡ ሳቱ

**pass over**

1. ዳሰሰ. Pass your hand over the silk and feel how soft it is! ሐሩን ፡ ዳስህ ፡ እንዴት ፡ እንደሚለሰልስ ፡ ተመልከት

2. ችላ ፡ አለ ፤ አለፈ. Just pass over the first part of the letter! የደብዳቤውን ፡ የመጀመሪያ ፡ ክፍል ፡ ችላ ፡ በለው ፡ (እለፈው)

**pass up** ሳይቀበለው ፡ ቀረ

He passed up the chance to go to America. አሜሪካ ፡ ለመሄድ ፡ የነበረውን ፡ ዕድል ፡ ሳይቀበለው ፡ ቀረ

**come to pass** ተደረገ

Strange things came to pass. እንግዳ ፡ ነገሮች ፡ ተደረጉ

**it will pass** ምንም ፡ አይል

This copy isn't very good, but it will pass. ይህ ፡ ግልባጭ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ አይደለም ፤ ሆኖም ፡ ምንም ፡ አይል

**let pass**

1. አሳለፈ. The guard didn't let me pass. ዘበኛው ፡ አላሳልፍ ፡ አለኝ

2. እንዲያልፍ ፡ ፈቀደ. The censor let the letter pass. ሳንሱሩ ፡ ደብዳቤው ፡ እንዲያልፍ ፡ ፈቀደ

3. ችላ ፡ አለ. He decided to let the insult pass. ስድቡን ፡ ችላ ፡ ለማለት ፡ ወሰነ

4. አመለጠ(ው). +Don't let the opportunity to go to Ethiopia pass. ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለመሄድ ፡ ያጋጠመህ ፡ ዕድል ፡ እንዳያመልጥህ

[See also 'obscurity']

## pass (n.)

1. የፈቃድ ፡ ወረቀት ፤ ፈቃድ. You will need a pass to get by the gate. በሩን ፡ ለማለፍ ፡ የፈቃድ ፡ ወረቀት ፡ (ፈቃድ) ፡ ያስፈልግሃል

2. ጊዜያዊ ፡ የይለፍ ፡ ወረቀት. Stateless persons may be granted passes, but not passports. ዜግነት ፡ የሌላቸው ፡ ጊዜያዊ ፡ የይለፍ ፡ ወረቀት ፡ እንጂ ፡ ፓስፖርት ፡ አይሰጣቸውም

3. በተራራዎች ፡ መሀል ፡ ያለ ፡ መተላለፊያ. The pass was held by the government troops. በተራራዎች ፡ መሀል ፡ ያለው ፡ መተላለፊያ ፡ በመንግሥት ፡ ወታደሮች ፡ ተይዞ ፡ ነበር

## passable መጠነኛ

He has a passable knowledge of Amharic. መጠነኛ ፡ ያማርኛ ፡ ችሎታ ፡ አለው

**be passable** ያስኬዳል

This road is passable only in the dry season. ይህ ፡ መንገድ ፡ የሚያስኬደው ፡ በበጋ ፡ ብቻ ፡ ነው

## passage

1. መተላለፊያ. We had to go through a dark

passage. ጭልም ፡ ባለ ፡ መተላለፊያ ፡ ማለፍ ፡ ነበረብን
2. የማለፍ ፡ ፈቃድ. He was given passage through the enemy lines. በጠላት ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ የማለፍ ፡ ፈቃድ ፡ ተሰጠው
3. ጉዞ. We had a calm passage across the Atlantic. አትላንቲክን ፡ ስናቋርጥ ፡ ደኅና ፡ ጉዞ ፡ አጋጠመን
4. ምንባብ. He read us an interesting passage from his book. ከመጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ የሚያስደስት ፡ ምንባብ ፡ አነበበልን
5. ክፍል. The expurgated edition of Shakespeare has no offensive passages in it. የታረመው ፡ የሼክስፒር ፡ ቲያትር ፡ በውስጡ ፡ የሚያስከፋ ፡ ክፍል ፡ የለበትም
6. ማለፍ. The passage of the bill was very well received. የረቂቁን ፡ ማለፍ ፡ በደስታ ፡ ተቀበሉት

**book passage** ቦታ ፡ ያዘ
He booked passage to New York. ወደ ፡ ኒው ፡ ዮርክ ፡ ለመሄድ ፡ ቦታ ፡ ያዘ

**force passage** ተጋፍቶ ፡ አለፈ
He had to force passage through the crowd. በሕዝቡ ፡ መሀከል ፡ ተጋፍቶ ፡ ማለፍ ፡ ነበረበት

**with the passage of time** በቀን ፡ ብዛት
With the passage of time, old hatreds are forgotten. በቀን ፡ ብዛት ፡ የቆየ ፡ ቂም ፡ ይረሳል

**passenger** መንገደኛ ፤ ተሳፋሪ
The bus holds only thirty passengers. አውቶቡሱ ፡ ሠላሳ ፡ መንገደኞች ፡ ብቻ ፡ ይይዛል
Boats ply among the islands of Lake Tana carrying food and passengers. ጀልባዎች ፡ ምግብና ፡ ተሳፋሪዎች ፡ ይዘው ፡ በጣና ፡ ደሴቶች ፡ መካከል ፡ ይመላለሳሉ

**passer-by** መንገደኛ ፤ አላፊ ፡ አግዳሚ
A passer-by must have picked it up. መንገደኛ ፡ (አላፊ ፡ አግዳሚ) ፡ አንሥቶት ፡ ይሆናል

**passing** (n.) ሞት
The whole nation mourned his passing. በሱ ፡ ሞት ፡ አገሩ ፡ በሙሉ ፡ አዘነ

**passing** (adj.)
1. ተላላፊ. The passing crowd paid no attention to the sick child. ተላላፊው ፡ ሕዝብ ፡ በሽተኛውን ፡ ልጅ ፡ ዞር ፡ ብሎም ፡ አላየው
2. ዘላቂነት ፡ የሌለው. This is only a passing fashion. ይህ ፡ ሞድ ፡ ዘላቂነት ፡ የሌለው ፡ ነው

**give a passing glance** መልከት ፡ አደረገ
I gave the girl a passing glance. ልጅቷን ፡ መልከት ፡ አደረግኋት

**give a passing mark** አሳለፈ
The teacher gave the student a passing mark. አስተማሪው ፡ ተማሪውን ፡ አሳለፈው

**in passing** በነገሬ ፡ ላይ
In passing, I'd like to say that ... በነገሬ ፡ ላይ ፡ ለማለት ፡ የምፈልገው

**passion**
1. ስሜት. He is guided by passion rather than by reason. በምርምር ፡ ሳይሆን ፡ በስሜት ፡ ይመራል
2. ፍቅር. The sight of her filled him with passion. ሲያያት ፡ በፍቅር ፡ ተነሸጠ
*Music is her passion. ሙዚቃ ፡ በጣም ፡ ትወዳለች

**fly into a passion** በንዴት ፡ ጦፈ
He flew into a passion when he heard his speech. ንግግሩን ፡ ሲሰማ ፡ በንዴት ፡ ጦፈ

**have a passion for** በጣም ፡ ወደደ
She has a passion for American food. የአሜሪካን ፡ ምግብ ፡ በጣም ፡ ትወዳለች

**passionate**
1. የጋለ ፡ ስሜት ፡ ያለው. Passionate believers in religion are willing to fight to the death. ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ለሃይማኖቱ ፡ የጋለ ፡ ስሜት ፡ ካለው ፡ ሕይወቱን ፡ ለመሠዋት ፡ እንኳ ፡ አይመለስም
2. (= adv.) በጋለ ፡ ስሜት. He made a passionate speech. በጋለ ፡ ስሜት ፡ ንግግር ፡ አደረገ
*He's a very passionate man. ሲወድ ፡ ከልቡ ፤ ሲጠላም ፡ እንዲሁ ፡ ነው

**passionately** በጥልቅ ፡ ስሜት
He spoke passionately of Ethiopia's sufferings in the war. በጦርነቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ስለደረሰው ፡ ሥቃይ ፡ ሲያወራ ፡ በጥልቅ ፡ ስሜት ፡ ነው

**passive**
1. ተካፋይ ፡ ያልሆነ. In spite of my efforts, the boy remained passive. ምንም ፡ ብለፋ ፡ እንኳ ፡ ልጁ ፡ ተካፋይ ፡ ሳይሆን ፡ ቀረ
2. የታዛዥነት. His son has a passive disposition. ልጁ ፡ የታዛዥነት ፡ ጠባይ ፡ አለው
*The child listened to the scolding in passive silence. ልጁ ፡ ጸጥ ፡ ብሎ ፡ ቁጣውን ፡ ተቀበለ

**passive resistance** ሰላማዊ ፡ ተቃውሞ
Gandhi was a strong believer in passive resistance. ጋንዲ ፡ የሰላማዊ ፡ ተቃውሞ ፡ ተከራካሪ ፡ ነበር

**passport** የይለፍ ፡ ወረቀት ፤ ፓስፖርት
When passing through customs, you have to

show your passport. ጉምሩክ ፡ ተቈጣጣሪዎች ፡ ዘንድ ፡ ሲደርሱ ፡ የይለፍ ፡ ወረቀት ፡ (ፓስፖርት) ፡ ማሳየት ፡ አለብዎ

**password** የመለያ ፡ ቃል ፤ የማለፊያ ፡ ቃል
In order to be allowed to enter the soldiers' camp, you have to know the password. ከወታደሮቹ ፡ ሰፈር ፡ ለመግባት ፡ የመለያውን ፡ ቃል ፡ (የማለፊያውን ፡ ቃል) ፡ ማወቅ ፡ አለብህ

**past** (n.)
1. የጥንት ፡ ታሪክ. Ethiopia's past interests historians. የኢትዮጵያ ፡ የጥንት ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎችን ፡ ይስባል
2. (= adj.) የቀረ. Slavery is a thing of the past. ባርነት ፡ የቀረ ፡ ነገር ፡ ነው
3. ያለፈ ፡ ነገር ፤ ያለፈ. History deals with the past. ታሪክ ፡ ስላለፈ ፡ ነገር ፡ ይናገራል
Try to forget the past now that your troubles are over. አሁን ፡ ችግርህ ፡ ስላለፈ ፡ ያለፈውን ፡ እርሳው
4. ጥንት. The old man talked of the past. ሽማግሌው ፡ ሰውዬ ፡ ስለ ፡ ጥንቱ ፡ ተናገረ
5. ያሳለፈው ፡ ጊዜ. The explorer had a colorful past. አሳሹ ፡ ያሳለፈው ፡ ጊዜ ፡ የሚያስደስት ፡ ነው

**past** (adj.)
1. ያለፈ. Where were you this past week? ባለፈው ፡ ሳምንት ፡ የት ፡ ነበርክ ?
2. የቀድሞ. Three past presidents of the club came to the meeting. ሦስት ፡ የክበቡ ፡ የቀድሞ ፡ ፕሬዚዳንቶች ፡ ለስብሰባው ፡ መጡ
3. የድሮ. The book describes the past glories of Greece. መጽሐፉ ፡ የግሪክን ፡ የድሮ ፡ ዝና ፡ ይገልጻል

**past** (prep.) ከ --- አለፍ ፡ ብሎ
Past the Ras Makonnen bridge, there is an optician. ከራስ ፡ መኰንን ፡ ድልድይ ፡ አለፍ ፡ ብሎ ፡ ያይን ፡ መነጽር ፡ ሻጭ ፡ ይገኛል
*It's five minutes past twelve. ስድስት ፡ ሰዓት ፡ ከምስት ፡ ደቂቃ ፡ ነው

**be past** ታለፈ
The most dangerous part of the trip is past. የጉዞው ፡ አደገኛ ፡ ክፍል ፡ ታልፏል

**go past** በ --- በኩል ፡ አለፈ
Does this bus go past Arat Kilo? ይህ ፡ አውቶቡስ ፡ በአራት ፡ ኪሎ ፡ በኩል ፡ ያልፋል ?

**in the past** ከዚህም ፡ በፊት
That has often happened in the past. ያ ፡ ከዚህም ፡ በፊት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተደርጓል

**run past** በ --- በኩል ፡ ሮጦ ፡ አለፈ
The boy ran past the house. ልጁ ፡ በቤቱ ፡ በኩል ፡ ሮጦ ፡ አለፈ

**walk right past** ባጠገብ ፡ አለፈ
He walked right past me without seeing me. ሳያየኝ ፡ ባጠገቤ ፡ አለፈ
[See also 'distant, remote']

**paste** (v.) ለጠፈ
Paste these labels on the jars! እነዚህን ፡ ምልክቶች ፡ በማሰሮዎቹ ፡ ላይ ፡ ለጥፋቸው

**paste** (n.) ሙቅ
Do you have any paste to put on this paper? ይህንን ፡ ወረቀት ፡ ማጣበቂያ ፡ ሙቅ ፡ አለህ ?

**pastime** የጊዜ ፡ ማሳለፊያ
Children need some kind of pastime on rainy days. በዝናብ ፡ ጊዜያት ፡ ሕፃናት ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ የጊዜ ፡ ማሳለፊያ ፡ ያስፈልጋቸዋል

**pastor** ካህን
The pastor of the Lutheran church will give a speech. የሉተራን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ካህን ፡ ንግግር ፡ ያደርጋሉ

**pastoral**
1. ከብት ፡ አርቢ. The pastoral tribes of the mountains graze their sheep on the hillside. ተራራዎች ፡ ላይ ፡ የሚኖሩ ፡ ከብት ፡ አርቢ ፡ ጐሳዎች ፡ በጎቻቸውን ፡ የሚያሰማሩት ፡ ጋራው ፡ ጥጋት ፡ ላይ ፡ ነው
2. ያገር ፡ ቤት. Pastoral life is depicted in these paintings. ያገር ፡ ቤት ፡ ኑሮ ፡ በነዚህ ፡ ሥዕሎች ፡ ላይ ፡ ተገልጿል
3. መንፈሳዊ. The priest read the bishop's pastoral letter to the church members. ቄሱ ፡ የጳጳሱን ፡ መንፈሳዊ ፡ መልእክት ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ አባሎች ፡ አነበቡ
4. የቅስና. Pastoral duties include visiting the sick. የቅስና ፡ ተግባር ፡ የታመሙ ፡ ሰዎችን ፡ መጐብኘት ፡ ይጨምራል

**pastry** (pastries) ብስኩት ፡ መሳይ
I like to have pastry with my coffee. ቡና ፡ ስጠጣ ፡ ብስኩት ፡ መሳይ ፡ መብላት ፡ ደስ ፡ ይለኛል

**past tense** ኀላፊ ፡ ጊዜ
The past tense of 'walk' is 'walked'. የ« መሄድ » ፡ ኀላፊ ፡ ጊዜ ፡ « ሄደ » ፡ ነው

**pasture** (v.) በላ
The sheep pastured on the hillside. በተራራው ፡ ጥጋት ፡ ላይ ፡ በጎች ፡ ይበሉ ፡ ነበር

**pasture** (n.) ግጦሽ
He takes the cattle to pasture early every

morning. ሁልቀን ፡ ማለዳ ፡ ከብቶቹን ፡ ወደ ፡ ግ
ጦሽ ፡ ይወስዳል
The rocky hillside had enough pasture for sheep. ድንጋያማው ፡ የተራራ ፡ ጥግ ፡ ለበጎች ፡
የሚበቃ ፡ ግጦሽ ፡ ነበረበት

**pasture land** የግጦሽ ፡ መሬት
The pasture land is fenced in. የግጦሹ ፡ መሬ
ት ፡ ታጥሯል

**pat** (patted)
1. አሻሸ. He patted the dog. ውሻውን ፡ አሻሸው
2. መታ ፡ መታ ፡ አደረገ. He patted me on the back to comfort me. ሊያጽናናኝ ፡ ጀርባዬን ፡ መ
ታ ፡ መታ ፡ አደረገ
3. ጠፈጠፈ. She patted the dough into a flat cake. ቂጣውን ፡ ስስ ፡ እንዲሆን ፡ ጠፈጠፈችው

**pat oneself on the back** ራሱን ፡ በራሱ ፡ አሞ
ገሰ
He has been patting himself on the back for the deal he made yesterday. ትላንት ፡ ስለፈጸ
መው ፡ ጉዳይ ፡ ራሱን ፡ በራሱ ፡ አሞገሰ

**pat** (adj.) ተገቢ
A pat solution is to work hard. ተገቢው ፡ መፍ
ትሔ ፡ ተግቶ ፡ መሥራት ፡ ነው

**stand pat** አጥብቆ ፡ ተከተለ
The government must stand pat in its policy.
መንግሥቱ ፡ መመሪያውን ፡ አጥብቆ ፡ መከተል ፡
አለበት

**patch** (v.)
1. ለጠፈ. I patched the tire, but it still leaks.
ጎማውን ፡ ለጥፌው ፡ ነበር ፡ ግን ፡ አሁንም ፡ ይተ
ነፍሳል
2. ጣፈ. Mother has to patch my trousers.
እናቴ ፡ ሱሪዬን ፡ መጣፍ ፡ አለባት

**patch together**
He patched together a speech. በችኰላ ፡ ንግግ
ር ፡ አጠናቀረ

**patch up**
1. ታረቀ. They haven't patched up their quarrel yet. በተጣሉበት ፡ ነገር ፡ አሁንም ፡ አ
ልታረቁም
2. ጠገን ፡ አደረገ. I have patched up the leak.
የሚያፈሰውን ፡ ጠገን ፡ አድርጌዋለሁ

**patch** (n.)
1. ልጥፍ. He put a new patch on the tire.
ጎማው ፡ ቡትት ፡ ላይ ፡ አዲስ ፡ ልጥፍ ፡ አደረገበት
2. እራፊ. I will have to put a new patch on the trousers. ሱሪዬ ፡ ላይ ፡ አዲስ ፡ እራፊ ፡ መጣፍ ፡
አለብኝ
3. ጨርቅ. He covered the perforation with a patch. ቀዳዳውን ፡ በጨርቅ ፡ ለጠፈ
4. ፋሻ. He wore a patch over his eye for days.
ለብዙ ፡ ቀኖች ፡ ዓይኑ ፡ ላይ ፡ ፋሻ ፡ አስሮ ፡ ነበር
5. መደብ. Her garden patch has only tomato plants in it. አትክልት ፡ መደቧ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡
የቲማቲም ፡ ተክል ፡ ብቻ ፡ ነው

**patent** (n.) የመብት ፡ ማስከበሪያ ፡ ሰነድ
He took out a patent to protect his invention.
እሱ ፡ ላደረገው ፡ ፍልሰፋ ፡ የመብት ፡ ማስከበሪያ ፡ ሰ
ነድ ፡ አወጣ

**patent** (adj.) እልም ፡ ያለ
That's a patent lie. ይህ ፡ እልም ፡ ያለ ፡ ውሸ
ት ፡ ነው

**paternal**
1. አባታዊ. He gave me some paternal advice.
አባታዊ ፡ ምክር ፡ ሰጠኝ
2. (= adv.) እንደ ፡ አባት ፡ ሆኖ. Some governors want to appear paternal. አንዳንድ ፡ ገዢዎች ፡ እ
ንደ ፡ አባት ፡ ሆነው ፡ ለመታየት ፡ ይፈልጋሉ

**paternal grandfather** ያባት ፡ አባት
My paternal grandfather is still alive. ያባቴ ፡
አባት ፡ አሁንም ፡ በሕይወት ፡ አለ

**paternalism** አባታዊ ፡ አስተዳደር
The employees appreciate the paternalism of the old president. ሠራተኞቹ ፡ የቀድሞውን ፡
ፕሬዚዳንት ፡ አባታዊ ፡ አስተዳደር ፡ ይወዳሉ

**paternity** አባት ፡ መሆን
He refused to acknowledge the paternity of the child. የልጁ ፡ አባት ፡ መሆኑን ፡ ካደ
*They couldn't trace the paternity of the child.
የልጁ ፡ አባት ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ ለማወቅ ፡ አል
ቻሉም

**path**
1. የእግር ፡ መንገድ. Keep to the path, or you will lose your way! የእግር ፡ መንገዱን ፡ ተከተ
ል ፤ ያለበለዚያ ፡ ትጠፋለህ
2. መንገድ. A narrow path leads to the river.
አንድ ፡ ጠባብ ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ ወንዙ ፡ ይወስዳል
He followed the path of righteousness all his life. ሕይወቱን ፡ በሙሉ ፡ የቅድስናን ፡ መንገድ ፡
ተከተለ

**beat a path**
*We beat a path through the tall grass. ደገላ
ውን ፡ በዱላ ፡ እየጣስን ፡ ሄድን
[See also 'cleave, duty']

**pathetic** አሳዛኝ
The cries of the wounded were pathetic. የቈስለኞቹ ፡ ጩኸት ፡ አሳዛኝ ፡ ነበር

**patience** ትዕግሥት ፤ ታጋሽነት
He lacks the patience to endure the noise of children. የልጆችን ፡ ጫጫታ ፡ ለመቻል ፡ ትዕግሥት ፡ የለውም
Parenthood requires patience and understanding. ወላጅ ፡ መሆን ፡ ታጋሽነትንና ፡ አድማጭነትን ፡ ይጠይቃል

**patient** (n.) በሽተኛ
There are two more patients waiting outside. ሌሎች ፡ ሁለት ፡ በሽተኞች ፡ ውጭ ፡ ይጠብቃሉ

**patient** (adj.)
1. ትዕግሥተኛ. The patient boy let his comrade's insult go by as though he did not hear it. ትዕግሥተኛው ፡ ልጅ ፡ የጓደኛውን ፡ ስድብ ፡ እንዳልሰማ ፡ ሰምቶ ፡ አለፈው
2. ቻይ. His wife nags him because he is very patient. በጣም ፡ ቻይ ፡ ስለሆነ ፡ ሚስቱ ፡ ትነዘንዘዋለች
*It took five years of patient labor to perfect his invention. ፍልሰፋውን ፡ ከፍጹምነት ፡ ለማድረስ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ በትዕግሥት ፡ ሠራ

**patiently** ጥርሱን ፡ ነክሶ
He endured his disease patiently. በሽታውን ፡ ጥርሱን ፡ ነክሶ ፡ ቻለ

**patriarch**
1. ባለቤት. The patriarch of the family rules with an iron hand. ባለቤቱ ፡ ቤተሰቡን ፡ በጥብቅ ፡ ያስተዳድራል
2. ባላባት. Abraham was one of the Jewish patriarchs. አብርሃም ፡ ከአይሁድ ፡ ባላባቶች ፡ አንዱ ፡ ነበር
3. ፓትሪያርክ. The Patriarch will dedicate the new church. ፓትሪያርኩ ፡ አዲሱን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይመርቃሉ

**patrimony** (patrimonies) የወረሰው ፡ ሀብት
His patrimony was worth millions of dollars. የወረሰው ፡ ሀብት ፡ ብዙ ፡ ሚሊዮን ፡ ብር ፡ የሚያወጣ ፡ ነበር

**patriot** አገሩን ፡ የሚወድ ፡ ሰው ፤ አርበኛ
Patriots will always serve their country. አገራቸውን ፡ የሚወዱ ፡ ሰዎች ፡ ምንጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ሀገራቸውን ፡ ያገለግላሉ
The patriot was a pattern of bravery. አርበኛው ፡ የጀግንነት ፡ ምሳሌ ፡ ነበር

**patriotic**
1. ያገር ፡ ፍቅር. We wrote patriotic songs for the schools. ለትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ያገር ፡ ፍቅር ፡ መዝሙሮች ፡ ጻፍን
2. ያገር ፡ ፍቅር ፡ ያለበት. The patriotic soldier fights hard. ያገር ፡ ፍቅር ፡ ያለበት ፡ ወታደር ፡ ጠንክሮ ፡ ይዋጋል

**patriotism** የሀገር ፡ ፍቅር ፤ ያገር ፡ ፍቅር
He is imbued with patriotism. በሀገር ፡ ፍቅር ፡ የተመሰጠ ፡ ነው

**patrol** (patrolled), v. እየተዘዋወረ ፡ ጠበቀ
A policeman patrols these streets all night long. ሌሊቱን ፡ በሙሉ ፡ ፖሊስ ፡ በዚህ ፡ መንገድ ፡ እየተዘዋወረ ፡ ይጠብቃል

**patrol** (n.) ቅኝት ፤ ቃኚ ፡ ጓድ
The patrol was surrounded and captured by the enemy. ቅኝቱ ፡ (ቃኚው ፡ ጓድ) ፡ በጠላት ፡ ከተከበበ ፡ በኋላ ፡ ተማረከ

**patron**
1. ደንበኛ. The patrons of this bar are asked not to be too noisy. የዚህ ፡ ቡና ፡ ቤት ፡ ደንበኞች ፡ ጩኸት ፡ እንዳያበዙ ፡ ተጠይቀዋል
2. በጎ ፡ አድራጊ. Most of the museum's expenses are paid by patrons. የቤተ ፡ መዘክሩ ፡ ወጪ ፡ አብዛኛው ፡ የሚከፈለው ፡ በበጎ ፡ አድራጊዎች ፡ ነው
[See also 'saint']

**patronage**
*Thank you for your patronage of our restaurant! እምግብ ፡ ቤታችን ፡ መጥተህ ፡ ስለተመገብህ ፡ እናመሰግንሃለን

**under the patronage of** በ --- ፡ ደጋፊነት ፡ ሥር
The exhibit was under the patronage of the Patriotic Association. ኤግዚቢሽኑ ፡ ባገር ፡ ፍቅር ፡ ማኅበር ፡ ደጋፊነት ፡ ሥር ፡ ነበር

**patronize**
1. ደንበኛ ፡ ነው. She patronizes the same dressmaker. እሷና ፡ እኔ ፡ ያንድ ፡ ልብስ ፡ ሰፊ ፡ ደንበኞች ፡ ነን
2. ረዳ. My uncle patronizes the museum. አጐቴ ፡ ቤተ ፡ መዘክሩን ፡ ይረዳል
3. ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ገመተ. Don't patronize me! I'm every bit as good as you are. በምንም ፡ ካንተ ፡ ስለማላንስ ፡ ዝቅ ፡ አድርገህ ፡ አትገምተኝ

**patron saint** ታዳጊ
Our patron saint is St. George. ታዳጊያችን ፡ ጊዮርጊስ ፡ ነው

**patronymics** ያባቱ ፡ ስም
Ethiopians are not called by their patronymics. ኢትዮጵያውያን ፡ ባባታቸው ፡ ስም ፡ አይጠሩም

**patter** ገረፈ
The rain pattered on the windowpane. ዝናቡ ፡ የመስኮቱን ፡ መስታወት ፡ ገረፈ

**patter about** ተሯሯጠ
The child pattered about the room. ልጁ ፡ በክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ተሯሯጠ

**patter on** ቀባጠረ
The salesman pattered on while displaying his wares. አሻሻጩ ፡ የሚሸጡትን ፡ እቃዎች ፡ እያሳየ ፡ ቀባጠረ

**pattern** (v.) አመሳሰለ
He patterned his life after his father's. ኑሮውን ፡ ካባቱ ፡ የኑሮ ፡ ሁኔታ ፡ ጋር ፡ አመሳሰለው

**pattern oneself after** የ - - - ፡ አርአያ ፡ ተከተለ
He patterns himself after Napoleon. የናፖሊዮንን ፡ አርአያ ፡ ይከተላል

**pattern** (n.)
1. ሐረግ. This rug has a pretty pattern. ይህ ፡ ምንጣፍ ፡ ጥሩ ፡ ሐረግ ፡ አለው
2. ንድፍ. Where did you get the pattern for your new dress? ላዲሱ ፡ ልብስሽ ፡ ንድፍ ፡ ከየት ፡ አገኘሽ ?
3. ምሳሌ. The patriot was a pattern of bravery. አርበኛው ፡ የጀግንነት ፡ ምሳሌ ፡ ነበር
4. ሁኔታ. The behavior pattern of the young generation is different from that of the old. የወጣቶች ፡ የጠባይ ፡ ሁኔታ ፡ ከዐዋቂዎች ፡ የተለየ ፡ ነው

**paucity** ማነስ
The paucity of native-born engineers harms our development. የሀገር ፡ ተወላጅ ፡ መሀንዲሶች ፡ ማነስ ፡ እድገታችንን ፡ ያደክመዋል

**pauper** የኔ ፡ ቢጤ
A pauper was out begging this morning. አንድ ፡ የኔ ፡ ቢጤ ፡ ዛሬ ፡ ጧት ፡ ሲለምን ፡ ነበር

**pause** (v.)
1. ቆም ፡ አለ. He paused each time he could not think of the proper word. ትክክለኛውን ፡ ቃል ፡ ባጣ ፡ ቁጥር ፡ ቆም ፡ ይል ፡ ነበር
2. ሰፊ ፡ ሐተታ ፡ ሰጠ. The speaker paused upon a particular point of his speech. ተናጋሪው ፡ በተለይ ፡ ባንድ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ሰፊ ፡ ሐተታ ፡ ሰጠ

**pause** (n.)
1. እልፈት. There was a pause of several seconds between each ringing of the bell. ባንዱና ፡ በተከታዩ ፡ የደወል ፡ ድምፅ ፡ መካከል ፡ የብዙ ፡ ሰከንድ ፡ እልፈት ፡ ነበር
2. ዕረፍት. Everyone welcomed the pause after the long test. ከረጅሙ ፡ ፈተና ፡ በኋላ ፡ በመጣው ፡ ዕረፍት ፡ ሁሉም ፡ ደስ ፡ አለው
*There was a pause in the fighting which lasted only a short time. ጦርነቱ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ቆም ፡ ብሎ ፡ ነበር

**after a short pause** ትንሽ ፡ ቆም ፡ ካለ ፡ በኋላ
After a short pause, the speaker continued. ትንሽ ፡ ቆም ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ ተናጋሪው ፡ ንግግሩን ፡ ቀጠለ

**pave**
1. አነጠፈ. The highway authorities are paving the street in front of our house. የአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣን ፡ ከቤታችን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ያለውን ፡ መንገድ ፡ በማንጠፍ ፡ ላይ ፡ ነው
2. ጠረገ. Technology paves the way to better living. ቴክኖሎጂ ፡ ለተሻለ ፡ ኑሮ ፡ መንገድ ፡ ይጠርጋል

**be paved** ባስፋልት ፡ ተነጠፈ
Our street has finally been paved. መንገዳችን ፡ በመጨረሻው ፡ ባስፋልት ፡ ተነጠፈ
[See also 'way']

**pavement** የተነጠፈ ፡ መንገድ
The pavement is very bumpy. የተነጠፈው ፡ መንገድ ፡ በጣም ፡ አባጣ ፡ ጐባጣ ፡ ይበዛዋል

**pavilion** [ለኤግዚቢሽን ፡ የሚያገለግል ፡ ጊዜያዊ ፡ ዳስ ፡ መሳይ ፡ ቤት]

**paving** አስፋልት
To repair the leak, the paving had to be ripped up. የሚመነጨውን ፡ ለመድፈን ፡ አስፋልቱ ፡ መቈፈር ፡ ነበረበት

**paw** (v.)
1. ፎገረ. The angry bull pawed the ground. የተናደደው ፡ ወይፈን ፡ መሬቱን ፡ ፎገረ
2. በፊት ፡ እግሩ ፡ ነካ ፡ ነካ ፡ አደረገ. The cat pawed the mouse she had caught. ድመቷ ፡ የያዘቻትን ፡ አይጥ ፡ በፊት ፡ እግሯ ፡ ነካ ፡ ነካ ፡ አደረገቻት

**paw** (n.) መዳፍ
The dog has hurt his paw. ውሻው ፡ መዳፉን ፡ ተጐዳ

**pawn** (v.) አስያዘ
I have to pawn my watch to get some money. ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ ሰዓቴን ፡ ማስያዝ ፡ አለብኝ

**pawn** (n.) መያዣ
He left his watch in pawn. ሰዓቱን ፡ መያዣ ፡ ሰጠ

**pay** (paid), vt.
1. ከፈለ. We will pay all your expenses. ወጪህን ፡ በሙሉ ፡ እንከፍላለን
2. ጠቀመ. It will pay you to follow my advice. ምክሬን ፡ ብትከተል ፡ ይጠቅምሃል
3. አስገኘ. The job pays $100 a week. ሥራው ፡ በሳምንት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ያስገኛል

**pay** (vi.) ከፈለ
If you paid, let's go! ከከፈልክ ፡ እንሂድ

**pay back**
1. ብድር ፡ መለሰ. I'll pay you back for all those insults. እንደዚያ ፡ ስለሰደብከኝ ፡ ብድሬን ፡ እመልሳለሁ
2. መለሰ. I'll pay you back the dollar on Monday. ብሩን ፡ ሰኞ ፡ እመልስልሃለሁ
3. ከፈለ. He paid me back the favor that I did him. የዋልኩለትን ፡ ውለታ ፡ ከፈለኝ

**pay down** በቅድሚያ ፡ ከፈለ
He agreed to pay $40 down and $10 a month. አርባ ፡ ብር ፡ በቅድሚያ ፡ ከፍሎ ፡ ዐሥር ፡ ብር ፡ ደግሞ ፡ በየወሩ ፡ ሊከፍል ፡ ተስማማ

**pay (for)**
1. ዋጋውን ፡ አገኘ. The thief paid for his crime with a term in jail. ሌባው ፡ እስር ፡ ቤት ፡ በመግባት ፡ ለሠራው ፡ ወንጀል ፡ ዋጋውን ፡ አገኘ
2. ተካ. Money will not pay for the loss of his home. የጠፋውን ፡ ቤቱን ፡ ገንዘብ ፡ አይተካውም

**pay for itself** ዋጋውን ፡ መለሰ
This machine will pay for itself in five months. ይህ ፡ መሣሪያ ፡ ዋጋውን ፡ ባምስት ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ይመልሳል

**pay off** ከፍሎ ፡ ጨረሰ
He paid off all his debts. ዕዳውን ፡ ሁሉ ፡ ከፍሎ ፡ ጨረሰ

**pay out** ከፈለ (ተከፈለ)
The money is paid out on Fridays. ገንዘቡ ፡ የሚከፈለው ፡ ዓርብ ፡ ዓርብ ፡ ነው

**pay up** ከፍሏል
I'm all paid up. ዕዳዬን ፡ ሁሉ ፡ ከፍያለሁ

**pay (one's) way through**
*He paid his way through college by selling magazines. መጽሔት ፡ እየሸጠ ፡ ለትምህርቱ ፡ በመክፈል ፡ ኮሌጅን ፡ ጨረሰ

[See also 'attention, call, compliment, heed, homage, notice, order, sum, tribute, visit']

**pay** (n.)
1. ደሞዝ. How much is your monthly pay? የወር ፡ ደሞዝህ ፡ ስንት ፡ ነው ?
2. ክፍያ. Equal pay for equal work. ለተመጣጣኝ ፡ ሥራ ፡ እኩል ፡ ክፍያ

**(be) payable** መከፈል ፡ አለበት
This bill is payable today. ይህ ፡ ሒሳብ ፡ ዛሬ፡ መከፈል ፡ አለበት

**payday** ልደታ
I am penniless until payday. እስከ ፡ ልደታ ፡ ባዶ ፡ እጄን ፡ ነኝ

**payment**
1. መከፈል. Prompt payment is requested. በጊዜው ፡ መከፈል ፡ አለበት
2. ክፍያ. I still have three more payments to make on my car. ለመኪናዬ ፡ ሦስት ፡ ክፍያ ፡ ቀርቶኛል
*Her thanks was payment enough for my work. ለሥራዬ ፡ ምስጋናዋ ፡ ብቻ ፡ የዋጋ ፡ ያህል ፡ ነበር

**payroll**
*How many men are on our payroll? ደሞዝ ፡ የሚከፈላቸው ፡ ስንት ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ?
*The payroll of this company is more than twenty thousand dollars a week. ይህ ፡ ኩባንያ ፡ ለሠራተኞች ፡ ደሞዝ ፡ የሚያወጣው ፡ በሳምንት ፡ ከሃያ ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ በላይ ፡ ነው

**pea** አተር
Children eat peas. ልጆች ፡ አተር ፡ ይበላሉ

**peace**
1. ሰላም. Our goal is lasting peace. ዓላማችን ፡ ዘላቂ ፡ ሰላም ፡ ነው
He doesn't give me any peace. ሰላም ፡ ይነሣኛል
2. የሰላም ፡ ውል. Peace was signed between the two countries. በሁለቱ ፡ ሀገሮች ፡ መሀከል ፡ የሰላም ፡ ውል ፡ ተፈረመ

**peace of mind** የመንፈስ ፡ ዕረፍት
Insurance gives one peace of mind. ኢንሹራንስ ፡ የመንፈስ ፡ ዕረፍት ፡ ይሰጣል

**be at peace** ሰላም ፡ ነው
The country has been at peace for the last twenty years. ከሀያ ፡ ዓመት ፡ ወዲህ ፡ አገሩ ፡ ሰላም ፡ ነው

**break the peace** ጸጥታ ፡ አደፈረሰ
He broke the peace by firing a gun. ጠመንጃውን ፡ በመተኰስ ፡ ጸጥታውን ፡ አደፈረሰ

**keep the peace** ጸጥታ ፡ አስከበረ
Three policemen were on hand to keep the peace. ጸጥታውን ፡ ለማስከበር ፡ ሦስት ፡ ፖሊሶች ፡ ተገኝተው ፡ ነበር

**make peace**
1. አስታረቀ. He tried to make peace between the quarreling parties. የተጣሉትን ፡ ወገኖች ፡ ለማስታረቅ ፡ ሞከረ
2. ታረቀ. They made peace after their bitter quarrel. የከረረ ፡ ጥል ፡ ከተጣሉ ፡ በኋላ ፡ ታረቁ

**peaceable** ሰላማዊ
Peaceable people keep out of quarrels. ሰላማዊ ፡ ሰዎች ፡ ከጠብ ፡ ይርቃሉ

**Peace Corps** የሰላም ፡ ጓድ
Peace Corps volunteers taught English in Ethiopia. የሰላም ፡ ጓድ ፡ አባሎች ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ያስተምሩ ፡ ነበር

**peaceful**
1. ጸጥ ፡ ያለ. Everything is peaceful around here. በዚህ ፡ አካባቢ ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ጸጥ ፡ ያለ ፡ ነው
2. ሰላማዊ. This peaceful tribe tries to avoid war. ይህ ፡ ሰላማዊ ፡ ነገድ ፡ ከጦርነት ፡ ለመራቅ ፡ ይሞክራል

**peach** ኮክ

**peacock** ጣውስ

**peak**
1. ጫፍ. We climbed to the peak of the mountain. ወደ ፡ ተራራው ፡ ጫፍ ፡ ወጣን
2. ጽንፍ. He was then at the peak of his power. ያኔ ፡ ከሥልጣኑ ፡ ጽንፍ ፡ ላይ ፡ ነበር
*Traffic reaches its peak on this road about five o'clock. በዚህ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ከፍተኛው ፡ የትራፊክ ፡ መጨናነቅ ፡ የሚደርሰው ፡ በዐሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ነው

**peal** (v.) ተደወለ
The bells pealed. ደወሎቹ ፡ ተደወሉ

**peal** (n.)
*A peal of laughter interrupted his speech. ክት ፡ ክት ፡ ብሎ ፡ ሲሥቅ ፡ ንግግሩ ፡ ተቋረጠ

**peanut** ኦቾሊኒ
They sell peanuts in the streets. መንገድ ፡ ላይ ፡ ኦቾሊኒ ፡ ይሸጣሉ

**pear** [የፍሬ ፡ ዓይነት]

**pearl** ሉል
The necklace is made of beautiful pearls. ድሪው ፡ ከውብ ፡ ሉል ፡ የተሠራ ፡ ነው

**peasant** ገበሬ
The peasants would like to use modern agricultural methods. ገበሬዎቹ ፡ በዘመናዊ ፡ የእርሻ ፡ ዘዴ ፡ መጠቀም ፡ ይፈልጋሉ

**pebble** ጠጠር
The path is covered with pebbles. ጠባቡ ፡ መንገድ ፡ ጠጠር ፡ ፈሶበታል

**peck** (v.)
1. ለቀመ. The chicken pecked at the grain on the ground. ዶሮዋ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ጥራጥሬ ፡ ለቀመች
2. ጠቈመ. The parrot pecked my arm. በቀቀኑ ፡ ክንዴን ፡ ጠቈመኝ

**peck a hole in** እየጠቈመ ፡ በሳ
An unhatched chick pecks a hole in the shell. ያልተቀፈቀፈች ፡ ጫጩት ፡ የእንቁላሉን ፡ ቅርፊት ፡ እየጠቈመች ፡ ትበሳለች

**peck** (n.) መስፈሪያ
Give me a peck of barley! አንድ ፡ መስፈሪያ ፡ ገብስ ፡ ስጠኝ

**give a peck** ጠቈመ
The hen gave me a peck. ዶሮዋ ፡ ጠቈመችኝ

**peculiar**
1. የተለየ ፤ እንግዳ. Her peculiar behavior has estranged her from her friends. የተለየ ፡ (እንግዳ) ፡ ጠባይዋ ፡ ከወዳጆቿ ፡ አለያያት
2. ልዩ. He is a peculiar fellow. ልዩ ፡ ሰው ፡ ነው
3. (= adv.) ብቻ. These markings are peculiar to this bird. እንዲህ ፡ ዓይነት ፡ ቀለም ፡ ያላት ፡ ይህች ፡ ወፍ ፡ ብቻ ፡ ናት

**be peculiar** ይገርማል
It is peculiar that he has not come, for he promised he would. እመጣለሁ ፡ ብሎ ፡ ቃል ፡ ገብቶ ፡ መቅረቱ ፡ የሚገርም ፡ ነው

**peculiarity** (peculiarities)
1. ልዩ ፡ ጠባይ. One of his peculiarities is his interest in birds. ከልዩ ፡ ጠባዮቹ ፡ አንዱ ፡ ለወፍ ፡ ያለው ፡ ፍቅር ፡ ነው
2. የእንግዳነት ፡ ጠባይ. In a big city, peculiarity attracts less notice than in a small town. የእንግዳነት ፡ ጠባይ ፡ ከትላልቅ ፡ ከተማዎች ፡ ይልቅ ፡ በትናንሽ ፡ ከተማዎች ፡ ውስጥ ፡ ጐልቶ ፡ ይታያል

**pecuniary** የገንዘብ
Because of his present pecuniary difficulties, he cannot afford to buy the house. ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ስላለበት ፡ የገንዘብ ፡ ችግር ፡ ምክንያት ፡ ቤቱን ፡ ሊገዛ ፡ አይችልም

**pedal** (v.), ~ **a bike** ቢስኪሌት ፡ ነድቶ ፡ ወጣ
It is hard to pedal a bike uphill. ቢስኪሌት ፡ ዳገት ፡ ነድቶ ፡ መውጣት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**pedal** (n.) መርገጫ
The pedal came off my bicycle. የቢስኪሌቴ ፡ መርገጫ ፡ ወለቀ

**step on the pedal** ቤንዚን ፡ መስጫውን ፡ ረገጠ
The driver accelerated the motor by stepping on the pedal. ነጂው ፡ ቤንዚን ፡ መስጫውን ፡ በመርገጥ ፡ የሞተሩን ፡ ፍጥነት ፡ ጨመረ

**pedantic** ጥራዝ ፡ ነጠቅ
He is a pedantic scholar. እሱ ፡ ጥራዝ ፡ ነጠቅ ፡ ምሁር ፡ ነው

**peddle** እየዞረ ፡ ሸጠ
He peddles small items like pins. እንደ ፡ ወረቀት ፡ መርፌ ፡ ያሉ ፡ ትናንሽ ፡ ነገሮች ፡ እየዞረ ፡ ይሸጣል

**peddler** ሱቅ ፡ በደረቴ ፤ አዟሪ
A peddler is hawking his wares outside. እውጭ ፡ አንድ ፡ ሱቅ ፡ በደረቴ ፡ ይህን ፡ ፈላጊ ! እያለ ፡ ይጮኻል
The dishonest peddler duped his customers. አታላዩ ፡ አዟሪ ፡ ደንበኞቹን ፡ አጭበረበረ

**pedestal** መቆሚያ
Only the pedestal of the statue remains. የቀረው ፡ የሐውልቱ ፡ መቆሚያ ፡ ብቻ ፡ ነው

**pedestrian** እግረኛ
For pedestrians only! ለእግረኞች ፡ ብቻ

**pedestrian** (adj.)
1. የእግረኞች. A pedestrian bridge crosses the highway. የእግረኞች ፡ ድልድይ ፡ አውራ ፡ ጐዳናውን ፡ ያቋርጣል
2. የማይማርክ. He gave a pedestrian lecture suitable for a general audience. ለማንም ፡ አዳማጭ ፡ የሚስማማ ፡ የማይማርክ ፡ ንግግር ፡ አደረገ

**pedigree** የዘር ፡ ግንድ
The Emperor's pedigree appears in several books. የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የዘር ፡ ግንድ ፡ ብዙ ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ ይገኛል

**have a pedigree**
Does this dog have a pedigree? ይህ ፡ ውሻ ፡ ዘሩ ፡ ጥሩ ፡ ነው ?

**peek**
1. አሾልቆ ፡ አየ. A child peeked through the door. ሕፃን ፡ በበሩ ፡ አሾልቆ ፡ አየ
2. ተመለከተ. We crept up and peeked over the wall. ቀስ ፡ ብለን ፡ ባጥሩ ፡ ላይ ፡ አጮልገን ፡ ተመለከትን

**peel** (vt.) ላጠ
I have to peel the potatoes. ድንቹን ፡ መላጥ ፡ አለብኝ

**peel** (vi.)
1. ተቀረፈ. The paint is beginning to peel. ቀለሙ ፡ መቀረፍ ፡ ጀምሯል
2. እየተቀረፈ ፡ ወደቀ. My skin is peeling. ቆዳዬ ፡ እየተቀረፈ ፡ ይወድቃል
3. ተላጠ. My back is peeling from my sunburn. ከፀሐይ ፡ ሙቀት ፡ የተነሣ ፡ ጀርባዬ ፡ ሊላጥ ፡ ነው

**peel** (n.) ቆዳ ፤ ልጣጭ
These oranges have a thick peel. እነዚህ ፡ ብርቱካኖች ፡ ወፍራም ፡ ቆዳ ፡ አላቸው
Throw away the orange peel! የብርቱካኑን ፡ ልጣጭ ፡ ጣል

**peep** (v.)
1. አሾልቆ ፡ አየ. I peeped through the window to see what she was doing. ምን ፡ ታደርግ ፡ እንደ ነበረ ፡ ለማየት ፡ በመስኮቱ ፡ አሾልቄ ፡ አየሁ
2. ብቅ ፡ ብቅ ፡ አለ. Stars peeped through the clouds. ኮከቦች ፡ በደመናው ፡ ውስጥ ፡ ብቅ ፡ ብቅ ፡ አሉ
3. ጮኸ. The little bird peeped in its nest. ትንሿ ፡ ወፍ ፡ ጎጆዋ ፡ ውስጥ ፡ ሆና ፡ ጮኸች

**peep** (n.), **let out a** ~ ትንፍሽ ፡ አለ
Quiet! Don't let out a peep! ጭጭ ፡ በል ፤ ትንፍሽ ፡ እንዳትል

**take a peep** ሰርቆ ፡ አየ
He took a peep into the room. ወደ ፡ ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ሰርቆ ፡ አየ

**peer** (v.)
1. አትኩሮ ፡ ተመለከተ. He peered into the darkness, but could see nothing. በጨለማ ፡ ውስጥ ፡ አትኩሮ ፡ ተመለከተ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ሊያይ ፡ አልቻለም
2. ብቅ ፡ አለ. The sun was peering from behind a cloud. ፀሐይዋ ፡ በደመና ፡ ውስጥ ፡ ብቅ ፡ ብላ ፡ ነበር

**peer** (n.)
1. የሚስተካከል. It will not be easy to find his

peer. እሱን ፡ የሚስተካከል ፡ ለማግኘት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው
2. እኩያ. His work can only be judged by his peers. ሥራው ፡ ሊገመት ፡ የሚችለው ፡ በእኩዮቹ ፡ ብቻ ፡ ነው

**peerless** ተወዳዳሪ ፡ የሌለው
The peerless beauty of the girl was admired by all. ተወዳዳሪ ፡ የሌለው ፡ ቁንጅናዋ ፡ በሁሉ ፡ ዘንድ ፡ ተደነቀ

**(be) peeved** ተበሳጨ
Mother will be peeved if we are late. የዘገየን ፡ እንደሆነ ፡ እናታችን ፡ ትበሳጫለች

**peevish** ብስጩ
Illness made her peevish. ሕመሙ ፡ ብስጩ ፡ አደረጋት

**peg** (v.), ~ **down** ቸከለ
We must peg down our tent. ድንኳናችንን ፡ መቸከል ፡ አለብን

**be pegged to** ከ - - - ጋር ፡ ተለዋወጠ
Our wages are pegged to living costs. ደሞዛችን ፡ ከኑሮው ፡ ውድነት ፡ ጋር ፡ ይለዋወጣል

**peg** (n.) ዕንጨት ፤ ችካል
The boards are joined by pegs. ሳንቃዎቹ ፡ የተጋጠሙት ፡ በዕንጨት ፡ ነው
This tent requires ten pegs. ይህ ፡ ድንኳን ፡ ዐሥር ፡ ችካሎች ፡ ያስፈልጉታል

**pellet** ጥይት
The pellets of a shotgun are made of lead. የረሽ ፡ ጠመንጃ ፡ ጥይቶች ፡ ከእርሳስ ፡ የተሠሩ ፡ ናቸው

**pell-mell**
1. ሳያጣጥፍ. He tossed his clothes pell-mell into the suitcase. ልብሱን ፡ ሳያጣጥፍ ፡ ሻንጣው ፡ ውስጥ ፡ ወረወረው
2. ተንጋግተው. The children rushed out onto the playground pell-mell. ልጆቹ ፡ ተንጋግተው ፡ ወደ ፡ መጫወቻ ፡ ሜዳው ፡ ሮጡ

**pelt** (v.)
1. ደበደበ. Rain pelted the roof. ዝናብ ፡ ጣሪያውን ፡ ደበደበ
2. ወረወረ. The boys pelted the windows with pebbles. ልጆቹ ፡ መስኮቶቹ ፡ ላይ ፡ ጠጠር ፡ ወረወሩ

**pelt** (n.) ቆዳ
I bought a tiger's pelt at the market. ከገበያ ፡ የነብር ፡ ቆዳ ፡ ገዛሁ

**pelvis** የወገብ ፡ አጥንት
The doctor examined the man's pelvis with an X ray. ሐኪሙ ፡ የሰውዬውን ፡ የወገብ ፡ አጥንት ፡ በራጂ ፡ መረመረ

**pen** (penned), v. አጐረ
He penned the sheep in a small enclosure. በጎቹን ፡ በትንሽ ፡ አጥር ፡ ውስጥ ፡ አጐራቸው

**pen in a corner** ወስዶ ፡ ዘጋ(በት)
He had me penned in a corner where I could not escape. ማምለጥ ፡ ከማልችልበት ፡ ወስዶ ፡ ዘጋብኝ

**be penned up** ታሰረ
His wife complained that she is penned up in the house all day. ሚስቱ ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ታስርኩ ፡ ብላ ፡ ተነጫነጨች

**pen** (n.)
1. ብዕር. This pen scratches. ይህ ፡ ብዕር ፡ ይጭራል
2. በረት ፤ ጋጣ. The cattle got out of the pen somehow. ከብቶቹ ፡ ከበረታቸው ፡ (ከጋጣቸው) ፡ እንደምንም ፡ ወጡ

**penal** የወንጀለኞች
The only settlement in the wilderness was a penal colony. በበረኻው ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ መኖሪያ ፡ የወንጀለኞች ፡ ብቻ ፡ ነበር
Penal labor is used in constructing some highways. አንዳንድ ፡ አውራ ፡ ጐዳናዎች ፡ በወንጀለኞች ፡ ጉልበት ፡ ይሠራሉ
[See also 'offense']

**penal code** የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ
The new penal code is harsh. አዲሱ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ጥብቅ ፡ ነው

**penalize** ቀጣ
The judge penalized him for speeding. ከፍጥነት ፡ በላይ ፡ በመንዳቱ ፡ ዳኛው ፡ ቀጣው

**penalty** (penalties)
1. ቅጣት. The penalty is ten years' imprisonment. ቅጣቱ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ እስራት ፡ ነው
2. መቀጮ. If you do wrong, you have to pay the penalty. ካጠፋህ ፡ መቀጮ ፡ መክፈል ፡ አለብህ
3. ሥቃይ. Indigestion is often the penalty for eating fast. የሆድ ፡ ቁርጠት ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በችኰላ ፡ ከመብላት ፡ የሚመጣ ፡ ሥቃይ ፡ ነው
[See also 'death, inflict']

**penance** ንስሐ
He tried to expiate his sin through penance. ኀጢአቱን ፡ በንስሐ ፡ ሊያስወርድ ፡ ሞከረ

**do penance** ንስሐ ፡ ገባ
He must do penance for his sins. ስለሠራው ፡ ኀጢአት ፡ ንስሐ ፡ መግባት ፡ አለበት

**pencil** እርሳስ
The point of my pencil is broken. የእርሳሴ ፡ ጫፍ ፡ ተሰብሯል

**pendant, a diamond ~** የተንጠለጠለ ፡ አልማዝ
She wore a diamond pendant as her necklace. የተንጠለጠለ ፡ አልማዝ ፡ እንደ ፡ ሐብል ፡ አድርጋ ፡ አጥልቃለች

**pending** (adj.)
1. በይደር ፡ ላይ ፡ ያለ. Tax reform is the pending business of parliament. የግብር ፡ መሻሻል ፡ በይደር ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ የፓርላማ ፡ ተግባር ፡ ነው
2. (= adv.) በቀጠሮ. The matter is still pending. ነገሩ ፡ ገና ፡ በቀጠሮ ፡ ነው

**pending**, prep. (= adv.) እስከሚደረግ ፡ ድረስ
The police sealed all the drawers of the desk pending an investigation. ፖሊሱ ፡ ምርመራ ፡ እስከሚደረግ ፡ ድረስ ፡ የጠረጴዛውን ፡ መሳቢያዎች ፡ ሁሉ ፡ አሽጋቸው
*We sat in the garden pending father's return. አባባን ፡ አትክልት ፡ ስፍራ ፡ ውስጥ ፡ ተቀምጠን ፡ ጠበቅነው
*The equipment is kept in a storehouse pending future use. ለወደፊት ፡ አገልግሎት ፡ እንዲውል ፡ መሣሪያው ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ተቀምጧል

**pendulum** የግድግዳ ፡ ሰዓት ፡ ዘንግ
The pendulum swings back and forth. የግድግዳው ፡ ሰዓት ፡ ዘንግ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ይወዛወዛል

**pendulum clock** የግድግዳ ፡ ሰዓት
The pendulum clock strikes every hour. የግድግዳው ፡ ሰዓት ፡ በየሰዓቱ ፡ ይደውላል

**penetrate** (vt.)
1. ገባ. New ideas have penetrated the countries of Asia. አዳዲስ ፡ ሐሳቦች ፡ ወደ ፡ እስያ ፡ አገሮች ፡ ገብተዋል
Smoke penetrated the living room. ጭስ ፡ ሳሎኑ ፡ ውስጥ ፡ ገብቷል
2. ደረሰ(በት). I could not penetrate the mystery. ምስጢሩን ፡ ልደርስበት ፡ አልቻልኩም
3. ሰብሮ ፡ ገባ. The bullet penetrated his skull. ጥይቱ ፡ ራስ ፡ ቅሉን ፡ ሰብሮ ፡ ገባ
4. ዘለቀ. Gradually, the sound of the bell penetrated the sleeping man's consciousness. የደወሉ ፡ ድምፅ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ የተኛውን ፡ ሰው ፡ አንጎል ፡ ዘለቀው
5. ጣሰ. The troops penetrated the enemy lines. ወታደሮቹ ፡ የጠላትን ፡ የጦር ፡ ግንባር ፡ ጣሱት
6. ሊያይ ፡ ቻለ. Our eyes couldn't penetrate the darkness. ዓይኖቻችን ፡ በጨለማ ፡ ውስጥ ፡ ሊያዩ ፡ አልቻሉም

**penetrate** (vi.) ገባ
The water penetrates slowly into the ground. ውኃው ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ መሬት ፡ ውስጥ ፡ ይገባል

**penetrating** ጥልቅ
He made a penetrating remark. ጥልቅ ፡ አስተያየት ፡ ሰጠ

**peninsula** ባሕረ ፡ ገብ ፡ መሬት
The peninsula of Italy was reunited in 1871. የኢጣልያን ፡ ባሕረ ፡ ገብ ፡ መሬት ፡ እንደገና ፡ አንድ ፡ የሆነው ፡ በ፲፰፻፸፩ ዓ. ም. ነው

**penitence** ንስሐ
He was given three Hail Marys as penitence. ለንስሐው ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ በሰላም ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ መልአክን ፡ እንዲደግም ፡ ታዘዘ

**penitent** የጸጸት
He had a penitent expression on his face. በፊቱ ፡ ላይ ፡ የጸጸት ፡ መልክ ፡ ይታይበት ፡ ነበር

**penitential** የንስሐ
Lent is a penitential season. ሁዳዴ ፡ የንስሐ ፡ ጊዜ ፡ ነው

**penitentiary** (penitentiaries) ወህኒ ፡ ቤት
Two prisoners have escaped from the penitentiary. ሁለት ፡ እስረኞች ፡ ከወህኒ ፡ ቤት ፡ አምልጠዋል

**penknife** ሰንጢ
He cut the meat with a penknife. ሥጋውን ፡ በሰንጢ ፡ ቈረጠ

**penmanship** የእጅ ፡ ጽሕፈት
His penmanship is bad. የእጅ ፡ ጽሕፈቱ ፡ መጥፎ ፡ ነው

**penniless** ባዶ ፡ እጁን
The thief snatched my purse and left me penniless. ሌባው ፡ ቦርሳዬን ፡ ነጥቆ ፡ ባዶ ፡ እጄን ፡ አስቀረኝ

**be penniless**
She is literally penniless. ቀዳዳ ፡ ፍራንክ ፡ የላትም

**penny** (pennies) ቤሳ
Let alone a dollar, I will not give you even a penny. እንኳን ፡ አንድ ፡ ብር ፡ ቤሳ ፡ አልሰጥህም
[See also 'pinch']

**penny-pinching, by ~** እየሠሠተ
He saves money by penny-pinching. እየሠሠተ ፡ ገንዘብ ፡ ያጠራቅማል

**(be) penny-wise** ገንዘብ ፡ በጣም ፡ ቈጠበ
He is penny-wise and never pays the regular price. ገንዘብ ፡ በጣም ፡ ስለሚቈጥብ ፡ የተወሰነውን ፡ ዋጋ ፡ አይከፍልም

**pension off** ጡረታ ፡ አስገባ ፤ ጡረታ ፡ መደበ
The government pensioned off the overage officers. በዕድሜ ፡ የገፉትን ፡ መኰንኖች ፡ መንግሥት ፡ ጡረታ ፡ አስገባቸው ፡ (መደባቸው)

**be pensioned** ጡረታ ፡ ገባ
He was pensioned at sixty-five. በስልሳ ፡ አምስት ፡ ዓመቱ ፡ ጡረታ ፡ ገባ

**pension** (n.) የጡረታ ፡ አበል
He received a small pension from the government. ከመንግሥት ፡ ጥቂት ፡ የጡረታ ፡ አበል ፡ አገኘ

**pensive, ~ mood** መተከዝ
His pensive mood was noticed by everyone. መተከዙን ፡ ሁሉም ፡ ዐውቆ ፡ ነበር

**be pensive** ተከዘ
Why are you so pensive today? ዛሬ ፡ ምን ፡ ነው ፡ ተክዘሃል ?

**look pensive** ተከዘ
He looks pensive today. ዛሬ ፡ ተክዟል

**pensively**
*She was pensively tapping the ground with her foot. በትካዜ ፡ መሬቱን ፡ በእግሯ ፡ ትቆረቍር ፡ ነበር

**Pentecost** የቆንጠጰስጤ ፡ በዓል
Pentecost is celebrated in our country. የቆንጠጰስጤ ፡ በዓል ፡ ባገራችን ፡ ይከበራል

**pent-up** ታፍኖ ፡ የነበረ
With the latest insult, his pent-up rage burst forth. በቅርቡ ፡ በደረሰበት ፡ ስድብ ፡ ታፍኖ ፡ የነበረ ፡ ቍጣው ፡ ገነፈለ

**be pent up** ተጨበጠ
Children love the spring after being pent up all winter. ክረምቱን ፡ ሙሉ ፡ ከተጨበጡ ፡ በኋላ ፡ ሕፃናት ፡ በልግን ፡ ይወዳሉ

**penultimate** ከመጨረሻው ፡ ቀጥሎ ፡ ያለ
The penultimate consonant in this verb is geminated. የዚህ ፡ ግስ ፡ ከመጨረሻው ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ተናባቢ ፡ ይጠብቃል

**penury** ድኽነት
His penury is due to the fact that he is ill and unable to work. ድኽነቱ ፡ በመታመሙ ፡ ምክንያት ፡ ለመሥራት ፡ ካለመቻሉ ፡ የተነሣ ፡ ነው

**of penury** (= adv.) ተቈራምዶ
He hopes to save a lot of money by living a life of penury. ተቈራምዶ ፡ ኖሮ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ለማስቀመጥ ፡ ተስፋ ፡ ያደርጋል

**people** (v.) ሰፈረ
The pioneers peopled the West. የቀድሞ ፡ ሰፋሪዎች ፡ በምዕራብ ፡ ሰፈሩ

**people** (n.)
1. ሰው. Were there many people at the meeting? ስብሰባው ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ነበር ?
2. ሰዎች. Can you name the most important people of Asia? የእስያን ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ስም ፡ ልትጠቅስ ፡ ትችላለህ ?
3. ቤቶች. You must come home with me and meet my people. እቤቴ ፡ መጥተህ ፡ ከቤቶቼ ፡ መተዋወቅ ፡ አለብህ
4. ዘሮች. My people came to America from Italy. ዘሮቼ ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ የመጡት ፡ ከኢጣልያ ፡ ነው
5. ሕዝብ. The French nobles oppressed the people. የፈረንሳይ ፡ መኳንንት ፡ ሕዝቡን ፡ ጨቈኑት
The people of Ethiopia follow ancient traditions. የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የጥንት ፡ ባህል ፡ አክባሪ ፡ ነው
Many peoples of Africa have only recently obtained their independence. ብዙ ፡ የአፍሪካ ፡ ሕዝቦች ፡ ነጻነታቸውን ፡ የተቀዳጁት ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ነው
*He does not fear what people will say. ይሉኝታ ፡ አይፈራም

**people of the village** መንደርተኞች
The people of the village like the new doctor. መንደርተኞቹ ፡ አዲሱን ፡ ሐኪም ፡ ይወዱታል
[See also 'colored, old, simple, young']

**(be) peopled** (= act.) ሰፈረ
+The area is thickly peopled by various small tribes. በቀበሌው ፡ ብዙ ፡ ትናንሽ ፡ ጐሳዎች ፡ ጥቅጥቅ ፡ ብለው ፡ ሰፍረውበታል

**pep** (v.), **~ up** አነቃቃ
A brisk walk after dinner will pep you up.

ከእራት ፡ በኋላ ፡ ፈጠን ፡ ባለ ፡ እርምጃ ፡ ብትንሸራሸር ፡ ያነቃቃሃል

**pep** (n.) ንቃት
He is full of pep. ንቃት ፡ አለው

**pepper** በርበሬ
Pepper is hot. በርበሬ ፡ ያቃጥላል

**peppery** በርበሬ ፡ የበዛበት
A peppery meal makes me thirsty. በርበሬ ፡ የበዛበት ፡ ምግብ ፡ ውኃ ፡ ያስጠማኛል

**per**
1. በ -- እጅ. I sent the letter per my son. ደብዳቤውን ፡ በልጄ ፡ እጅ ፡ ላክሁት
2. በ. How much do you earn per day? በቀን ፡ስንት ፡ ታገኛለህ ?
3. ለ. Two cars per family is the norm in many American cities. በብዙ ፡ የአሜሪካን ፡ ከተማዎች ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ መኪና ፡ ላንድ ፡ ቤተሰብ ፡ የተለመደ ፡ ነው
*How much is this sugar per kilo? ይህ ፡ ስኳር ፡ ኪሎው ፡ ስንት ፡ ነው ?

**perambulate** ተንሸራሸረ
The lovers perambulate through the park. ፍቅረኞቹ ፡ መናፈሻው ፡ ውስጥ ፡ ይንሸራሸራሉ

**per capita** የነፍስ ፡ ወከፍ
The per capita income in this country is $150. የዚህ ፡ አገር ፡ የነፍስ ፡ ወከፍ ፡ ገቢ ፡ በዓመት ፡ መቶ ፡ ኀምሳ ፡ ብር ፡ ነው

**perceive**
1. ታየ(ው). +I perceived an object looming through the mist. በጭጋጉ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ታየኝ
2. ገባ(ው). +On entering his house, he at once perceived that something was amiss. ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ሲገባ ፡ አንድ ፡ ያልሆነ ፡ ነገር ፡ መኖሩ ፡ ወዲያውኑ ፡ ገባው
I perceive that you are unwilling to do it. ልትሠራው ፡ ፈቃደኛ ፡ እንዳልሆንክ ፡ ይገባኛል
3. መሰለ(ው). +This is a nice idea, but I perceive difficulties in putting it into practice. ይህ ፡ ጥሩ ፡ ሐሳብ ፡ ነው ፤ ሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ግን ፡ ችግር ፡ የሚያመጣ ፡ ይመስለኛል
4. ተገነዘበ. I soon perceived that the air was cold. አየሩ ፡ ቀዝቃዛ ፡ መሆኑን ፡ ወዲያውኑ ፡ ተገነዘብኩ

**percent** በመቶ
The cost of living has risen ten percent. የኑሮ ፡ ዋጋ ፡ በመቶ ፡ ዐሥር ፡ ከፍ ፡ ብሏል

**percentage**
1. ከመቶ. What percentage of Ethiopians live in towns? ከኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ከመቶው ፡ ስንቱ ፡ ነው ፡ ከተማ ፡ የሚኖረው ?
2. ከመቶ ፡ እጅ. The tenant farmers get a fixed percentage of the crop. ጭሰኞቹ ፡ ከምርቱ ፡ ከመቶ ፡ የተወሰነ ፡ እጅ ፡ ይደርሳቸዋል
3. ድርሻ. The agent receives a large percentage of the painter's income. ወኪሉ ፡ ከሠዓሊው ፡ ገቢ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ድርሻ ፡ ያገኛል
*A large percentage of these books deal with Ethiopia. ከነዚህ ፡ መጽሐፎች ፡ በርከት ፡ ያሉት ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ይናገራሉ

**perceptible** ጉልህ
There is a perceptible difference between these two brothers. በነዚህ ፡ ሁለት ፡ ወንድማማቾች ፡ መካከል ፡ ጉልህ ፡ የሆነ ፡ ልዩነት ፡ አለ

**be perceptible**
1. ታየ. The ship was barely perceptible in the fog. በጭጋጉ ፡ ውስጥ ፡ መርከቡ ፡ እምብዛም ፡ አይታይም ፡ ነበር
2. ተሰማ. The sound was very perceptible. ድምፁ ፡ በጣም ፡ ይሰማ ፡ ነበር

**perception**
1. የጠለቀ ፡ አስተሳሰብ. He lacks perception into foreign affairs. ስለ ፡ ውጭ ፡ አገሮች ፡ ጉዳይ ፡ የጠለቀ ፡ አስተሳሰብ ፡ የለውም
2. የመለየት ፡ ችሎታ. His perception of color is poor. ቀለም ፡ የመለየት ፡ ችሎታው ፡ አነስተኛ ፡ ነው

**have a clear perception** በግልጽ ፡ ተረዳ
He had a clear perception of what was wrong and soon fixed it. ስሕተቱን ፡ በግልጽ ፡ ተረድቶ ፡ ስለነበር ፡ ወዲያውኑ ፡ አስተካከለው

**perceptive**
1. የተጣራ. He gave a perceptive analysis of the political situation. ስለ ፡ ፖለቲካው ፡ ሁኔታ ፡ የተጣራ ፡ ሐተታ ፡ ሰጠ
2. አስተዋይ. A perceptive writer can express the spirit of the time. አስተዋይ ፡ ደራሲ ፡ የጊዜውን ፡ መንፈስ ፡ ሊገልጽ ፡ ይችላል

**perch** (v.) አረፈ
The bird perched on a branch of the tree. ወፏ ፡ በዛፉ ፡ ቅርንጫፍ ፡ ላይ ፡ አረፈች

**be perched** ጉብ ፡ ብሎ ፡ ታየ
The fort is perched on a high hill. ምሽጉ ፡ ከፍ ፡ ካለ ፡ ጋራ ፡ ላይ ፡ ጉብ ፡ ብሎ ፡ ይታያል

**perch** (n.)
1. ቆጥ. The parrot fell off his perch and

squawked. በቀቀኑ ፡ ከቆጡ ፡ ላይ ፡ በመውደቁ ፡ ጮኸ
2. ማረፊያ. The bird sat on a perch. ወፏ ፡ ማረፊያው ፡ ላይ ፡ ተቀምጣለች

**perchance** ምናልባት + imperfect + ይሆናል
Perchance, I shall return to Ethiopia some day. ምናልባት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ኢትዮጵያ ፡ እመለስ ፡ ይሆናል

**percolate** ዘለቀ
Water percolates through sand. ውኃው ፡ አሸዋውን ፡ ይዘልቃል

**percussion** ድምፅ
The loud percussion of a drum was heard. ኀይለኛ ፡ የከበሮ ፡ ድምፅ ፡ ይሰማ ፡ ነበር

**percussion instrument** [በዕንጨት ፤ በእጅና ፡ በመሳሰሉት ፡ ነገር ፡ የሚመታ ፡ የሙዚቃ ፡ መሣሪያ]

**per diem** የቀን ፡ አበል
He gets ten dollars per diem. ዐሥር ፡ ብር ፡ የቀን ፡ አበል ፡ ያገኛል

**perdition** ሲኦል
The angry priest told him to go to perdition. የተናደደው ፡ ቄስ ፡ ሲኦል ፡ እንዲገባ ፡ ረገመው

**peregrination** ጉዞ
His peregrination made him an authority on several countries. ጉዞው ፡ ስለ ፡ ብዙ ፡ አገሮች ፡ ዐዋቂ ፡ አደረገው

**peremptory** ድርቅ ፡ ያለ
The officer's peremptory commands were uttered in a loud voice. መኰንኑ ፡ ድርቅ ፡ ያለ ፡ ትእዛዙን ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ድምፅ ፡ ተናገረ

**perennial**
1. ዘላቂነት ፡ ያለው. The perennial beauty of the lakes attracts many visitors. ዘላቂነት ፡ ያለው ፡ የሐይቆች ፡ ውበት ፡ ብዙ ፡ ጐብኚዎችን ፡ ይማርካል
2. ከዓመት ፡ እስከ ፡ ዓመት ፡ የማይደርቅ. The perennial stream never freezes. ከዓመት ፡ እስከ ፡ ዓመት ፡ የማይደርቀው ፡ ወንዝ ፡ ፈጽሞ ፡ አይረጋም
3. ከዓመት ፡ ዓመት ፡ የሚያብብ. My garden has perennial flowers. ያትክልት ፡ ቦታዬ ፡ ከዓመት ፡ ዓመት ፡ የሚያብቡ ፡ አበባዎች ፡ አሉት
*He is a perennial candidate for public office. ምርጫ ፡ በተደረገ ፡ ቁጥር ፡ ይወዳደራል

**perfect** (v.)
1. እንከን ፡ የሌለበት ፡ ሥራ. They have perfected a new engine. እንከን ፡ የሌለበት ፡ አዲስ ፡ ሞተር ፡ ሠርተዋል
2. ከፍጹምነት ፡ አደረሰ. It took five years of patient labor to perfect his invention. ፍልሰፋውን ፡ ከፍጹምነት ፡ ለማድረስ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ በትዕግሥት ፡ ሠራ

**perfect** (adj.)
1. ፍጹም. The method is not yet perfect. ዘዴው ፡ ገና ፡ ፍጹም ፡ አልሆነም
They have perfect control over the territory. ግዛቱ ፡ በነሱ ፡ ፍጹም ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ነው
2. ትክክል. He drew a perfect circle with a compass. በኮምፓስ ፡ ትክክል ፡ የሆነ ፡ ክብ ፡ ሠራ
3. ጥሩ. The car is in perfect condition. መኪናው ፡ በጥሩ ፡ አኳኋን ፡ ይገኛል
4. ሙሉ. He is in perfect health. ሙሉ ፡ ጤንነት ፡ አለው
5. እንከን ፡ የማይወጣለት. He speaks perfect French. እንከን ፡ የማይወጣለት ፡ ፈረንሳይኛ ፡ ይናገራል
6. (= adv.) ጨርሶ. He is a perfect stranger to me. እሱ ፡ ለኔ ፡ ጨርሶ ፡ እንግዳ ፡ ነው

**be perfect** እንከን ፡ የለውም
Her beauty is perfect. ቊንጅናዋ ፡ እንከን ፡ የለውም

**perfection**
1. እንከን ፡ የማይወጣለት ፡ መሆን. His perfection made everyone jealous. እሱ ፡ እንከን ፡ የማይወጣለት ፡ መሆኑ ፡ ሁሉን ፡ ሰው ፡ አስቀና
2. (= verbal noun) የተሟላ ፡ ማድረግ. Perfection of our plans will take another week. ሥራችንን ፡ [የተሟላ] ፡ ለማድረግ ፡ በተጨማሪ ፡ ሳምንት ፡ ይወስድብናል

**bring to perfection** ከፍጹምነት ፡ አደረሰ
He brought the method of painting to perfection. የሥዕል ፡ አቀባብን ፡ ዘዴ ፡ ከፍጹምነት ፡ አደረሰው

**to perfection** ፍጹም ፡ አድርጎ
He did his job to perfection. ሥራውን ፡ ፍጹም ፡ አድርጎ ፡ ሠራው

**perfectly**
1. በደንብ. He was perfectly satisfied. በደንብ ፡ ተደስቶ ፡ ነበር
2. በትክክል. He did it perfectly the first time. በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በትክክል ፡ ሠራው
3. በሚገባ. The music and the action synchronized perfectly. ሙዚቃውና ፡ ድርጊቱ ፡ በሚገባ ፡ ተስማሙ

**perfectly well** በደንብ ፡ አድርጎ
I know him perfectly well. በደንብ ፡ አድርጌ ፡ አውቀዋለሁ

**be perfectly willing** ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ፈቃደኛ ፡ ነው
He is perfectly willing to work in the evening. ማታ ፡ ማታ ፡ ለመሥራት ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ፈቃደኛ ፡ ነው

**perfidious** ሸፍጠኛ
His perfidious behavior earned him the contempt of all. ሸፍጠኛ ፡ መሆኑ ፡ በሁሉ ፡ ዘንድ ፡ አስጠላው

**perfidy** ሸፍጥ
Laval's perfidy made him notorious. የላቫል ፡ ሸፍጥ ፡ ክፉ ፡ ስም ፡ አተረፈለት

**perforate** በሳ
A nail perforated the tire. ጎማውን ፡ ምስማር ፡ በሳው
The ticket seller perforates each ticket sold. ቲኬት ፡ ሻጩ ፡ የሸጠውን ፡ ቲኬት ፡ ሁሉ ፡ ይበሳል

**perforation** ቀዳዳ
He covered the perforation with a patch. ቀዳዳውን ፡ በጨርቅ ፡ ለጠፈ

**perforce** የግድ
I must perforce consult with my lawyer in this matter. ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ከጠበቃዬ ፡ ጋር ፡ የግድ ፡ መነጋገር ፡ አለብኝ

**perform** (vt.)
1. ፈጸመ ፤ አከናወነ. He performed the task assigned him with diligence. የተሰጠውን ፡ ሥራ ፡ በትጋት ፡ ፈጸመ ፡ (አከናወነ)
2. አደረገ. Who performed the operation? ቀዶ ፡ ጥገናውን ፡ ያደረገ ፡ ማነው ?

**perform** (vi.)
1. ተጫወተ. He is performing as Hamlet tonight. ዛሬ ፡ ማታ ፡ ሃምሌትን ፡ ሆኖ ፡ ይጫወታል
2. ተግባሩን ፡ አከናወነ. He performs well on that committee. በዚያ ፡ ደርግ ፡ ውስጥ ፡ ተግባሩን ፡ ደኅና ፡ ያከናውናል

**performance**
1. አፈጻጸም. His performance of his duties leaves much to be desired. የሥራው ፡ አፈጻጸም ፡ ብዙ ፡ እንከን ፡ አለበት
2. ቅልጥፍና. The performance of his work is outstanding. የሥራው ፡ ቅልጥፍና ፡ ተወዳዳሪ ፡ የለውም
3. ትርኢይት. Our interest lagged toward the end of the performance. ወደ ፡ ትርኢይቱ ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ያለን ፡ ስሜታችን ፡ ቀዘቀዘ
4. ጨዋታ. The actor's performance was brilliant. ተዋናዩ ፡ ያሳየው ፡ ጨዋታ ፡ ድንቅ ፡ ነበር
5. ጨዋታ ፡ ማሳየት. The young actor was tremulous before the performance. ወጣቱ ፡ ተዋናይ ፡ ጨዋታውን ፡ ከማሳየቱ ፡ በፊት ፡ ተርበደበደ
6. ዘፈን. The singer's performance was brilliant. ዘማሪው ፡ ያሰማው ፡ ዘፈን ፡ ድንቅ ፡ ነበር
*There are two performances of the play on Saturday. ቅዳሜ ፡ ቲያትሩ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ይታያል
[See also 'skillful']

**performer** ተጫዋች ፤ ተዋናይ
They gave the performer a big hand. ለተጫዋቹ ፡ (ለተዋናዩ) ፡ የጋለ ፡ ጭብጨባ ፡ አደረጉለት

**perfume** (v.)
1. አወደ. Roses perfumed the air. የጽጌ ፡ ረዳ ፡ መዐዛ ፡ አየሩን ፡ አወደው
2. ሽቶ ፡ ረጨ. He perfumed the air to hide the smell of roasted meat. የተጠበሰውን ፡ ሥጋ ፡ ሽታ ፡ ለማጥፋት ፡ ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ሽቶ ፡ ረጨ

**perfume** (n.) ሽቶ
I smell perfume in the air. ሽቶ ፡ ይሸተኛል
She bought the perfume in Paris. ሽቶውን ፡ ከፓሪስ ፡ ገዛች

**perfunctory**
1. ግዴለሽ. Her perfunctory performance caused her boss to fire her. ግዴለሽ ፡ አሠራሯ ፡ አለቃዋ ፡ እንዲያባርራት ፡ ምክንያት ፡ ሆነ
2. ካንገት ፡ በላይ ፡ የሆነ. His perfunctory cordiality didn't impress me. ካንገት ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ትሕትናው ፡ ስሜት ፡ አልሰጠኝም

**perhaps** ምናልባት
Perhaps I'll come along with you. ምናልባት ፡ አብሬህ ፡ እመጣለሁ

**peril** አደጋ
Travelers in the desert are in peril if they cannot find water. የምድረ ፡ በዳ ፡ መንገደኞች ፡ ውኃ ፡ ካላገኙ ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ ይወድቃሉ

**perilous** አደገኛ
They went on a perilous journey. አደገኛ ፡ ጉዞ ፡ አደረጉ

**period**
1. ዘመን. The last century was an interesting period in American history. ያለፈው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ በአሜሪካ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ የሚያስደንቅ ፡ ዘመን ፡ ነበረ

2. ጊዜ. He worked here for a short period. ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ እዚህ ፡ ይሥራ ፡ ነበር
3. ክፍለ ፡ ጊዜ. I have a third period free. በሦስተኛው ፡ ክፍለ ፡ ጊዜ ፡ ነጻ ፡ ነኝ
4. አራት ፡ ነጥብ. You forgot to put a period here. እዚህ ፡ አራት ፡ ነጥብ ፡ ማድረግ ፡ ረሳህ

**periodic** (= periodically) አልፎ ፡ አልፎ
He has periodic attacks of malaria. አልፎ ፡ አልፎ ፡ ወባ ፡ ትነሣበታለች
His periodic visits cheered up the ill. አልፎ ፡ አልፎ ፡ ሊጠይቃቸው ፡ መሄዱ ፡ ሕመምተኞቹን ፡ አበረታታ

**periodical** (n.) መጽሔት
I subscribe to several periodicals. በርከት ፡ ያሉ ፡ መጽሔቶች ፡ በደንበኝነት ፡ እገዛለሁ

**periodically** በየወቅቱ
Eclipses occur periodically. የፀሐይ ፡ ግርዶሽ ፡ በየወቅቱ ፡ ይደርሳል
*This stream flows periodically in the rainy season. ይህ ፡ ወንዝ ፡ ክረምት ፡ ክረምት ፡ ይሞላል

**periphery**
1. ጠረፎች. The periphery of Ethiopia is settled largely by nomads. በኢትዮጵያ ፡ ጠረፎች ፡ የሚኖሩት ፡ አብዛኞዎቹ ፡ ሰዎች ፡ ዘላኖች ፡ ናቸው
2. ዳር. The airport is located at the periphery of the city. አውሮፕላን ፡ ማረፊያው ፡ የሚገኘው ፡ ከተማው ፡ ዳር ፡ ነው

**perish**
1. አለቀ. Hundreds of people perished in the earthquake. በመሬቱ ፡ መንቀጥቀጥ ፡ በብዙ ፡ መቶ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ሰዎች ፡ አለቁ
2. ሞተ. In the fury of the battle, many soldiers perished. በተፋፋመው ፡ ጦርነት ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ወታደሮች ፡ ሞቱ
3. ተበላሸ. Some fruits perish quickly if not properly packed. አንዳንድ ፡ ፍራፍሬዎች ፡ በደንብ ፡ ካልታሸጉ ፡ ቶሎ ፡ ይበላሻሉ

**perishable** የሚበላሽ
These vegetables are perishable, so keep them in the refrigerator. እነዚህ ፡ አትክልቶች ፡ የሚበላሹ ፡ ስለሆኑ ፡ በማቀዝቀዣው ፡ ውስጥ ፡ አስቀምጧቸው

**perjure, ~ oneself** በሐሰት ፡ መሰከረ
He perjured himself at the trial. በሙግቱ ፡ ጊዜ ፡ በሐሰት ፡ መሰከረ

**perjuror** በሐሰት ፡ የመሰከረ
The perjuror was jailed by the judge. በሐሰት ፡ የመሰከረው ፡ በዳኛው ፡ ትእዛዝ ፡ ታሰረ

**perjury** በሐሰት ፡ መመስከር
Perjury is punishable by a fine or imprisonment. በሐሰት ፡ መመስከር ፡ በገንዘብ ፡ ወይም ፡ በእስራት ፡ ያስቀጣል

**perk** አቆመ
The dog perked his ears when he heard his master's voice. ውሻው ፡ የጌታውን ፡ ድምፅ ፡ ሲሰማ ፡ ጆሮውን ፡ አቆመ

**perk up** (vt.) አነቃቃ
His compliment perked her up. የሱ ፡ ምስጋና ፡ አነቃቃት

**perk up** (vi.) ነቃ ፡ ነቃ ፡ አለ
The sick girl perked up when she received the flowers. የታመመችው ፡ ልጅ ፡ አበባውን ፡ ስታገኝ ፡ ነቃ ፡ ነቃ ፡ አለች

**permanency** ረዥም ፡ ላለ ፡ ጊዜ ፡ መቆየት
The permanency of the financial crisis nearly ruined the country. የገንዘብ ፡ ችግር ፡ ረዥም ፡ ላለ ፡ ጊዜ ፡ መቆየቱ ፡ አገሪቱን ፡ ሊያጠፋት ፡ ምንም ፡ አልቀረውም ፡ ነበር

**permanent** ቋሚ
At the moment, I have no permanent address. ለጊዜው ፡ ቋሚ ፡ አድራሻ ፡ የለኝም

**permanently** ለሁል ፡ ጊዜ ፤ ለዘለቄታው
The road is closed temporarily, not permanently. መንገዱ ፡ የተዘጋው ፡ ለጊዜው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለሁል ፡ ጊዜ ፡ (ለዘለቄታው) ፡ አይደለም

**permeable** ውኃ ፡ የሚመጥ
This permeable soil is not fit for plowing. ይህ ፡ ውኃ ፡ የሚመጥ ፡ መሬት ፡ ለእርሻ ፡ አይሆንም

**be permeable** ፈሳሽ ፡ ነገርን ፡ መጠጠ
Blotting paper is a permeable material. የማምጠጫ ፡ ወረቀት ፡ ፈሳሽ ፡ ነገርን ፡ ይመጣል

**permeate**
1. ዘለቀ ፤ በሙሉ ፡ ዘለቀ. The rain permeated the roof. ዝናቡ ፡ ጣሪያውን ፡ ዘለቀ
The water has permeated the soil. ውኃው ፡ አፈሩን ፡ በሙሉ ፡ ዘልቆታል
2. ዘለቀ ፤ ገባ. New ideas have permeated even the uneducated class. አዲስ ፡ ሐሳብ ፡ ያልተማረውን ፡ ሕዝብ ፡ እንኳን ፡ ዘልቆታል ፡ (ገብቶታል)
3. አወደ. The smells of cooking permeated the house. የምግብ ፡ ሽታ ፡ ቤቱን ፡ አወደው

**(be) permissible** ተፈቀደ
Playing in the park is permissible only during the daytime. መናፈሻው ፡ ስፍራ ፡ ውስጥ ፡ መጫወት ፡ የሚፈቀደው ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡ ነው

**permission** ፈቃድ ፣ ፍቃድ
He asked for permission to visit his parents. ወላጆቹን ፡ ለመጠየቅ ፡ ፈቃድ ፡ ጠየቀ

**grant permission** ፈቀደ(ለት)
He granted us permission to leave early. ቀደም ፡ ብለን ፡ እንድንሄድ ፡ ፈቀደለን

**permissive** ልል
She is very permissive, and so her children often do bad things. በጣም ፡ ልል ፡ ስለሆነች ፡ ልጆቿ ፡ በየጊዜው ፡ መጥፎ ፡ ነገሮች ፡ ያደርጋሉ

**permit** (permitted), vt. ፈቀደ
I can't permit smoking in my house. ቤቴ ፡ ውስጥ ፡ ሲጃራ ፡ እንዲጨስ ፡ አልፈቅድም
Permit me to explain my case! ጉዳዬን ፡ እንዳቀርብ ፡ ይፍቀዱልኝ

**permit** (vi.) አመቸ
We will fly if weather permits. ያየሩ ፡ ሁኔታ ፡ ካመቸ ፡ ባውሮፕላን ፡ እንሄዳለን
*Write when time permits. ሲመችህ ፡ ጻፍ

**be permitted** ተፈቀደ
No one is permitted to enter this building. እዚህ ፡ ሕንጻ ፡ ውስጥ ፡ ማንም ፡ እንዲገባ ፡ አይፈቀድለትም
Is smoking permitted? ሲጃራ ፡ ማጨስ ፡ ይፈቀዳል ?

**permit** (n.) የፈቃድ ፡ ወረቀት
Have you a permit to hunt on this land? እዚህ ፡ ቦታ ፡ እንድታድን ፡ የፈቃድ ፡ ወረቀት ፡ አለህ ?

**permitting**
*Weather permitting, we sail on Monday. አየሩ ፡ ከተስማማን ፡ ሰኞ ፡ በመርከብ ፡ እንነሣለን

**permutation** እያለዋወጡ ፡ ማስቀመጥ
The permutation of numbers is an important part of math. ቁጥሮችን ፡ እያለዋወጡ ፡ ማስቀመጥ ፡ የሒሳብ ፡ ዋናው ፡ ክፍል ፡ ነው

**permute** ለወጠ
Time permutes all customs. ጊዜ ፡ ልማዶቹን ፡ ሁሉ ፡ ይለውጣል

**pernicious** ጠንቅ
This pollution of the air is pernicious to our health. ይህ ፡ ያየር ፡ መበላሸት ፡ ለጤናችን ፡ ጠንቅ ፡ ነው

**perpendicular**
1. ቀጥ ፡ ብሎ ፡ የሚወርድ. He drew a perpendicular line on the board. በሰሌዳው ፡ ላይ ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ የሚወርድ ፡ መሥመር ፡ ሣለ
2. ቀጥ ፡ ያለ. The wall should be perpendicular to the floor. ግድግዳው ፡ ከወለሉ ፡ ጋር ፡ ሲተያይ ፡ ቀጥ ፡ ያለ ፡ መሆን ፡ አለበት

**perpetrate** ፈጸመ
He perpetrated a crime on the ignorant farmer. በደንቆሮው ፡ ገበሬ ፡ ላይ ፡ ወንጀል ፡ ፈጸመ
[See also 'fraud']

**perpetual**
1. የማያቋርጥ. She is tired of their perpetual chatter. የማያቋርጠው ፡ ወሬያቸው ፡ ሰልችቷታል
2. ዘላቂ. This insurance will provide your children with a perpetual income. ይህ ፡ የሕይወት ፡ ዋስትና ፡ ለልጆችህ ፡ ዘላቂ ፡ ገቢ ፡ ይሆናቸዋል

**perpetually**
1. ሁልጊዜ. He is perpetually late. ሁልጊዜ ፡ ዘግይቶ ፡ ይመጣል
2. ያለማቋረጥ. The earth turns perpetually on its axis. መሬት ፡ ያለማቋረጥ ፡ በዘንጓ ፡ ላይ ፡ ትሽከረከራለች

**perpetuate** ጠብቆ ፡ አቆየ
This statue will perpetuate the memory of our heroes. ይህ ፡ ሐውልት ፡ የጀግኖቻችንን ፡ ትዝታ ፡ ጠብቆ ፡ ያቆያል

**perpetuity, in ~**
1. እስከነጭራሹ. This land has been given to the church in perpetuity. ይህ ፡ መሬት ፡ እስከነጭራሹ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተሰጥቷል
2. ለዘለቄታው. The charity was established in perpetuity by the millionaire. ሀብታሙ ፡ የበጎ ፡ አድራጎቱን ፡ ድርጅት ፡ ያቋቋመው ፡ ለዘለቄታው ፡ ነው

**perplex** ግራ ፡ አጋባ ፣ አደናገረ
The problems perplexed him greatly. ፕሮብሌሙ ፡ በጣም ፡ ግራ ፡ አጋባው
His talk perplexed me. ንግግሩ ፡ አደናገረኝ

**perplexed** (adv.) ግራ ፡ ገብቶት
He stood perplexed at the crossroads, not knowing which way to go. የት ፡ እንደሚሄድ ፡ ግራ ፡ ገብቶት ፡ በመንገዶቹ ፡ መገናኛ ፡ ላይ ፡ ቆመ

**perplexity** (perplexities)
1. መደናገር. His perplexity was so great that he had to ask several people for advice. በጣም ፡ ከመደናገሩ ፡ የተነሣ ፡ ከብዙ ፡ ሰዎች ፡ ምክር ፡ መጠየቅ ፡ ነበረበት
2. የሚያደናግር ፡ ነገር. There are many perplexities in such a complicated job. እንዲህ ፡ በተወሳሰበ ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ የሚያደናግሩ ፡ ነገሮች ፡ አሉ

**perquisite, as a ~** ከደሞዙ ፡ ሌላ

The maid had the old dresses of her mistress given her as a perquisite. ገረዲቱ ፡ ከደሞዟ ፡ ሌላ ፡ የሚሰጣትን ፡ የእመቤቷን ፡ አሮጌ ፡ ልብስ ፡ ታስቀምጥ ፡ ነበር

**persecute**

1. አሠቃየ. The Romans persecuted the Christians in the early days. በጥንት ፡ ዘመን ፡ ሮማውያን ፡ ክርስቲያኖችን ፡ አሠቃይተዋቸዋል
2. አስቸገረ. The older boys in school persecuted the younger ones. በትምህርት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ትልልቆቹ ፡ ትንንሾቹን ፡ ልጆች ፡ አስቸገሯቸው
3. ሊያጠቃው ፡ ፈለገ. He is possessed by the idea that someone is persecuting him. አንድ ፡ ሰው ፡ ሊያጠቃኝ ፡ ይፈልጋል ፡ በሚል ፡ ሐሳብ ፡ ተውጧል

**persecution** ማሠቃየት

The boy's persecution of the kitten was cruel. የልጁ ፡ ድመቲቷን ፡ ማሠቃየት ፡ የጭካኔ ፡ ሥራ ፡ ነበር

*The persecution of the Christians by the Romans is described in this book. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ሮማውያን ፡ ክርስቲያኖችን ፡ እንዳሠቃዩዋቸው ፡ ይገልጻል

*He remained secure in his faith despite persecution. ቢያሳድዱት ፡ እንኳ ፡ በእምነቱ ፡ ጸንቶ ፡ ቆየ

**perseverance** የመጣጣር ፡ ብዛት

By perseverance, the lame boy learned to swim. ከመጣጣር ፡ ብዛት ፡ አንካሳው ፡ ልጅ ፡ መዋኘት ፡ ለመደ

**persevere**

1. ያለመሰልቸት ፡ ጣረ. He persevered until he learned how to do it perfectly. በደንብ ፡ መሥራት ፡ እስኪቻለ ፡ ድረስ ፡ ያለመሰልቸት ፡ ጣረ
2. ወደ ፡ ኋላ ፡ አላለም. She persevered in the face of many obstacles. ብዙ ፡ ችግር ፡ ቢያጋጥማትም ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አላለችም

**Persian**

1. ፋርስ. Persians used to rule Yemen. ፋርሶች ፡ የመንን ፡ ይገዙ ፡ ነበር
2. የፋርስ ፡ ቋንቋ. Can you speak Persian? የፋርስ ፡ ቋንቋ ፡ መናገር ፡ ትችላለህ ?

**persist**

1. ቀጠለ. He persisted in asking embarrassing questions. አሳፋሪ ፡ ጥያቄዎች ፡ መጠየቁን ፡ ቀጠለ
2. ቆየ. The fog is likely to persist in most areas. ጭጋጉ ፡ በብዙ ፡ ቦታዎች ፡ ሳይቆይ ፡ አይቀርም

*He persists in reading in bed. አልጋ ፡ ላይ ፡ ተጋድሜ ፡ ካላነበብኩ ፡ ይላል

*The child persists in playing in the living room. ልጁ ፡ አሻፈረኝ ፡ ብሎ ፡ እንግዳ ፡ ማረፊያው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ይጫወታል

**persistence** መንፈስ ፡ ጠንካራነት

By persistence, many people won religious freedom. በመንፈስ ፡ ጠንካራነት ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ የሃይማኖት ፡ ነጻነት ፡ አገኙ

**persistent**

1. ያልተቈጠበ. Only persistent effort will effectuate the desired results. ያልተቈጠበ ፡ ጥረት ፡ ብቻ ፡ የተፈለገውን ፡ ውጤት ፡ ያስገኛል
2. የማያቋርጥ. Last August was a month of persistent rain. ያለፈው ፡ ነሐሴ ፡ የማያቋርጥ ፡ ዝናም ፡ የዘነበበት ፡ ወር ፡ ነበር
3. ቶሎ ፡ የማይጠፋ. Walking through the house, I became aware of the persistent odor of pepper. እቤት ፡ ውስጥ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ስል ፡ ቶሎ ፡ የማይጠፋ ፡ የበርበሬ ፡ ሽታ ፡ ሸተተኝ
4. (= adv.) ነጋጠባ. He gave in to her persistent demands and bought her a fur coat. እሷ ፡ ነጋጠባ ፡ በምታደርገው ፡ ጉትጐታ ፡ ተሸንፎ ፡ አንድ ፡ ጸጉራማ ፡ ኮት ፡ ገዛላት

*He suffers persistent attacks of malaria. ወባው ፡ ይመላለስበታል

**person**

1. ሰው. She is a nice person. ጥሩ ፡ ሰው ፡ ነች
2. ሰውነት. We should keep our persons clean. ሰውነታችንን ፡ በንጽሕና ፡ መጠበቅ ፡ አለብን
3. መደብ. The verb agrees with the subject in person and gender. ግስ ፡ በመደብና ፡ በጾታ ፡ ከባለቤት ፡ ጋር ፡ ይስማማል

**in person**

1. ራሱ. I shall be present at the meeting in person. ስብሰባው ፡ ላይ ፡ ራሴ ፡ እገኛለሁ
2. በጁ. Please deliver this to him in person! አደራህን ፡ ይህንን ፡ በጁ ፡ ስጠው

**per person** እያንዳንዳቸው

They paid fifty cents per person to see the show. ትርኢይቱን ፡ ለማየት ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ኀምሳ ፡ ሳንቲም ፡ ከፈሉ

**this person** ይህ ፡ ሰውዬ

This person is the only one here who knows Amharic. እዚህ ፡ አማርኛ ፡ የሚያውቅ ፡ ይህ ፡ ሰውዬ ፡ ብቻ ፡ ነው

**personable** መልክ ፡ መልካም
He is a personable young man. መልክ ፡ መልካም ፡ ወጣት ፡ ነው

**personage** ሰው
Important personages will attend the ceremonies. ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ በሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ላይ ፡ ይገኛሉ
[See also 'kingly']

**personal**
1. የግል. He would like to discuss a personal matter with you. ካንተ ፡ ጋር ፡ የግል ፡ ጉዳይ ፡ ለመወያየት ፡ ይፈልጋል
They confiscated everything, even personal property. የግል ፡ ንብረት ፡ እንኳን ፡ ሳይቀር ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ወረሱ
2. የግል ፡ ሁኔታ. Reporters invaded his privacy by asking personal questions. ጋዜጠኞች ፡ ስለግል ፡ ሁኔታ ፡ እየጠየቁ ፡ በግል ፡ ኑሮው ፡ ጣልቃ ፡ ገቡበት
3. እሱን ፡ የሚነካ ፡ ነገር. I meant nothing personal, so do not take my remarks to heart. አንተን ፡ የሚነካ ፡ ነገር ፡ ስላላሰብኩ ፡ የሰጠሁትን ፡ አስተያየት ፡ ከከፋት ፡ አትቍጠረው
*The Emperor paid the soldier a personal visit while he was in a hospital. ወታደሩ ፡ ሆስፒታል ፡ ተኝቶ ፡ ሳለ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሄደው ፡ ጠየቁት
*Do you have personal knowledge of this matter? ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ራስህ ፡ የምታውቀው ፡ ነገር ፡ አለ ?

**be personal** ሰው ፡ ነካ
He always becomes personal in a dispute. በክርክር ፡ ጊዜ ፡ ዘወትር ፡ ሰው ፡ ይነካል

**personal beauty** መልክ
Personal beauty is not as important as intelligence. መልክ ፡ የብልህነትን ፡ ያህል ፡ አይጠቅምም
[See also 'personal pronoun']

**personality** (personalities)
1. ባሕርይ. The two brothers have different personalities. ሁለቱ ፡ ወንድማማቾች ፡ የተለያየ ፡ ባሕርይ ፡ አላቸው
2. ጠባይ. The boy is developing a fine personality. ልጁ ፡ ጥሩ ፡ ጠባይ ፡ ይዟል
3. ማንነት. You have to respect a child's personality. የልጅን ፡ ማንነት ፡ ልታከብርለት ፡ ይገባል
4. እሱነት. An author leaves an imprint of his personality on what he writes. ጸሐፊ ፡ በሚጽፈው ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ እሱነቱን ፡ የሚገልጽ ፡ ይታይበታል
5. ሰው. He is a leading personality of the theater. እሱ ፡ በቲያትር ፡ ቤቱ ፡ ከፍተኛ ፡ ሰው ፡ ነው

**personally**
1. በበኩሉ. Personally, I have no objection to your joining us. በበኩሌ ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ብትሆን ፡ አልቃወምም
2. እሱን ፡ ራሱን. I would like to speak to him personally. እሱን ፡ ራሱን ፡ ለማነጋገር ፡ እፈልጋለሁ
3. ራሱ. The hostess personally saw to the comfort of her guests. ባለቤቲቱ ፡ ራሳቸው ፡ እንግዶቹን ፡ ተከባከቡ
*I dislike the painter personally, but I respect his talent. ለሥዓሊው ፡ የግል ፡ ጥላቻ ፡ ቢኖረኝም ፡ ችሎታውን ፡ አደንቃለሁ

**take personally**
She took his remark personally. የሰጠውን ፡ አስተያየት ፡ በሷ ፡ ላይ ፡ የተሰነዘረ ፡ አድርጋ ፡ ቈጠረችው

**personal pronoun** ምድብ ፡ ተውላጠ ፡ ስም
"I", "you", and "he" are personal pronouns. « እኔ » ፤ « አንተ » ና ፡ « እሱ » ፡ ምድብ ፡ ተውላጠ ፡ ስሞች ፡ ናቸው

**personification** መልካም ፡ ምሳሌ
She is the personification of neatness. ለንጽሕና ፡ መልካም ፡ ምሳሌ ፡ ናት

**personify** (personified)
1. መሰለ. The poet personified truth as a beautiful maiden. ገጣሚው ፡ እውነትን ፡ በውብ ፡ ወይዘሮ ፡ መሰላት
2. የ - - - ምሳሌ ፡ ነው ፤ የ - - - መጨረሻ ፡ ነው. A snake personifies the devil. እባብ ፡ የሰይጣን ፡ ምሳሌ ፡ ነው
This man personifies avarice. ይህ ፡ ሰው ፡ የንፉግ ፡ መጨረሻ ፡ ነው

**personnel** ሠራተኞች
There is a lack of trained personnel. የሠለጠኑ ፡ ሠራተኞች ፡ እጥረት ፡ አለ
[See also 'authorized']

**perspective**
1. አስተያየት. You must view foreign affairs in the proper perspective. የውጭ ፡ ሀገርን ፡ ጉዳይ ፡ በተገቢው ፡ አስተያየት ፡ መመልከት ፡ አለብህ
2. ሐሳብ. Working in a factory gave him a new perspective in labor problems. በፋብሪካው ፡ ውስጥ ፡ መሥራት ፡ ስለ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ችግር ፡ አዲስ ፡ ሐሳብ ፡ ጨመረለት

**in perspective** ርቀትንና ፡ ቅርበትን ፡ ጠብቆ
It is difficult to learn how to draw in perspective. ርቀትንና ፡ ቅርበትን ፡ ጠብቆ ፡ ሥዕል ፡ መሣልን ፡ መማር ፡ ከባድ ፡ ነው

**perspicacious**
1. አስተዋይ. He is a perspicacious person, so you can rely on whatever he tells you. አስተዋይ ፡ ስለሆነ ፡ በሚነግርህ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ልትተማመን ፡ ትችላለህ
2. ሎሌ. The perspicacious trader made a large profit selling grain. ሎሌው ፡ ነጋዴ ፡ እህል ፡ በመሸጥ ፡ ከፍተኛ ፡ ትርፍ ፡ አገኘ

**perspicacity** ልቡና
He judges with great perspicacity. በብሩህ ፡ ልቡና ፡ ያስተውላል

**perspiration** ላብ
His shirt was wet with perspiration. ሸሚዙ ፡ በላብ ፡ በስብሶ ፡ ነበር

**perspire** አላበ(ው)
He perspired so profusely that his shirt was wet. በጣም ፡ ስላላበው ፡ ሸሚዙ ፡ ርሷል

**persuade** አግባባ
He persuaded me to accept the money. ገንዘቡን ፡ እንድቀበል ፡ አግባባኝ

**persuasion**
1. (= being persuaded) መግባባት. Exertion of authority is not always appıopriate; persuasion may be better. በሥልጣን ፡ ኀይል ፡ ብቻ ፡ መሥራት ፡ ሁልጊዜ ፡ ጥሩ ፡ አይደለም ፤ መግባባት ፡ ይሻል ፡ ይሆናል
2. እምነት. The two brothers had different political persuasions. ሁለቱ ፡ ወንድማማቾች ፡ የተለያየ ፡ የፖለቲካ ፡ እምነት ፡ ነበራቸው
*I am open to persuasion. የሰው ፡ ሐሳብ ፡ ለመስማት ፡ ዝግጁ ፡ ነኝ

**persuasive** የማግባባት
The salesman had a very persuasive way of talking. አሻሻጩ ፡ ሰው ፡ የማግባባት ፡ ችሎታው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው

**pert** ደፋር
The pert girl was scolded by the teacher. አስተማሪው ፡ ደፋሯን ፡ ልጃገረድ ፡ ገሠጸት

**pertain**
1. ተመለከተ. This does not pertain to you. ይህ ፡ አንተን ፡ አይመለከትም
These are the duties that pertain to your new job. አዲሱን ፡ ሥራህን ፡ የሚመለከቱት ፡ ተግባሮች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው
2. አስፈላጊ ፡ ሆነ ፤ ተገቢ ፡ ሆነ. We had goose and everything else that pertains to a holiday dinner. ዝዪና ፡ ሌሎችም ፡ ለበዓል ፡ ቀን ፡ እራት ፡ አስፈላጊ ፡ (ተገቢ) ፡ የሆኑ ፡ የምግብ ፡ ዓይነቶች ፡ ሁሉ ፡ ነበሩን

**pertaining** ከነ - -
He bought the house and the land pertaining to it. መሬቱን ፡ ከነቤቱ ፡ ገዛው

**pertinacious**
1. የማያቋርጥ. His pertinacious efforts finally resulted in his getting the job. የማያቋርጥ ፡ ጥረቱ ፡ በመጨረሻ ፡ ሥራውን ፡ አስገኘለት
2. ሞዛዛ. A pertinacious salesman offends many of his customers. ሞዛዛ ፡ አሻሻጭ ፡ ብዙ ፡ ደንበኞቹን ፡ ያበሳጫል

**pertinence** ተገቢነት
The pertinence of the boy's replies shows that he is not stupid. የልጁ ፡ መልስ ፡ ተገቢነት ፡ ደደብ ፡ አለመሆኑን ፡ ያመለክታል

**pertinent**
1. ተገቢ. He made a pertinent comment on the international situation. ስለ ፡ ዓለም ፡ ሁኔታ ፡ ተገቢ ፡ አስተያየት ፡ ሰጠ
2. አግባብነት ፡ ያለው. His observations are not always pertinent. የሚሰጣቸው ፡ አስተያየቶች ፡ ሁልጊዜ ፡ አግባብነት ፡ ያላቸው ፡ አይደሉም
3. አስፈላጊ. He informed himself of all the pertinent facts. አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ መረጃዎች ፡ ሁሉ ፡ ተረዳ

**perturb** አሳሰበ
The rise in crime perturbs many people. የወንጀል ፡ መብዛት ፡ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ያሳስባል

**perusal** በጥንቃቄ ፡ ማንበብ
His daily perusal of the newspaper takes him an hour. በየቀኑ ፡ በጥንቃቄ ፡ ጋዜጣ ፡ ማንበቡ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ይፈጅበታል

**peruse** በጥንቃቄ ፡ አነበበ
He perused the book. መጽሐፉን ፡ በጥንቃቄ ፡ አነበበ

**pervade**
1. አወደ. The odor of roses pervades the air. የጽጌ ፡ ረዳ ፡ መዓዛ ፡ አየሩን ፡ ያውዳል
2. ዐጠነ ፤ በከለ ፤ አወደ. The stink of rotting meat pervaded the air. የገማው ፡ ሥጋ ፡ ሽታ ፡ አየሩን ፡ ዐጠነው ፡ (በከለው ፤ አወደው)
3. ሞላ. A sickening odor of burned flesh pervaded the room. የሚያቅለሸልሽ ፡ ያረረ ፡ ሥጋ ፡ ሽታ ፡ ክፍሉን ፡ ሞላው

4. ሰፈነ(በት). Joy pervades his poems. ግጥሙ ፡ ሁሉ ፡ ደስታ ፡ ሰፍኖበታል

**perverse**

1. እልኸኛ. The perverse child did just what we told him not to do. እልኸኛው ፡ ልጅ ፡ ል ክ ፡ እንዳያደርግ ፡ የነገርነውን ፡ ነገር ፡ አደረገ
2. የሰው ፡ ምክር ፡ የማይቀበል ፤ ድርቅ ፡ ብዬ. The perverse man continued to smoke, against his doctor's orders. የሰው ፡ ምክር ፡ የማይቀበ ለው ፡ (ድርቅ ፡ ብዬ) ፡ ሰው ፡ የሐኪሙን ፡ ት እዛዝ ፡ ጥሶ ፡ ሲጋራ ፡ ማጤሱን ፡ ቀጠለ
3. ብልሹ. He has a perverse mind which delights in causing trouble. ብልሹ ፡ አእም ሮ ፡ ስላለው ፡ ችግር ፡ ማምጣት ፡ ያስደስተዋል
4. የተሳሳተ. His perverse reasoning leads him to believe that riots are beneficial. የተሳሳተ ፡ አ ስተሳሰቡ ፡ ሁከት ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ እ ምነት ፡ አሳድሮበታል

**perverse act** ኀጢአት

Cruelty to animals is a perverse act. በእን ስሳት ፡ መጨከን ፡ ኀጢአት ፡ ነው

**perversion** ማዛባት

Perversion of the facts is harmful to true understanding. እውነተኛውን ፡ ነገር ፡ ማዛባት ፡ በደንብ ፡ ለመግባባት ፡ ዕንቅፋት ፡ ይሆናል

**pervert** (v.)

1. አዞረ. His enemies perverted his friendly remark and made it into an insult. ጠላቶቹ ፡ እሱ ፡ የሰጠውን ፡ የወዳጅነት ፡ አስተያየት ፡ አዞረ ው ፡ ስድብ ፡ አስመሰሉት
2. አበላሸ. He perverted the minds of the young people. የወጣቶቹን ፡ አእምሮ ፡ አበላሸ
Reading silly stories perverts our taste for good books. የማይረባ ፡ ታሪኮችን ፡ ማንበብ ፡ ጥ ሩ ፡ መጽሐፍ ፡ ለማንበብ ፡ ያለንን ፡ ስሜት ፡ ያ በላሽብናል

**pessimism**

*An air of pessimism prevails regarding the efforts to end the war. ጦርነቱን ፡ ለማቆም ፡ የሚደረገው ፡ ጥረት ፡ ውጤት ፡ አያምርም ፡ የሚ ል ፡ እምነት ፡ አለ

**pessimist** ክፉ ፡ አሳቢ

The pessimist always looks at the dark side of things. ክፉ ፡ አሳቢ ፡ ሁልጊዜ ፡ የሚደረጉት ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ መጥፎ ፡ መስለው ፡ ይታዩታል

**(be) pessimistic about** ጥሩ ፡ መስሎ ፡ አይታየ ውም

I am pessimistic about his chances of passing the examination. ፈተናውን ፡ ለማለፍ ፡ ያለው ፡ ዕ ድል ፡ ጥሩ ፡ መስሎ ፡ አይታየኝም

**pest**

1. ወረርሽኝ ፡ በሽታ. The pest known as the Black Death depopulated Europe in the Middle Ages. በመሀከለኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ጥቁር ፡ ሞት ፡ የተባለው ፡ ወረርሽኝ ፡ በሽታ ፡ የ አውሮፓን ፡ ሕዝብ ፡ ብዛት ፡ ቀነሰው
2. መርዘኛ ፡ ነፍሳት. Mosquitoes are pests. የወባ ፡ ትንኞች ፡ መርዘኛ ፡ ነፍሳት ፡ ናቸው
3. መኸርገር. He is a pest; he always wants some favor to be given him. መኸርገር ፡ ነው ፤ ዘወት ር ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ እንድታደርግለት ፡ ይፈልጋል

**insect pest** ተባይ

We must destroy insect pests or we'll lose our crops. ተባዮችን ፡ ማጥፋት ፡ አለብን ፤ አለበለዚ ያ ፡ ሰብላችን ፡ ይበላሻል

**pester** ጨቀጨቀ

Don't pester me to go with you to the store! ወደ ፡ ሱቅ ፡ አብረኸኝ ፡ ካልሄድክ ፡ ብለሽ ፡ አት ጨቅጭቂኝ

**pestilence** ቸነፈር

A pestilence has broken out in the South. በደቡብ ፡ ቸነፈር ፡ ተነሥቷል

**pestilent**

1. መርዘኛ. A pestilent disease like typhus will cause many deaths. ተስቦን ፡ የመሰለ ፡ መርዘኛ ፡ በሽታ ፡ ሰው ፡ ይጨርሳል
2. አስከፊ. The pestilent barking of the dog keeps me awake. የውሻው ፡ አስከፊ ፡ ጩኸት ፡ እንቅልፍ ፡ አላስወሰደ ፡ አለኝ

**pestle** ዘነዘና

The pestle is used in grinding coffee. ዘነዘና ፡ ቡና ፡ ለመውቀጫ ፡ ያገለግላል

**pet** (petted)

1. ደባበሰ. She petted the child to make it stop crying. ሕፃኑ ፡ ማልቀሱን ፡ እንዲያቆም ፡ ደባበሰችው
2. አንከባከበ. A mother often pets her sick child. እናት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የታመመ ፡ ልጇ ን ፡ ታንከባክባለች

**pet** (n.)

1. ለማዳ ፡ እንስሳ. We are not allowed to keep pets in our apartment. አፓርተማችን ፡ ውስጥ ፡ ለማዳ ፡ እንስሳ ፡ እንድናኖር ፡ አይፈቀድልንም
2. ብርቅዬ. She is her mother's pet. ለናቷ ፡ ብርቅ ዬ ፡ ናት

**pet** (adj.) ከሁሉ ፡ አብልጦ ፡ የሚያስበው
Building a school for the blind is his pet project. ለዕውራን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ማቋቋም ፡ ከሁሉ ፡ አብልጦ ፡ የሚያስበው ፡ ነገር ፡ ነው

**petal** (ያበባ) ፡ ቅጠል
This flower has waxy petals. ይህ ፡ አበባ ፡ ሰም ፡ መሳይ ፡ ነገር ፡ ያለበት ፡ ቅጠል ፡ አለው

**petition** (v.) አቤቱታ ፡ አቀረበ
We petitioned the mayor for a new school. አዲስ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ እንዲሠራ ፡ ለከንቲባው ፡ አቤቱታ ፡ አቀረብን

**petition** (n.)
1. አቤቱታ. He sent a petition to the mayor asking for a new traffic light. አዲስ ፡ የትራፊክ ፡ መብራት ፡ እንዲገባ ፡ ለከንቲባው ፡ አቤቱታ ፡ አቀረበ
2. ማመልከቻ. He forged my signature to his petition. ማመልከቻው ፡ ላይ ፡ የኔን ፡ ፊርማ ፡ አስመስሎ ፡ ፈረመ

**petrify** (petrified)
1. እንደ ፡ ድንጋይ ፡ አደረገ. Heat and the passage of time petrifies wood. ሙቀትና ፡ የጊዜ ፡ ብዛት ፡ ዕንጨቱን ፡ እንደ ፡ ድንጋይ ፡ ያደርጋል
2. በድን ፡ አደረገ. The sight of the fire petrified him. ቃጠሎውን ፡ ማየት ፡ በድን ፡ አደረገው

**be petrified** እንደ ፡ ድንጋይ ፡ ጠጠረ
The wood became petrified after being many years in the ground. ዕንጨቱ ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ መሬት ፡ ውስጥ ፡ ወድቆ ፡ ስለቆየ ፡ እንደ ፡ ድንጋይ ፡ ጠጠረ

**be petrified with fear** በድን ፡ ሆነ
He was petrified with fear when he saw the lion. አንበሳውን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ በድን ፡ ሆነ

**petrol** ቤንዚን
Fill my gas tank with petrol! የነዳጅ ፡ ጋኔን ፡ በቤንዚን ፡ ሙላው

**petroleum** ዘይት
Does Ethiopia import all its petroleum? ኢትዮጵያ ፡ ዘይቷን ፡ በሙሉ ፡ የምታስመጣው ፡ ከውጭ ፡ ነው ?

**petty**
1. ዝቅተኛ. My uncle is a petty official in the Ministry of Education. አጐቴ ፡ በትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ ውስጥ ፡ ዝቅተኛ ፡ ባለሥልጣን ፡ ነው
2. የማይረባ ፡ ጥቃቅን. They argued over petty details. በማይረባ ፡ ጥቃቅን ፡ ዝርዝሮች ፡ ላይ ፡ ተከራከሩ

**petty cash** ለጥቃቅን ፡ ወጪ ፡ የተመደበ ፡ ገንዘብ
The thief stole the petty cash that was in the drawer. ሌባው ፡ መሳቢያ ፡ ውስጥ ፡ የነበረውን ፡ ለጥቃቅን ፡ ወጪ ፡ የተመደበውን ፡ ገንዘብ ፡ሰረቀው

**petulant**
*The child's petulant behavior is due to his parents' refusal to buy him candy. ልጁ ፡ የሚነጫነጨው ፡ ወላጆቹ ፡ ከረሜላ ፡ አንገዛልህም ፡ ስላሉት ፡ ነው

**pew** [የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አግዳሚ ፡ መቀመጫ]

**phantom** ጣረ ፡ ሞት ፡ የሚመስል ፡ ነገር
He thought he saw a phantom in the graveyard. በመካነ ፡ መቃብሩ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ጣረ ፡ ሞት ፡ የሚመስል ፡ ነገር ፡ ያየ ፡ መሰለው

**pharmacist** መድኃኒት ፡ ቀማሚ
The pharmacist compounds medicine. መድኃኒት ፡ ቀማሚው ፡ መድኃኒት ፡ ይቀምማል

**pharmacy** (pharmacies) መድኃኒት ፡ ቤት
The pharmacy that remains open this evening is near our house. የዛሬ ፡ መድኃኒት ፡ ቤት ፡ ተረኛ ፡ በቤታችን ፡ አጠገብ ፡ ነው

**phase** (v.), ~ **out** ቀስ ፡ በቀስ ፡ አስቀረ
The factory has plans to phase out the obsolescent machinery. ፋብሪካው ፡ ጊዜ ፡ ያለፈባቸውን ፡ መሣሪያዎች ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ለማስቀረት ፡ ያስባል

**phase** (n.)
1. ምዕራፍ. This is a critical phase in world history. ይህ ፡ በዓለም ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ የሚያሳስብ ፡ ምዕራፍ ፡ ነው
2. የእድገት ፡ ደረጃ. Adolescence is a phase we all go through. ጕርምስና ፡ ሁላችንም ፡ የምናልፍበት ፡ የእድገት ፡ ደረጃ ፡ ነው
3. ክፍል. What phase of arithmetic are you studying now? አሁን ፡ የምታጠናው ፡ የሒሳብ ፡ ክፍል ፡ የትኛው ፡ ነው ?
*The admiral wrote about the naval phase of the invasion. አድሚራሉ ፡ የባሕሩን ፡ ጦርነት ፡ ስለሚመለከተው ፡ ወረራ ፡ ጻፈ
*In the final phase of his illness, his skin became entirely yellow. ሕመሙ ፡ ሊለቀው ፡ ሲል ፡ ቆዳው ፡ ፍጹም ፡ ቢጫ ፡ ሆነ

**pheasant** ጣዎስ

**phenomenon** (phenomena)
1. ምልክት. Fever and inflammation are phenomena of diseases. ትኩሳትና ፡ የሰውነት ፡ ማጉረብረብ ፡ የበሽታ ፡ ምልክቶች ፡ ናቸው

2. ያልተለመደ ፡ ሁኔታ. The moon turned red last night. No one can explain this phenomenon. ትላንትና ፡ ማታ ፡ ጨረቃ ፡ ደም ፡ መሰለች ፤ ይህንን ፡ ያልተለመደ ፡ ሁኔታ ፡ ማንም ፡ ሊገልጸው ፡ አይችልም
3. ሁኔታ. We studied gravitation and relative phenomena. ስለ ፡ ስበትና ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ሁኔታዎች ፡ አጠናን
*Lightning is an electrical phenomenon. መብረቅ ፡ ከኤሌክትሪክ ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ነው

**philanthropic** የችሮታ
His philanthropic bequests have created museums and libraries. በሱ ፡ የችሮታ ፡ ኑዛዜዎች ፡ ቤተ ፡ መዘክሮችና ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍቶች ፡ ተሠርተዋል

**philanthropy** (philanthropies)
1. ችሮታ. A home for orphans was one of his philanthropies. እናት ፡ አባት ፡ ለሌላቸው ፡ ልጆች ፡ ቤት ፡ መስጠቱ ፡ ከችሮታው ፡ አንዱ ፡ ነው
2. የበጎ ፡ አድራጊዎች ፡ እርዳታ. The Red Cross appeals to philanthropy. ቀይ ፡ መስቀል ፡ የበጎ ፡ አድራጊዎችን ፡ እርዳታ ፡ ይለምናል

**philosopher** ፈላስፋ
There were many philosophers in ancient Greece. በጥንታዊት ፡ ግሪክ ፡ ብዙ ፡ ፈላስፋዎች ፡ ነበሩ

**philosophy** (philosophies) ፍልስፍና
We study philosophy in college. ኮሌጅ ፡ ውስጥ ፡ ፍልስፍና ፡ እናጠናለን

**philter** መድኃኒት
The witch gave the man a philter which turned him into a frog. አስማተኛዋ ፡ ወደ ፡ እንቁራሪትነት ፡ የሚለውጥ ፡ አስማት ፡ ለሰውዬው ፡ ሰጠችው

**love philter** መስተፋቅር
He went to a medicine man to have a love philter made for him. መስተፋቅር ፡ እንዲያደርግለት ፡ ወደ ፡ ደብተራ ፡ ሄደ

**phlegm** አክታ
He has a lot of phlegm due to his cold. ከጉንፋኑ ፡ የተነሣ ፡ ብዙ ፡ አክታ ፡ አለው

**phlegmatic** ግድየለሽ
The phlegmatic fellow showed no concern about the coming hurricane. ግድየለሹ ፡ ሰው ፡ ስለሚመጣው ፡ ዓውሎ ፡ ነፋስ ፡ ምንም ፡ አልተጨነቀም

**phone** (v.) ስልክ ፡ ደወለ
Did anyone phone? ስልክ ፡ የደወለ ፡ ሰው ፡ ነበር ?

**be on the phone** ስልክ ፡ ያዘ
Just a moment; I am on the phone. አንዴ ፡ ቆይ ፤ ስልክ ፡ ይዤያለሁ

**phone** (n.) ስልክ
The phone is ringing. ስልኩ ፡ ይደውላል

**phonetic** የድምፅ
The marks used in a dictionary to show pronunciation are called phonetic symbols. በመዝገበ ፡ ቃላት ፡ ውስጥ ፡ የቃላትን ፡ አነባበብ ፡ ለማመልከት ፡ የምንጠቀምባቸው ፡ የድምፅ ፡ ምልክቶች ፡ ይባላሉ

**phonetics** የድምፅ ፡ ልሳን ፡ ጥናት
Phonetics teaches how the sounds are pronounced. የድምፅ ፡ ልሳን ፡ ጥናት ፡ የንግግር ፡ ድምፆችን ፡ አጠራር ፡ ያስተምረናል

**phonograph** ሸክላ ፡ ማጫወቻ
The phonograph is playing too loudly. ሸክላ ፡ ማጫወቻው ፡ ከለመጠን ፡ ይጮኻል

**phony** የውሸት
He is a sucker for phony oil stocks. ተላላ ፡ ስለሆነ ፡ የውሸት ፡ የዘይት ፡ አክሲዮኖች ፡ ያግበሰብሳል

**photo** ፎቶግራፍ
This is my sister's photo. ይህ ፡ የእኅቴ ፡ ፎቶግራፍ ፡ ነው

**photograph** (v.) ፎቶግራፍ ፡ አነሣ
They photographed the coronation. የዘውድ ፡ በዓሉን ፡ ሥርዓት ፡ ፎቶግራፍ ፡ አነሡ

**photographer** ፎቶግራፍ ፡ አንሺ
The photographer photographed the ceremony. ፎቶግራፍ ፡ አንሺው ፡ በዓሉን ፡ ፎቶግራፍ ፡ አነሣ

**phrase** (v.) ገለጸ
He phrased his excuse in polite words. ምክንያቱን ፡ በትሕትና ፡ ገለጸ

**phrase** (n.) ሐረግ
How do you translate the phrase "to be or not to be" into Amharic? « ቱ ፡ ቢ ፡ ኦር ፡ ኖት ፡ ቱ ፡ ቢ » ፡ የሚለውን ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ሐረግ ፡ እንዴት ፡ አድርገህ ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ ትተረጉመዋለህ ?

**phraseology** አነጋገር
Legal phraseology is hard to understand. የሕግን ፡ አነጋገር ፡ መረዳት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**physical**
1. ግዙፍ. Physical entities are perceived by the five senses, the spiritual ones are not. ግዙፍ ፡ አካሎችን ፡ ባምስቱ ፡ ሕዋሳት ፡ ለማወቅ ፡ ስንችል ፡ ረቂቁን ፡ ግን ፡ አንችልም
2. ግዘፍ. The change from water to ice is a physical change. የውኃ ፡ ወደ ፡ በረዶነት ፡ መለወጥ ፡ ግዘፍ ፡ ለውጥ ፡ ነው
3. አካላዊ. He has to give up all physical activity for a while. ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ማንኛውንም ፡ አካላዊ ፡ እንቅስቃሴ ፡ መተው ፡ አለበት
4. የሰውነት. His illness is mental, not physical. በሽታው ፡ የአእምሮ ፡ እንጂ ፡ የሰውነት ፡ አይደለም
5. የተፈጥሮ. The physical laws determine the structure of a building. የተፈጥሮ ፡ ሕጎች ፡ የንድን ፡ ሕንጻ ፡ አሠራር ፡ ይወስናሉ
[See also 'exercise']

**physically** ባካል
It is physically impossible to be in two places at once. ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ሁለት ፡ ቦታ ፡ ባካል ፡ ለመገኘት ፡ አይቻልም

**physician** ሐኪም
The physician prescribes a medicine to the patient. ሐኪም ፡ ለበሽተኛ ፡ መድኃኒት ፡ ያዛል

**physics** ፊዚክስ
He is taking a course in physics. ፊዚክስ ፡ ይማራል

**physiology** የሰው ፡ አካል ፡ ጥናት

**piano** ፒያኖ

**pick** (v.)
1. ቀጠፈ. I will pick some roses for the table. ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ለማኖር ፡ ጥቂት ፡ ጽጌረዳዎች ፡ እቀጥፋለሁ
2. ለቀመ (ተለቀመ). The farmer picked coffee from the tree. ገበሬው ፡ ከዛፉ ፡ ላይ ፡ ቡና ፡ ለቀመ
Is the fruit ripe enough to pick? ፍሬው ፡ ለመለቀም ፡ ደርሷል ?
3. ገፈፈ. She picked the meat from the bones. ሥጋውን ፡ ከጥንቱ ፡ ላይ ፡ ገፈፈች
4. ያዘ. Pick an odd number! ጐዶሎ ፡ ቁጥር ፡ ያዝ
5. መረጠ. The judges picked the winner. ዳኞቹ ፡ አሸናፊውን ፡ መረጡ
6. ጐረጐረ. The boy picks his teeth with a toothpick. ልጁ ፡ በስንጥር ፡ ጥርሱን ፡ ይጐረጉራል

**pick about** ለቃቀመ
The hens were busily picking about in their coop. ዶሮዎቹ ፡ በዶሮ ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ይለቃቅማሉ

**pick at** ቀመስ ፡ አድርጎ ፡ ተወ
She only picked at her food. ምግቡን ፡ ቀመስ ፡ አድርጋ ፡ ተወችው

**pick (off)** ላጠ
Don't pick the scab off your wound! የቁስልህን ፡ ቅርፊት ፡ አትላጠው

**pick on**
1. ተነኰሰ. Don't always pick on the child! ሕፃኑን ፡ ሁልጊዜ ፡ አትተንኵሰው
2. መረጠ. The teacher always picks on me to translate long passages. ረዥም ፡ ምንባቦችን ፡ ለመተርጐም ፡ መምህሩ ፡ ዘወትር ፡ እኔን ፡ ይመርጠኛል

**pick out**
1. መረጠ. He picked out a very nice gift for his wife. ለሚስቱ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ የሆነ ፡ ስጦታ ፡ መረጠ
2. ለየ. Can you pick me out in this picture? እዚህ ፡ ፎቶግራፍ ፡ ውስጥ ፡ ልትለየኝ ፡ ትችላለህ ?

**pick (one's) pocket** ከኪሱ ፡ ሰረቀው ፤ ኪስ ፡ ገባ
Someone picked my pocket. አንድ ፡ ሰው ፡ ከኪሴ ፡ ሰረቀኝ
A thief picked my pocket. ሌባ ፡ ኪሴ ፡ ገባ

**pick up** (vt.)
1. ለቃቀመ ፤ ቃረመ. He is out picking up bits of information. ከዚያም ፡ ከዚህም ፡ ወሬ ፡ ለመለቃቀም ፡ (ለመቃረም) ፡ ወጥቷል
2. አሳፈረ. The bus stops here to pick up passengers. መንገደኞችን ፡ ለማሳፈር ፡ አውቶቡሱ ፡ እዚህ ፡ ይቆማል
3. ወሰደ. He picks up his letters from the post office box. ደብዳቤዎቹን ፡ ከፖስታው ፡ ሣጥን ፡ ይወስዳል
4. አነሣ. Pick up the paper from the floor! ወረቀቱን ፡ ከወለሉ ፡ ላይ ፡ አንሣው
5. ያዘ. The police picked up several suspects. ፖሊስ ፡ ብዙ ፡ ተጠርጣሪዎችን ፡ ያዘ
6. አገኘ. The woman picked up a bargain at the dress sale. በልብስ ፡ መሸጫው ፡ መደብር ፡ ሴትዮዋ ፡ ጥሩ ፡ ግዢ ፡ አገኘች
7. ቃረመ ፤ ተማረ. I picked up a lot of Italian on my trip. በጉዞዬ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ጣሊያንኛ ፡ ቃረምኩ ፡ (ተማርኩ)

**pick up** (vi.)
1. ሞቀ. Business picks up after the rainy

season is over. ከረምቱ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ንግድ ፡ ይሞቃል
2. ጀምር ፡ ቀጠለ. Tom picked up where he stopped the day before. ቶም ፡ ባለፈው ፡ ቀን ፡ ካቆመበት ፡ ጀምሮ ፡ ቀጠለ
3. ፍጥነት ፡ ጨመረ. The car picked up once it was on the open road. ግልጽ ፡ መንገድ ፡ ስታገኝ ፡ መኪናዋ ፡ ፍጥነቷን ፡ ጨመረች

**pick (oneself) up** ብድግ ፡ አለ
She slipped and fell, but quickly picked herself up. አድጧት ፡ ወድቃ ፡ ወዲያውኑ ፡ ብድግ ፡ አለች
[See also 'bone, hole, quarrel, tab']

**pick** (n.)
1. ዶማ. The men were carrying picks and shovels. ሰዎች ፡ ዶማ ፡ አካፋ ፡ ተሸክመው ፡ ነበር
2. ምርጫ. He is our pick for president. ለፕሬዚዳንትነት ፡ ምርጫችን ፡ እሱ ፡ ነው
3. አዝመራ. The pick is poor this season. በዚህ ፡ ወቅት ፡ አዝመራው ፡ መጥፎ ፡ ነው

**take one's pick** የሚመርጠውን ፡ ወሰደ
Take your pick of these books! ከነዚህ ፡ መጻሕፍት ፡ የምትመርጠውን ፡ ውሰድ

**the pick of** ምርጥ ፡ የሆኑት
We got a high price for the pick of the roses. ምርጥ ፡ ለሆኑት ፡ ጽጌረዳዎች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ አገኘን

**pickaxe** ዶማ
A pickaxe is used to break hard ground. ዶማ ፡ ጠንካራ ፡ መሬትን ፡ ለመቈፈር ፡ ያገለግላል

**picket** (v.) ሰላማዊ ፡ ሰልፍ ፡ አደረገ
The employees picketed the store for better wages. ሠራተኞቹ ፡ ደሞዝ ፡ እንዲጨመርላቸው ፡ ከመደብሩ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ሰላማዊ ፡ ሰልፍ ፡ አደረጉ

**picket** (n.), **wooden** ~ የሾላ ፡ አጠና
The fence is made of wooden pickets. አጥሩ ፡ የተሠራው ፡ ከሾላ ፡ አጠና ፡ ነው

**pickle** [በኮምጣጤና ፡ በጨው ፡ የተዘፈዘፈ ፡ ዱባ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ዓይነት ፡ ፍሬ]

**pickpocket** ኪስ ፡ አውላቂ
The pickpocket was caught and beaten. ኪስ ፡ አውላቂው ፡ ተይዞ ፡ ተደበደበ

**pickup**
*The mailman makes three pickups a day. ፖስተኛው ፡ በቀን ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ደብዳቤ ፡ ይሰበስባል
*There was a pickup in retail sales last month. ባለፈው ፡ ወር ፡ የችርቻሮ ፡ ሽያጭ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ነበር

**have a good pickup** የፍጥነት ፡ ኀይል ፡ አለው
Our old car still has a good pickup. አሮጌዋ ፡ መኪናችን ፡ አሁንም ፡ የፍጥነት ፡ ኀይል ፡ አላት

**picnic** (picnicked)
*Our family often picnics at the beach. ቤተ ፡ ሰባችን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ዳርቻ ፡ ለሽርሽር ፡ ሄደው ፡ እዚያው ፡ በልተው ፡ ይውላሉ

**picnic** (n.) ሽርሽር
Let's go on a picnic! ሽርሽር ፡ እንሂድ

**pictorial** ሥዕላዊ
A pictorial magazine will be published for the tourists. ላገር ፡ ጐብኚዎች ፡ ሥዕላዊ ፡ መጽሔት ፡ ይታተማል
A photograph album is a pictorial record of the family. የፎቶግራፍ ፡ ማጠራቀሚያ ፡ የቤተሰቡ ፡ ሥዕላዊ ፡ መዝገብ ፡ ነው

**picture** (v.)
1. ገለጸ. This novel pictures life a thousand years ago. ይህ ፡ የልብ ፡ ወለድ ፡ ታሪክ ፡ ከሺ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ የነበረውን ፡ ኑሮ ፡ ይገልጻል
2. ሣለ. The artist pictured the saints. ሠዓሊው ፡ ቅዱሳኑን ፡ ሣለ
3. አሳየ. The scenery pictures a garden in the moonlight. የቲያትሩ ፡ ትርእይት ፡ ጨረቃ ፡ የፈነጠቀችበት ፡ ያትክልት ፡ ቦታ ፡ ያሳያል
4. አስተያየት ፡ ሰጠ. He pictured the situation in America differently. የአሜሪካንን ፡ ሁኔታ ፡ ልዩ ፡ አስተያየት ፡ ሰጠው
5. አሰበ. It is hard to picture life a hundred years ago. ከመቶ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ የነበረውን ፡ የኑሮ ፡ ሁኔታ ፡ ማሰብ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው

**be pictured** ተነበበ
Joy is pictured in his face. ደስታ ፡ በፊቱ ፡ ላይ ፡ ይነበባል

**picture oneself** ራሱን ፡ ቈጠረ
He likes to picture himself as an explorer. ራሱን ፡ እንደ ፡ አሳሽ ፡ መቍጠር ፡ ይወዳል

**picture someone as** መሰለ(ው)
+I can't picture you as a politician. የፖለቲካ ፡ ሰው ፡ አትመስለኝም

**picture** (n.)
1. ሥዕል. They have some beautiful pictures for sale. የሚሸጡ ፡ አንዳንድ ፡ ጥሩ ፡ ሥዕሎች ፡ አሉዋቸው

2. መግለጫ. He gave me a false picture of the situation in the country. ስለ ፡ አገሪቱ ፡ ሁኔታ ፡ ትክክል ፡ ያልሆነ ፡ መግለጫ ፡ ሰጠኝ
3. ትርእይት. The trees and the brook make a lovely picture. ዛፎቹና ፡ ምንጩ ፡ አስደሳች ፡ ትርእይት ፡ ናቸው
4. ፊልም. Yesterday we saw a picture with Greta Garbo. ግሬታ ፡ ጋርቦ ፡ ያለችበትን ፡ ፊልም ፡ ትላንትና ፡ አየን
5. ፎቶግራፍ. That is a picture of my fiancée. ያ ፡ የእጮኛዬ ፡ ፎቶግራፍ ፡ ነው
*She's the picture of health. ጤነኛ ፡ ሰው ፡ ማለት ፡ እሷ ፡ ናት
*She is the pict.ıre of her mother. ቁርጥ ፡ እናቷን ፡ ናት

**have a picture of** ታየ(ው)
I have a clear picture of how he looked that day. ያን ፡ ቀን ፡ ምን ፡ ይመስል ፡ እንደነበረ ፡ በግልጽ ፡ ይታየኛል

**take a picture** ፎቶግራፍ ፡ አነሣ
Take a picture of me and send it to your friends! ፎቶግራፍ ፡ አንሣኝና ፡ ለጓደኞችህ ፡ ላክላቸው

**picture** (adj.) ሥዕላዊ
There is little reading in this picture magazine. በዚህ ፡ ሥዕላዊ ፡ መጽሔት ፡ ውስጥ ፡ የሚነበብ ፡ ጥቂት ፡ ነው

**picturesque** ውብና ፡ ማራኪ
Gondar is a picturesque city. ጐንደር ፡ ውብና ፡ ማራኪ ፡ ከተማ ፡ ናት
*This is a picturesque description of life in the city. ይህ ፡ የከተማን ፡ ኑሮ ፡ በዓይነ ፡ ኅሊና ፡ እንደሚታይ ፡ አድርጎ ፡ ይገልጻል

**piece** (v.), ~ **together**
1. አጠናቀረ. They pieced together bits of information to discover the cause of the explosion. የፈንጅውን ፡ ምክንያት ፡ ለማግኘት ፡ የተገኙትን ፡ ጥቃቅን ፡ ማስረጃዎች ፡ አጠናቀሩ
2. ገጣጠመ. I pieced the broken jug together. የተሰበረውን ፡ ገንቦ ፡ ገጣጠምኩት

**piece** (n.)
1. ቁራሽ. May I have a piece of cake? ቁራሽ ፡ ኬክ ፡ ልትሰጠኝ ፡ ትችላለህ ?
2. ቁራጭ. Sew the two pieces together! ሁለቱን ፡ ቁራጮች ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ስፋቸው
May I have another piece of meat? ከሥጋው ፡ አንዲት ፡ ቁራጭ ፡ ትጨምርልኝ ?
3. ስብርባሪ. I swept up the pieces of glass. የብርጭቆውን ፡ ስብርባሪ ፡ ጠረግሁት
*This table is a fine piece of workmanship. ይህ ፡ ጠረጴዛ ፡ በልዩ ፡ ጥበብ ፡ የተሠራ ፡ ነው

**piece of information** ወሬ
He gave me a useful piece of information. አንዲት ፡ ጠቃሚ ፡ ወሬ ፡ ነገረኝ

**piece of land** ትንሽ ፡ መሬት
I bought a piece of land yesterday. ትናንት ፡ አንድ ፡ ትንሽ ፡ መሬት ፡ ገዛሁ

**break to pieces** እንክትክቱ ፡ ወጣ
The teapot fell and was broken to pieces. የሻዩ ፡ ጀበና ፡ ወድቆ ፡ እንክትክቱ ፡ ወጣ

**by the piece**
1. በሠራው ፡ መጠን. These workers are paid by the piece and not by the hour. እነዚህ ፡ ሠራተኞች ፡ በሠሩት ፡ መጠን ፡ እንጂ ፡ በሰዓት ፡ አይከፈሉም
2. እየቸረቸረ. He sells cloth by the piece. ጨርቅ ፡ የሚሸጠው ፡ እየቸረቸረ ፡ ነው

**fall to pieces**
1. ተገነጣጠለ. This book is falling to pieces. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ሊገነጣጠል ፡ ነው
2. ፈራረሰ. That old house is falling to pieces. ያ ፡ አሮጌ ፡ ቤት ፡ ሊፈራርስ ፡ ነው
3. ውልቅልቁ ፡ ወጣ. This car is so old, it's falling to pieces. ይህ ፡ መኪና ፡ በጣም ፡ ከማርጀቱ ፡ የተነሣ ፡ ውልቅልቁ ፡ ሊወጣ ፡ ነው

**give one a piece of his mind**
1. ክፉኛ ፡ ነቀፈው. He gave his employee a piece of his mind when he saw that he did not do his job well. ሥራውን ፡ በደንብ ፡ ባለመሥራቱ ፡ ባለቤቱ ፡ ሠራተኛውን ፡ ክፉኛ ፡ ነቀፈው
2. ቅር ፡ እንደተሰኘ ፡ ገለጸ(ለት). I will give him a piece of my mind for telling such a lie. ይህን ፡ መሳይ ፡ ውሸት ፡ ስለነገረኝ ፡ ቅር ፡ እንደተሰኘሁ ፡ እገልጽለታለሁ
[See also 'go, pull, rend']

**piecemeal** ጥቂት ፡ በጥቂት
He did the work piecemeal. ሥራውን ፡ ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ ሠራው

**pier** የወደብ ፡ መድረክ
He was standing on the pier waiting for the boat. የወደቡ ፡ መድረክ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ ጀልባውን ፡ ይጠብቅ ፡ ነበር

**pierce**
1. በሳ. The bullet pierced his skull. ጥይቱ ፡ ራስ ፡ ቅሉን ፡ በሳው
2. ጥሶ ፡ ገባ. Our forces have pierced the enemy lines. የኛ ፡ የጦር ፡ ኃይሎች ፡ የጠላትን ፡ ይዞታ ፡ ጥሰው ፡ ገቡ

3. ጥሶ ፡ ወጣ. The sun pierced the clouds. ፀሐይ ፡ ደመናውን ፡ ጥሳ ፡ ወጣች
4. ወጋ. The needle pierced her finger. መርፌው ፡ ጣቷን ፡ ወጋው
5. ዘልቆ ፡ ገባ. The cold wind pierced our clothes. ቀዝቃዛው ፡ ነፋስ ፡ ልብሳችንን ፡ ዘልቆ ፡ ገባ
6. ነካ. The loss of her kitten pierced the little girl's heart. የድመቷ ፡ መጥፋት ፡ የትንሿን ፡ ልጅ ፡ ልብ ፡ ነካው
7. ደረሰ(በት). She couldn't pierce his thoughts. ሐሳቡ ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ልትደርስበት ፡ አልቻለችም

**piercing**
1. በጣም ፡ ቀጭን. She has a piercing voice. በጣም ፡ ቀጭን ፡ ድምፅ ፡ አላት
2. ጆሮ ፡ የሚበጥስ. The child let out a piercing scream. ልጁ ፡ ጆሮ ፡ የሚበጥስ ፡ ጩኸት ፡ ለቀቀ
3. አጥንት ፡ የሚሰብር. A piercing wind chilled us to the bone. አጥንት ፡ የሚሰብር ፡ ነፋስ ፡ አኮራመተን

**piety**
1. ሃይማኖተኛነት. He is famous for his piety. በሃይማኖተኛነቱ ፡ የታወቀ ፡ ነው
2. ቅድስና. Because of his piety, people came from far to receive his blessing. ስለ ፡ ቅድስናው ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ቡራኬ ፡ ለማግኘት ፡ ከሩቅ ፡ መጡ

**act of piety** የተቀደሰ ፡ ተግባር
Manumission of slaves is an act of piety. ባሮችን ፡ አርነት ፡ ማውጣት ፡ የተቀደሰ ፡ ተግባር ፡ ነው

**pig** አሳማ
There are not many pigs in Ethiopia. በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ አሳማዎች ፡ የሉም

**pigeon** እርግብ
The pigeon alighted on a tree. እርግቧ ፡ በዛፍ ፡ ላይ ፡ አረፈች

**pigeonhole** (v.) በጉን ፡ አኑሮ ፡ ረሳው
British officials pigeonholed Emperor Theodore's letter to Queen Victoria. የእንግሊዝ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ከአፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ለንግሥት ፡ ቪክቶርያ ፡ የተላከውን ፡ ደብዳቤ ፡ በጉን ፡ አኑረው ፡ ረሱት

**pigeonhole,** n. [ደብዳቤዎችና ፡ ወረቀቶች ፡ የሚቀመጡባቸው ፡ እንደ ፡ ሣጥን ፡ ያሉ ፡ ትናንሽ ፡ የጠረጴዛ ፡ ክፍሎች]

**piggy** ግልገል ፡ አሳማ ፤ ትንሽ ፡ አሳማ

**piggyback, carry ~** አዘለ
The father carried the baby piggyback. አባትዬው ፡ ልጁን ፡ አዘለ

**pigheaded** ሐሳበ ፡ ግትር
Don't argue with him! He is pigheaded. ከሱ ፡ ጋር ፡ አትከራከር ፤ ሐሳበ ፡ ግትር ፡ ነው

**pigment** ማቅለሚያ
Pigment is added to oil to make paint. ቀለም ፡ ለመሥራት ፡ ማቅለሚያው ፡ ከዘይት ፡ ጋር ፡ ይቀላቀላል

**pike** ጦር
This pike was captured in a battle centuries ago. ይህ ፡ ጦር ፡ ከብዙ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ በጦርነት ፡ ላይ ፡ የተገኘ ፡ ምርኮ ፡ ነው

**pile** (vt.)
1. ቆለለ. He piled the books on the table. መጻሕፍቱን ፡ ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ቆለለ
2. ጫነ. The farmer piled the wagon with hay. ገበሬው ፡ ጋሪውን ፡ ድርቆሽ ፡ ጫነው

**pile** (vi.)
1. ተቆለለ. Snow piled against the fences. በረዶው ፡ አጥሩ ፡ ላይ ፡ ተቆለለ
2. ታጐረ. We piled into the bus. አውቶቡሱ ፡ ውስጥ ፡ ታጐርን

**pile in a heap** ከመረ
He piled the sand in a heap. አሸዋውን ፡ ከመረው

**pile up** (vt.) ከመረ
The gardener piled up the leaves. አትክልተኛው ፡ ቅጠሉን ፡ ከመረ

**pile up** (vi.) ተከመረ
My debts are piling up. ዕዳዬ ፡ እየተከመረ ፡ ሄደ

**pile** (n.)
1. ቁልል. The green book is on the bottom of the pile. አረንጓዴው ፡ መጽሐፍ ፡ ከመጽሐፉ ፡ ቁልል ፡ ሥር ፡ ነው
2. ክምር. What am I to do with that pile of books? ያን ፡ የመጽሐፍ ፡ ክምር ፡ ምን ፡ ላድርገው ?
3. የዕንጨት ፡ ምሰሶ. The building rests on wooden piles. ሕንጻው ፡ የቆመው ፡ ዕንጨት ፡ ምሰሶዎች ፡ ላይ ፡ ነው

**a pile of** ብዙ
I have a pile of work to do. ብዙ ፡ የምሠራው ፡ ሥራ ፡ አለኝ
*Here's a pile of letters to answer. መልስ ፡ የሚያስፈልጋቸው ፡ ደብዳቤዎች ፡ ተከምረዋል

**make a pile of stones** ድንጋይ ፡ ከበ
Make a pile of stones to show the boundary of your field! የመሬታችሁን ፡ ድንበር ፡ ለማሳየት ፡ ድንጋይ ፡ ከቡ

**pilfer** ሰረቀ
The thief pilfered coins. ሌባው ፡ ገንዘብ ፡ ሰረቀ

**pilgrim** ተሳላሚ
The pilgrims are going to Mecca by ship. ተሳላሚዎቹ ፡ ወደ ፡ መካ ፡ በመርከብ ፡ ይሄዳሉ

**pilgrimage** ወደ ፡ ቅዱሳን ፡ ስፈር ፡ ያደረገው ፡ ጉዞ ፤ መሳለም
His pilgrimage lasted four weeks. ወደ ፡ ቅዱሳን ፡ ስፍራዎች ፡ ያደረገው ፡ ጉዞ ፡ አራት ፡ ሳምንት ፡ ወሰደበት
He is going to the Holy Land on a pilgrimage. ቅድስት ፡ አገርን ፡ ለመሳለም ፡ ይሄዳል

**make a pilgrimage** ሊሳለም ፡ ሄደ
He made a pilgrimage to the Holy Land. ቅድስት ፡ አገርን ፡ ሊሳለም ፡ ሄደ

**pill** ኪኒን
He takes several different kinds of pills for his illness. ለበሽታው ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ኪኒን ፡ ይውጣል

**pillage** (v.) ዘረፈ
The bandits pillaged the village and fled. ሽፍቶቹ ፡ መንደሩን ፡ ዘርፈው ፡ ሸሹ

**pillage** (n.) የተዘረፈ ፡ ንብረት
A lot of pillage was recovered from the outlaws. ብዙ ፡ የተዘረፈ ፡ ንብረት ፡ በሽፍቶቹ ፡ እጅ ፡ ላይ ፡ ተያዘ

**pillar**
1. ዓምድ. A large pillar blocked my view of the stage. አንድ ፡ ትልቅ ፡ ዓምድ ፡ መድረኩን ፡ እንዳላይ ፡ ከለለኝ
2. ምሰሶ. These three men are the pillars of the community. እነዚህ ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ የኅብረ ፡ ሰቡ ፡ ምሰሶ ፡ ናቸው

**pillory** [ለእጅና ፡ ላንገት ፡ ማስገቢያ ፡ ያለው ፡ ከዕንጨት ፡ የተሠራ ፡ ወንጀለኛ ፡ ባደባባይ ፡ የሚቀጣበት ፡ ነገር]

**pillow**
1. ትራስ. I bought a pillow for three dollars. በሦስት ፡ ብር ፡ ትራስ ፡ ገዛሁ
2. መከዳ. Give me a pillow for a chair! ለወንበሩ ፡ የሚሆን ፡ መከዳ ፡ ስጠኝ

**sleep on a pillow** ትራስ ፡ ተንተራሰ
I like to sleep on two pillows. ሁለት ፡ ትራስ ፡ መንተራስ ፡ እወዳለሁ

**pillowcase** የትራስ ፡ ልብስ
The pillowcase is dirty. የትራስ ፡ ልብሱ ፡ ቆሽሿል

**pilot** (v.)
1. መራ. The captain piloted the ship through the storm. ካፒቴኑ ፡ መርከቧን ፡ በማዕበሉ ፡ ውስጥ ፡ መራ
2. ነዳ. The captain piloted the plane through the storm. ካፒቴኑ ፡ አውሮፕላኑን ፡ በዓውሎ ፡ ነፋሱ ፡ ውስጥ ፡ ነዳ

**pilot to a landing** አሳረፈ
He piloted the aircraft to a safe landing. አውሮፕላኑን ፡ ያላንዳች ፡ አደጋ ፡ አሳረፈው

**pilot** (n.)
1. የመርከብ ፡ ነጂ. The pilot brought the ship into harbor. የመርከቡ ፡ ነጂ ፡ መርከቧን ፡ ወደ ፡ ወደብ ፡ አስገባ
2. አውሮፕላን ፡ ነጂ. The pilot of the plane prevented a serious accident. አውሮፕላን ፡ ነጂው ፡ አውሮፕላኑን ፡ ከሚያሰጋ ፡ አደጋ ፡ አዳነው

**pilot** (adj.) የሙከራ
A small pilot study was done first. በመጀመሪያ ፡ አነስተኛ ፡ የሙከራ ፡ ጥናት ፡ ተደረገ

**pimple** ብጉር
His face is covered with pimples. ፊቱን ፡ ብጉር ፡ ጨርሶታል

**pin** (pinned), v.
1. ላከከ. They pinned the crime on him. ወንጀሉን ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ ላከኩ
2. አጣበቀ. When the tree fell, it pinned him to the ground. ዛፉ ፡ በወደቀ ፡ ጊዜ ፡ ከመሬት ፡ ጋር ፡ አጣበቀው
3. ሰካ. She pinned a flower on her dress. ቀሚሷ ፡ ላይ ፡ አበባ ፡ ሰካች

**be pinned** ተቀረቀረ
He was pinned under the wreckage of his car. ባደጋው ፡ ከተጨራመተው ፡ መኪና ፡ ሥር ፡ ተቀርቅሮ ፡ ነበር

**pin down**
1. እንዲወሰን ፡ አደረገ. We couldn't pin him down to a definite date. ቁርጥ ፡ ያለ ፡ ቀን ፡ እንዲወስን ፡ ለማድረግ ፡ አልቻልንም
2. ቃል ፡ አስገባ. He couldn't pin his boss down to a raise in pay. አለቃው ፡ የደሞዝ ፡ ጭማ

ሬ ፡ የሚያደርግለት ፡ ለመሆኑ ፡ ቃል ፡ ሊያስገ ባው ፡ አልቻለም

**pin on** በእስፒል ፡ አስያዘ
I'll pin the flower on for you. አበባውን ፡ በእስ ፒል ፡ እኔ ፡ አሲዝልሃለሁ

**pin** (n.)
1. እስፒል ፤ የወረቀት ፡ መርፌ. She stuck her finger with a pin. ጣቷን ፡ በስፒል ፡ (በወረ ቀት ፡ መርፌ) ፡ ወጋች
2. አርማ. She wore her class pin. የክፍሏን ፡ አ ርማ ፡ ሰክታለች

**pincers** ወረንጦ
I need a pair of pincers to remove this thorn. ይህንን ፡ እሾህ ፡ ለማውጣት ፡ ወረንጦ ፡ ያስፈ ልገኛል

**pinch** (vt.)
1. ቈነጠጠ. Her brother pinched her arm. ወንድሟ ፡ ክንዷን ፡ ቈነጠጣት
2. ያዘ. Her shoe pinches her toes. ጫማዋ ፡ ጣ ቷን ፡ ይዟታል
3. ቀረጠፈ. +He pinched his finger in the door. መዝጊያው ፡ ጣቱን ፡ ቀረጠፈው
4. አሠቃየ. Poverty pinched the family for many years. ድኽነት ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ ቤ ተሰቡን ፡ አሠቃይቶት ፡ ነበር

**pinch** (vi.)
1. ጥርሱን ፡ ነክሶ ፡ ገንዘብ ፡ ቈጠበ. He pinched for years to buy a car. መኪና ፡ ለመግዛት ፡ ለ ብዙ ፡ ዓመታት ፡ ጥርሱን ፡ ነክሶ ፡ ገንዘብ ፡ ቈጠበ
2. ያዘ. Where does the shoe pinch? ጫማው ፡ የ ሚይዘው ፡ የት ፡ ላይ ፡ ነው ?

**pinch pennies**
*They didn't pinch pennies on the new municipality building. ላዲሱ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ማሠ ሪያ ፡ ገንዘብ ፡ ሲያወጡ ፡ ወደኋላ ፡ አላሉም

**be pinched** ተቸገረ
The builders were pinched by the shortage of good lumber. በጥሩ ፡ ዕንጨት ፡ እጥረት ፡ ምክን ያት ፡ ገንቢዎቹ ፡ ተቸገሩ

**get pinched** (= active) ቀረጠፈ
+I got my finger pinched in the door. በሩ ፡ ጣ ቴን ፡ ቀረጠፈኝ

**pinch** (n.) ቁንጥጫ
The pinch really hurts. ቁንጥጫው ፡ በጣም ፡ ያ ማል
*Add a pinch of salt to the soup. ሾርባው ፡ ላ ይ ፡ ጨው ፡ ቈንጥረህ ፡ ጨምርበት

**do in a pinch** ለድንገተኛ ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ አይል
This string is not very strong, but it will do in a pinch. ይህ ፡ ሲባጎ ፡ በጣም ፡ ጠንካራ ፡ አ ይደለም ፤ ቢሆንም ፡ ለድንገተኛ ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ አይል

**pine** (v.) ጓጓ
She is pining to see him again. እንደገና ፡ ልታየ ው ፡ ጓጒታለች

**pine away** መነመነ
The prisoner pined away. እስረኛው ፡ መነመነ

**pine** (n.) የፈረንጅ ፡ ጥድ

**pinion , ~ one's arms** (v.) የፊጥኝ ፡ አሰረው
The thieves pinioned the man's arms. ሌቦቹ ፡ ሰውየውን ፡ የፊጥኝ ፡ አሰሩት

**pink** (v.) በጨረፍታ ፡ መታ
The bullet only pinked him. ጥይቱ ፡ የመታው ፡ በጨረፍታ ፡ ብቻ ፡ ነው

**pink** (adj.) ቀላ ፡ ያለ ፤ ሐምራዊ
She wears a pink blouse. ቀላ ፡ ያለ ፡ (ሐምራዊ) ፡ ብሉዝ ፡ ትለብሳለች

**pinnacle**
1. የተራራ ፡ ጫፍ. They reached the pinnacle after several days of climbing. ከብዙ ፡ ቀናት ፡ በኋላ ፡ ተራራው ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ደረሱ
2. ከፍተኛ ፡ ደረጃ. Still in his youth, he reached the pinnacle of his profession. ገና ፡ በወጣትነቱ ፡ በሥራው ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ደረሰ

**pinpoint** ለይቶ ፡ አመለከተ
The detectives pinpointed the criminals' hideout. ሰላዮቹ ፡ የወንጀለኞቹን ፡ ጐሬ ፡ ለይተው ፡ አ መለከቱ

**pint** [የፈሳሽ ፡ መለኪያ]

**pioneer** (v.) ቀዳሚነት ፡ ያዘ
Walter Reed pioneered in finding the cause of yellow fever. ዋልተር ፡ ሪድ ፡ የወባን ፡ መነሾ ፡ በ ማወቅ ፡ ረገድ ፡ ቀዳሚነትን ፡ ይዟል

**pioneer** (n.)
1. አቅኚ ፤ ሰፋሪ. The pioneers opened up the land to cultivation. አቅኚዎቹ ፡ (ሰፋሪዎቹ) ፡ መ ሬቱን ፡ ለእርሻ ፡ መነጠሩት
2. ቀዳሚነት ፡ የያዘ. Benjamin Franklin was a pioneer in the study of electricity. ቤንጃሚን ፡ ፍራንክሊን ፡ በኮሬንቲ ፡ ምርምራ ፡ ረገድ ፡ ቀ ዳሚነትን ፡ የያዘ ፡ ነው

**pious**
1. ሃይማኖተኛ. Pious people always observe the church fasts. ሃይማኖተኞች ፡ ሁልጊዜ ፡ አጽዋማትን ፡ ይጠብቃሉ
2. ጻድቅ. She is pious at church in the morning and gossips all afternoon. ጧት ፡ አቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጻድቅ ፡ ትመስላለች ፤ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ አሉባልተኛ ፡ ናት

**pipe** (v.) አሰማ
The little boy piped a tune in a high voice. ትንሹ ፡ ልጅ ፡ አንድ ፡ ዜማ ፡ በቀጭን ፡ ድምፅ ፡ አሰማ
**pipe in** በቧምቧ ፡ አመጣ
The municipality is piping water in from the hills. ማዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ ውኃ ፡ ከተራራው ፡ ላይ ፡ በቧምቧ ፡ ያመጣል

**pipe** (n.)
1. ዋሽንት. He plays the pipe well. ዋሽንት ፡ ጥሩ ፡ አድርጎ ፡ ይጫወታል
2. ፒፓ. He smokes a pipe. ፒፓ ፡ ያጨሳል
3. ቧምቧ. The pipe has burst. ቧምቧው ፡ ፈንድቷል

**piracy** የባሕር ፡ ላይ ፡ ዝርፊያ
Piracy was ended by the king's navy. የባሕር ፡ ላይ ፡ ዝርፊያ ፡ በንጉሡ ፡ የባሕር ፡ ኀይል ፡ ተደመሰሰ

**pirate** የባሕር ፡ ላይ ፡ ዘራፊ ፤ የባሕር ፡ ወንበዴ
There are no more pirates today. በዛሬው ፡ ጊዜ ፡ የባሕር ፡ ላይ ፡ ዘራፊች ፡ (የባሕር ፡ ወንበዴዎች) ፡ የሉም

**pistol** ሽጉጥ
He carried a pistol in his pocket. በኪሱ ፡ ሽጉጥ ፡ ይዞ ፡ ነበር

**pit**
1. ጉድጓድ. Joseph's brothers threw him in a pit. ዮሴፍን ፡ ወንድሞቹ ፡ ጉድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ጣሉት
2. ፍሬ. Here's a peach, but don't swallow the pit! ኮክ ፡ ይኸውልህ ፤ ፍሬውን ፡ ግን ፡ አትዋጠው
**in the pit of** ውስጥ
He felt a strange feeling in the pit of his stomach. ሆዱ ፡ ውስጥ ፡ ልዩ ፡ ስሜት ፡ ተሰማው

**pitch** (vt.)
1. ወረወረ. Pitch the ball to me! ኳሱን ፡ ወርውርልኝ
2. ተከለ. Where shall we pitch the tent? ድንኳኑን ፡ የት ፡ እንትከለው ?
*He pitched his hopes too high. ሁሉን ፡ ነገር ፡ አገኛለሁ ፡ የሚል ፡ ተስፋ ፡ አደረበት
**pitch** (vi.) ኮራ
The roof pitches sharply. ጣሪያው ፡ በጣም ፡ ኮርቷል
**pitch (down)** ተደፋ
The man lost his balance and pitched down the cliff. ሰውዬው ፡ ሚዛኑን ፡ ስለሳተ ፡ ከዳገቱ ፡ ላይ ፡ ተደፋ
**pitch forward** ተደፋ
The man pitched forward on his face. ሰውየው ፡ ባፍ ፡ ጢሙ ፡ ተደፋ
**pitch in**
1. ረዳ. Pitch in and help us finish the work on time! ሥራውን ፡ በጊዜ ፡ እንድንጨርስ ፡ እርዳን
2. በረታ. If I really pitch in, I may be able to finish my book by tomorrow. ከበረታሁ ፡ መጽሐፌን ፡ ነገ ፡ እጨርስ ፡ ይሆናል
3. አዋጣ. When they took up a collection for the dinner party, he promised to pitch in. ለእራት ፡ ግብዣው ፡ መዋጮ ፡ ሲሰበስቡ ፡ ለማዋጣት ፡ ቃል ፡ ገባ
**pitch into** ጠመደ
The hungry boy pitched into the food piled on the table. የተራበው ፡ ልጅ ፡ ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ የተቆለለውን ፡ ምግብ ፡ ጠመደው

**pitch** (n.)
1. ሙጫ. The farmers smear hides with pitch to make them waterproof. ገበሬዎች ፡ ቆዳው ፡ ውኃ ፡ እንዳይዘልቀው ፡ ሙጫ ፡ ይቀቡታል
2. ድምፅ. She sings in a high pitch. በቀጭን ፡ ድምፅ ፡ ታዜማለች
**be at high pitch** በጣም ፡ ከፍ ፡ አለ
Our excitement was at high pitch. ስሜታችን ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ነበር
**have a steep pitch** ዳገትነቱ ፡ ቀጥ ፡ አለ
Some roads in the mountains have a very steep pitch. በተራራው ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ አንዳንድ ፡ መንገዶች ፡ ዳገትነታቸው ፡ በጣም ፡ ቀጥ ፡ ያለ ፡ ነው

**pitch-black** በጣም ፡ ጨለማ
Since the road was pitch-black, he fell into a hole. መንገዱ ፡ በጣም ፡ ጨለማ ፡ ስለነበረ ፡ እጉድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ወደቀ

**pitch-dark** ጥቅጥቅ ፡ ያለ ፡ ጨለማ
It was pitch-dark when we came home. ወደ ፡ ቤት ፡ ስንመጣ ፡ ጥቅጥቅ ፡ ያለ ፡ ጨለማ ፡ ነበር

**pitcher**
1. ማንቆርቆሪያ. Please get me a pitcher of water! አንድ ፡ ማንቆርቆሪያ ፡ ውኃ ፡ አምጣልኝ
2. ኳስ ፡ አቀባይ. The pitcher hit him with the ball. ኳስ ፡ አቀባዩ ፡ ሰውየውን ፡ በኳስ ፡ መታው

**pitchfork** መንሽ
The pitchfork is one of the farmer's tools. መንሽ ፡ ከገበሬ ፡ መሣሪያዎች ፡ አንዱ ፡ ነው

**piteous** የሚያሳዝን
In the middle of the night, I heard piteous cries for help. እኩለ ፡ ሌሊት ፡ ላይ ፡ የሚያሳዝን ፡ የድረሱልኝ ፡ ጩኸት ፡ ድምፅ ፡ ሰማሁ
*Starving children are a piteous sight. የተራቡት ፡ ልጆች ፡ ለሚያያቸው ፡ ያሳዝናሉ

**piteously** በሚያሳዝን ፡ ሁኔታ
The sheep bleated piteously. በጎቹ ፡ በሚያሳዝን ፡ ሁኔታ ፡ ባ ፡ አሉ

**pitfall** ዕንቅፋት
A person will encounter many pitfalls before reaching the desired goal. አንድ ፡ ሰው ፡ ከፈለገው ፡ ግብ ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ ብዙ ፡ ዕንቅፋት ፡ ያጋጥመዋል

**pitiful**
1. አሳዛኝ. When they found the lost child, he was in a pitiful condition. የጠፋው ፡ ልጅ ፡ ሲገኝ ፡ በአሳዛኝ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ነበር
2. የማይረባ. He repaired my car in a pitiful way. መኪናዬን ፡ የጠገናት ፡ በማይረባ ፡ አኳኋን ፡ ነው

**(be) pitiless** ርኅራኄ ፡ የለውም
He is pitiless towards all lawbreakers. ሕግ ፡ ለሚያፈርሱ ፡ ሁሉ ፡ ርኅራኄ ፡ የለውም

**pity** (v.) አዘነ(ለት) ፤ ለ --- አዘነ
I pity you if you think you deserve to be helped. እርዳታ ፡ የሚያስፈልግህ ፡ መስሎ ፡ ከታየህ ፡ አዝንልሃለሁ
She pities any child who is hurt. ለተጐዳ ፡ ልጅ ፡ ሁሉ ፡ ታዝናለች
**be pitied** ታዘነ(ለት)
She doesn't want to be pitied. እንዲታዘንላት ፡ አትፈልግም

**pity** (n.) ሐዘኔታ ፤ ርኅራኄ
He gave the beggar a few coins out of pity. ከሐዘኔታ ፡ የተነሣ ፡ ለለማኙ ፡ ጥቂት ፡ ፍራንክ ፡ ሰጠው
Pity is often akin to love. ርኅራኄ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከመውደድ ፡ ጋር ፡ የተዛመደ ፡ ነው
**have pity on** አዘነ
He has pity on people less fortunate than himself. የሱን ፡ ያህል ፡ ላልታደሉ ፡ ሰዎች ፡ ያዝናል
**it's a pity** ያሳዝናል
It's a pity you can't come. ለመምጣት ፡ አለመቻልህ ፡ ያሳዝናል
**take pity on** አዘነ(ለት)
She took pity on him because he was so ill. በጣም ፡ ታሞ ፡ ስለነበር ፡ አዘነችለት
**what a pity** እንዴት ፡ ያሳዝናል
What a pity you could not go! ለመሄድ ፡ አለመቻልህ ፡ እንዴት ፡ ያሳዝናል

**pivot** (v.)
1. ተሽከረከረ. The earth pivots on its axis. መሬት ፡ በእንዝርቷ ፡ ላይ ፡ ትሽከረከራለች
2. ተመሠረተ. The arguments pivot on that point. ጉዳዩ ፡ እዚያ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ይመሠረታል
*John pivoted on his toe and faced me. ጆን ፡ ዞር ፡ ብሎ ፡ ፊቱን ፡ ወደኔ ፡ መለሰ

**pivot** (n.)
1. ማሽከርከሪያ. A swinging door turns on a pivot. ተወዛዋዥ ፡ መዝጊያ ፡ በማሽከርከሪያ ፡ ላይ ፡ ይዞራል
2. መሠረት. This point is the pivot of his argument. ይህ ፡ የክርክሩ ፡ መሠረት ፡ ነው

**placate** አባበለ
I tried to placate the angry woman with sweet words. የተናደደችውን ፡ ሴትዮ ፡ በለሰለሰ ፡ አንደበት ፡ ለማባበል ፡ ሞከርኩ

**place** (v.)
1. አኖረ ፤ አስቀመጠ. He placed the book on the table. መጽሐፉን ፡ ጠረጴዛ ፡ ላይ ፡ አኖረ ፡ (አስቀመጠ)
2. መደበ. The President placed him in the Ministry of Education. ፕሬዚዳንቱ ፡ በትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ ውስጥ ፡ መደበው
3. ቦታ ፡ አስያዘ. We have placed all of our graduates. ምሩቆቻችንን ፡ ሁሉ ፡ ቦታ ፡ አስይዘናል
4. ጣለ. The people placed confidence in their leader. ሕዝቡ ፡ እምነቱን ፡ በመሪው ፡ ላይ ፡ ጣለ
He placed the entire organization in my hands. ድርጅቱን ፡ በሙሉ ፡ እኔ ፡ ላይ ፡ ጣለ
5. ቦታው ፡ ትዝ ፡ አለ(ው). *I've met him before, but I can't place him. ከዚህ ፡ በፊት ፡ አግኝቼው ፡ ነበር ፤ ቦታው ፡ ግን ፡ ትዝ ፡ አይለኝም

6. ሆነ. He placed sixth in the race. በውድድሩ ፡ ስድስተኛ ፡ ሆነ

**be placed** ተደረገ
The table can be placed over there. ጠረጴዛው ፡ እዚያ ፡ ጋ ፡ ሊደረግ ፡ ይችላል
[See also 'ambush, command, credit, order']

**place** (n.)
1. ቦታ. Please put it back in the same place! ከነበረበት ፡ ቦታ ፡ መልሰው
Put yourself in my place! በኔ ፡ ቦታ ፡ ሆነህ ፡ እየው
Please take your places when the bell rings. ደወሉ ፡ ሲደውል ፡ በየቦታችሁ ፡ ተቀመጡ
2. ቤት. Please come and have dinner at my place! እቤቴ ፡ መጥተህ ፡ እራት ፡ ብላ
3. ተገቢ ፡ ቦታ. A café is not the place for an argument. ቡና ፡ ቤት ፡ ለክርክር ፡ ተገቢ ፡ ቦታ ፡ አይደለም
4. ሥራ. He lost his place at the bank. የባንክ ፡ ቤት ፡ ሥራውን ፡ ተነጠቀ
5. ሥልጣን. Who will take the place of the President when he dies? ፕሬዚዳንቱ ፡ ሲሞት ፡ ሥልጣኑን ፡ ማን ፡ ይይዛል ?
6. ተግባር. It is not my place to find fault. ስሕተት ፡ መልቀም ፡ የኔ ፡ ተግባር ፡ አይደለም
7. መኖሪያ. The Parkers have a beautiful place in the country. የሚስተር ፡ ፓርከር ፡ ቤተሰቦች ፡ ገጠር ፡ ውስጥ ፡ ጥሩ ፡ መኖሪያ ፡ አላቸው

**(be) in place**
1. ተገቢ ፡ ነው. Laughter is not in place in church. ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ መሣቅ ፡ ተገቢ ፡ አይደለም
2. ተዘጋጀ. Dinner is ready, and everything is in place. እራት ፡ ደርሷል ፤ እንዲሁም ፡ ማንኛቸውም ፡ ነገር ፡ ተዘጋጅቷል

**in (one's) place**
1. በሱ ፡ ምትክ. He couldn't go, so I went in his place. ሊሄድ ፡ ስላልቻለ ፡ በሱ ፡ ምትክ ፡ ሄድኩ
2. እሱን ፡ ቢሆን. I wouldn't have done it in his place. እሱን ፡ ብሆን ፡ አላደርገውም ፡ ነበር

**in place of** በ - - - ፈንታ
May I have another book in place of this one? በዚህ ፡ ፈንታ ፡ ሌላ ፡ መጽሐፍ ፡ ልወስድ ፡ እችላለሁ ?

**in the first place** አንደኛ ፡ ነገር
In the first place, we can't leave until tomorrow. አንደኛ ፡ ነገር ፡ እስከ ፡ ነገ ፡ ልንሄድ ፡ አንችልም

**know one's place** ደረጃውን ፡ ጠበቀ
They treated their servants well, but expected them always to know their place. አሽከሮቻቸውን ፡ በደንብ ፡ ይይዟቸዋል ፤ ሆኖም ፡ ደረጃቸውን ፡ እንዲጠብቁ ፡ ይፈልጉ ፡ ነበር

**(be) out of place**
1. አግባብ ፡ የለውም. Your remark is out of place. አስተያየትህ ፡ አግባብ ፡ የለውም
2. ተበታተነ. The chairs are out of place. ወንበሮቹ ፡ ተበታትነዋል

**put one in one's place** ልክ ፡ አገባ
Someone ought to put him in his place. አንድ ፡ ሰው ፡ ልክ ፡ ሊያገባው ፡ ያስፈልጋል

**take place**
1. ተደረገ. A great change has taken place in this country in the last twenty years. ባለፉት ፡ ሃያ ፡ ዓመታት ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ለውጥ ፡ ተደርጓል
2. ተፈጸመ ፤ ነው. The celebration took place yesterday. የበዓሉ ፡ አከባበር ፡ ትላንትና ፡ ተፈጸመ
When will the wedding take place? ሰርጉ ፡ መቼ ፡ ነው ?

**take the place of**
1. ተካ. Who will take the place of our boss when he is on vacation? አለቃችን ፡ ዕረፍት ፡ ሲሄድ ፡ ማን ፡ ይተካዋል ?
2. ዙፋኑን ፡ ወረሰ. The Crown Prince will take the place of the Emperor when he dies. ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሲያርፉ ፡ ዙፋኑን ፡ አልጋ ፡ ወራሹ ፡ ይወርሳሉ
[See also 'any, first, second, setting']

**placement** አቀማመጥ
The placement of the furniture in the room has to be changed. የዚህ ፡ ክፍል ፡ የቤት ፡ እቃ ፡ አቀማመጥ ፡ መለወጥ ፡ አለበት

**placement office** መቅጠሪያ ፡ ቢሮ
The school has a placement office for students. ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ የተማሪዎች ፡ መቅጠሪያ ፡ ቢሮ ፡ አለው

**placenta** የእንግዴ ፡ ልጅ
In the villages, the placenta is buried in a certain spot. በገጠር ፡ ውስጥ ፡ የእንግዴ ፡ ልጅ ፡ በተወሰነ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ይቀበራል

**placid** ጸጥ ፡ ያለ
The lake is placid this afternoon. ዛሬ ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ሐይቁ ፡ ጸጥ ፡ ያለ ፡ ነው

**have a placid expression** ረጋ
She has a placid expression, much like a cow's. እንደ ፡ ወተት ፡ የረጋች ፡ ናት

**plagiarize** የራሱ ፡ አስመስሎ ፡ ቀዳ
He deliberately plagiarized from earlier books.

ሆነ ፡ ብሎ ፡ ቀደም ፡ ሲል ፡ ከተጻፉት ፡ መጻሕፍት ፡ የ ራሱ ፡ አስመስሎ ፡ ቀዳ

**plague** (v.)
1. አስጨነቀ. The child plagued his uncle with questions. ልጁ ፡ አጐቱን ፡ በጥያቄ ፡ አስጨነቀው
2. ወረሰ. Severe unemployment plagued the nation. ኀይለኛ ፡ የሥራ ፡ መታጣት ፡ አገሪቱን ፡ ወርሷታል

**be plagued**
1. ተሠቃየ. As a child, he was plagued with illness. ልጅ ፡ ሆኖ ፡ በሕመም ፡ ይሠቃይ ፡ ነበር
2. ተወረረ. The neighboring countries of Sudan and Kenya are plagued by locusts. ጐረቤቶቻችን ፡ ኬንያና ፡ ሱዳን ፡ በአንበጣ ፡ ተወረዋል

**plague** (n.) ወረርሽኝ ፤ መዓት
A plague almost depopulated Europe in the Middle Ages. በመካከለኛው ፡ ዘመን ፡ ወረርሽኝ ፡ ያውሮፓን ፡ ሕዝብ ፡ ሊጨርሰው ፡ ምንም ፡ አልቀረውም ፡ ነበር
A plague of locusts devoured the crops. የአንበጣ ፡ መዓት ፡ እህሉን ፡ አወደመው

**plain** (n.) ሜዳ
Many people prefer the mountains to the plains. ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ከሜዳ ፡ ይልቅ ፡ ተራራ ፡ ይመርጣሉ

**plain** (adj.)
1. ተራ. We have a plain home in the country. በገጠር ፡ አንድ ፡ ተራ ፡ ቤት ፡ አለን
Poetic speech is harder to understand than plain speech. ከተራ ፡ ንግግር ፡ ይልቅ ፡ የረቀቀ ፡ ንግግር ፡ መረዳት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው
They are plain people. ተራ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው
The food was plain but substantial. መብሉ ፡ ተራ ፡ ቢሆንም ፡ ምግብነት ፡ ያለው ፡ ነበር
2. ግልጽ. It's quite plain that he is after her money. ገንዘቧን ፡ መፈለጉ ፡ ግልጽ ፡ ነው
3. ፍጹም. It is plain stupidity to try to cross the desert without water. ውኃ ፡ ሳይዙ ፡ በረኸን ፡ ለማቋረጥ ፡ መሞከር ፡ ፍጹም ፡ ጅልነት ፡ ነው
4. ጉልህ. The printed numbers are very plain. የታተሙት ፡ ቁጥሮች ፡ በጣም ፡ ጉልህ ፡ ናቸው
5. ፍርጥ ፡ ያለው. I told him the plain truth. ፍርጥ ፡ ያለውን ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ ነገርኩት
6. ልሙጥ. Embroidery costs more than plain cloth. ጥልፍ ፡ ከልሙጥ ፡ ጨርቅ ፡ ይወደዳል
7. ጌጥ ፡ የሌለበት. He bought a plain necktie for two dollars. ጌጥ ፡ የሌለበት ፡ ክራቫት ፡ በሁለት ፡ ብር ፡ ገዛ
8. የማያምር. Girls who were plain in their childhood become pretty as they grow up. በልጅነታቸው ፡ የማያምሩ ፡ የነበሩት ፡ ልጃገረዶች ፡ እያደሩ ፡ ሲያድጉ ፡ መልክ ፡ ይገዛሉ
9. (= plainly) በጉልህ. That's in plain view. ይህ ፡ በጉልህ ፡ የሚታይ ፡ ነው
*To put it in plain language: you are a thief. እቅጩን ፡ ለመናገር ፤ ሌባ ፡ ነህ

**plain** (adv.) ፈጽሞ
He is just plain stupid. እሱ ፡ ፈጽሞ ፡ ደደብ ፡ ነው

**make plain** በግልጽ ፡ አስረዳ
He made his meaning quite plain. ምን ፡ ማለቱ ፡ መሆኑን ፡ በግልጽ ፡ አስረዳ

**to be plain with you** እውነቱን ፡ ልንገርህ
To be plain with you, I cannot hire you for any job. እውነቱን ፡ ልንገርህ ፤ ለምንም ፡ ዓይነት ፡ ሥራ ፡ ልቀጥርህ ፡ አልችልም

**plainclothesman** ነጭ ፡ ለባሽ
A plainclothesman caught the shoplifter. ነጭ ፡ ለባሽ ፡ የሱቁን ፡ ሌባ ፡ ያዘው

**plainest** ግልጽ
The warning was conceived in the plainest language. ማስጠንቀቂያው ፡ የተነገረው ፡ በግልጽ ፡ አነጋገር ፡ ነበር

**plainly**
1. በጉልህ. All the goods are plainly priced. የእቃው ፡ ሁሉ ፡ ዋጋ ፡ በጉልህ ፡ ተጽፏል
2. በግልጽ. I thought they stated it plainly. በግልጽ ፡ የተናገሩ ፡ መስሎኝ ፡ ነበር
Speak plainly; the people have difficulty understanding your words. በግልጽ ፡ ተናገር ፤ ሰዎች ፡ የምትለውን ፡ ለማዳመጥ ፡ ይቸገራሉ

**plain-spoken** የልቡን ፡ የሚናገር
A plain-spoken person has few friends. የልቡን ፡ የሚናገር ፡ ሰው ፡ ብዙ ፡ ወዳጆች ፡ አይኖሩትም

**plaintiff** ከሳሽ
The plaintiff lost his case. ከሳሹ ፡ ተረታ

**plaintive, ~ song** የሐዘን ፡ እንጉርጉሮ
He sang a plaintive song. የሐዘን ፡ እንጉርጉሮ ፡ አዜመ

**plait** (v.) ጐነጐነ
The mother plaited the girl's hair. እናትዮዋ ፡ የልጇን ፡ ጸጉር ፡ ጐነጐነችላት

**plait** (n.) የጸጉር ፡ ጉንጉን
A long plait was hanging down the girl's back.

ረኸዋም ፡ የጸጉር ፡ ጉንጉን ፡ ልጅቷ ፡ ጀርባ ፡ ላይ ፡ ተንዠርግጎ ፡ ነበር

**plan** (planned), v.
1. አቀደ. We planned our trip carefully. ጉዞዋችንን ፡ በጥንቃቄ ፡ አቀድን
2. መደበ. He doesn't know how to plan his time. ጊዜውን ፡ መመደብ ፡ አይችልም
3. አሰበ. Where do you plan to spend the summer? በጋውን ፡ የት ፡ ለማሳለፍ ፡ ታስባለህ ?
4. ንድፍ ፡ አወጣ ፤ ነደፈ. An architect is planning their new house. መሀንዲስ ፡ ያዲሱን ፡ ቤታቸውን ፡ ንድፍ ፡ በማውጣት ፡ ላይ ፡ ነው
The architect planned the building in a new style. መሀንዲሱ ፡ ሕንጻውን ፡ የነደፈው ፡ ባዲስ ፡ መልክ ፡ ነው

**plan** (n.)
1. ፕላን. The plans for the new house are ready. ያዲሱ ፡ ቤት ፡ ፕላን ፡ ተዘጋጅቷል
The third five-year development plan was approved by parliament. ሦስተኛውን ፡ ያምስት ፡ ዓመት ፡ የልማት ፡ ፕላን ፡ ፓርላማው ፡ ተቀበለው
2. እቅድ. Our plans were discovered by the enemy. እቅዳችንን ፡ ጠላት ፡ ደረሰበት
3. ምኞት ፤ ሐሳብ. She has ambitious plans for her husband. ባሏ ፡ ከትልቅ ፡ ቦታ ፡ እንዲደርስ ፡ ከፍተኛ ፡ ምኞት ፡ አላት
She has very ambitious plans; she wants to become the supervisor of the department. ሐሳቧ ፡ ትልቅ ፡ ነው ፤ የክፍሉ ፡ ተቈጣጣሪ ፡ መሆን ፡ ትፈልጋለች

**according to plan** እንደታቀደ
Everything went according to plan. ሁሉም ፡ ነገር ፡ እንደታቀደው ፡ ሆነ

**make plans** አቀደ
Have you made any plans yet for the future? ለወደፊቱ ፡ ያቀድከው ፡ ነገር ፡ አለ ?
[See also 'devise, master']

**plane** (v.) ላገ
The carpenter planed the board. አናጢው ፡ ሳንቃውን ፡ ላገ

**plane** (n.)
1. አውሮፕላን. This plane flies to Athens. ይህ ፡ አውሮፕላን ፡ ወደ ፡ አቴን ፡ ይበራል
2. ደረጃ. The discussion was not on a very high plane. ውይይቱ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ደረጃ ፡ አልነበረም
3. መላጊያ. I need a plane to fix the door. በሩን ፡ ለመግጠም ፡ መላጊያ ፡ ያስፈልገኛል

**plane** (adj.) ዝርግ
The lines intersect on a plane surface. መሥመሮቹ ፡ በዝርግ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ይተላለፋሉ

**planet** ዓለም
The sun has nine planets in its system. ፀሐይ ፡ በዙሪያዋ ፡ ዘጠኝ ፡ ዓለማት ፡ አሏት

**plank** ሳንቃ
The floor is made of rough planks. ወለሉ ፡ ከሸካራ ፡ ሳንቃ ፡ የተሠራ ፡ ነው

**plant** (v.)
1. ተከለ. We planted flowers in our garden. አትክልት ፡ ስፍራችን ፡ ውስጥ ፡ አበባ ፡ ተከልን
2. ዘራ. They planted wheat. ስንዴ ፡ ዘሩ
3. ቸከለ. The workers planted posts along the road. ሠራተኞቹ ፡ መንገዱ ፡ ላይ ፡ ችካል ፡ ቸከሉ
4. አቆመ. During the demonstration, they planted policeman on every street. በሰላማዊ ፡ ሰልፉ ፡ ጊዜ ፡ በየመንገዱ ፡ ፖሊስ ፡ አቆሙ
5. አሳደረ(በት). His answer planted a doubt in my mind. መልሱ ፡ አእምሮዬ ፡ ውስጥ ፡ ጥርጣሬ ፡ አሳደረብኝ
The leader planted new ideas among his people. መሪው ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ አዳዲስ ፡ ሐሳቦችን ፡ አሳደረባቸው
*He planted his feet firmly on the ground and refused to move. ተንፈራጦ ፡ ቆሞ ፡ አልንቀሳቀም ፡ አለ

**plant** (n.)
1. ዕፅ (pl. ዕፀዋት). Various kinds of plants have been imported to Ethiopia. ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዕፀዋት ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንዲመጡ ፡ ተደርጓል
2. ፋብሪካ. The manager showed me around the plant. አስተዳዳሪው ፡ ፋብሪካውን ፡ አዙሮ ፡ አስጎበኘኝ
3. ድርጅት. The school has a fine plant, but not enough teachers. ትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ግሩም ፡ ድርጅት ፡ አለው ፤ ግን ፡ በቂ ፡ አስተማሪዎች ፡ የሉትም

**plantation** እርሻ
There are many false banana plantations in the South. በደቡብ ፡ ክፍል ፡ የእንሰት ፡ እርሻ ፡ በብዛት ፡ አለ

**planter** ባለመሬት
George Washington was a wealthy planter. ጆርጅ ፡ ዋሽንግቶን ፡ ሀብታም ፡ ባለመሬት ፡ ነበር

**plaster** (v.) ለሰነ
Have they finished plastering the walls yet? ግድግዳውን ፡ መለሰን ፡ ገና ፡ አልጨረሱም ?

**plaster** (n). ልስን
The plaster on the wall is all cracked. የግድግዳው ፡ ልስን ፡ በሙሉ ፡ ተሰነጣጥቋል

**lay on a coat of plaster**
The man laid on a coat of plaster. ሰውዬው ፡ ግድግዳውን ፡ ለሰነው
[See also 'cast']

**plastic** ፕላስቲክ
Many household articles are made of plastic. ብዙ ፡ የቤት ፡ እቃዎች ፡ ከፕላስቲክ ፡ ይሠራሉ

**plate** (v.) ነከረ
The goldsmith plated the cross with gold. ወርቅ ፡ አንጣሪው ፡ መስቀሉን ፡ ወርቅ ፡ ነከረው

**plate** (n.)
1. ሥዕል. The book has four hundred pages and twelve plates. መጽሐፉ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ገጾችና ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ሥዕሎች ፡ አሉት
2. ሳሕን. She bought three soup plates. ሦስት ፡ የሾርባ ፡ ሳሕን ፡ ገዛች
3. ምሳ. You can get lunch in this restaurant at a dollar a plate. እዚህ ፡ ምግብ ፡ ቤት ፡ አንድ ፡ ምሳ ፡ ባንድ ፡ ብር ፡ ታገኛለህ
4. ቆርቆሮ. The warship was covered with steel plates. የጦሩ ፡ መርከብ ፡ ከዐረብ ፡ ብረት ፡ በተሠሩ ፡ ቆርቆሮዎች ፡ የተለበደ ፡ ነው
*The banquet costs $25 a plate. ግብዣው ፡ በነፍስ ፡ ሃያ ፡ አምስት ፡ ብር ፡ ይከፈልበታል

**plateau** አምባ
A plateau covers the northern part of Ethiopia. ሰሜን ፡ ኢትዮጵያ ፡ አምባ ፡ የበዛበት ፡ ነው

**plated** ቅብ
This watch is plated with gold. ይህ ፡ ሰዓት ፡ የወርቅ ፡ ቅብ ፡ ነው
[See also 'silver']

**platform**
1. መድረክ. The speakers were seated on the platform. ተናጋሪዎቹ ፡ ከመድረኩ ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር
2. መምሪያ. The platform of the new political party demands lower taxes. ያዲሱ ፡ የፖለቲካ ፡ ቡድን ፡ መምሪያ ፡ ግብር ፡ እንዲቀነስ ፡ ነው

**platoon** የመቶ
The platoon was attacked by enemy soldiers. የመቶው ፡ በጠላት ፡ ወታደሮች ፡ ተጠቃ

**platter** ዝርግ ፡ ሳሕን
The roast lamb was served on a platter. አንድ ፡ የተጠበሰ ፡ በግ ፡ በዝርግ ፡ ሳሕን ፡ ቀረበ

**(be) plausible** እውነት ፡ ይመስላል
His excuse is plausible, but I don't really believe it. ምክንያቱ ፡ እውነት ፡ ይመስላል ፡ ግን ፡ አላመንኩትም

**play** (vt.)
1. ተጫወተ. The children played store. ልጆቹ ፡ ገዢና ፡ ነጋዴ ፡ ሆነው ፡ ተጫወቱ
We played cards for money. በገንዘብ ፡ ካርታ ፡ ተጫወትን
He plays the piano. ፒያኖ ፡ ይጫወታል
He played the title role in Hamlet. በሃምሌት ፡ ውስጥ ፡ መሪውን ፡ ቦታ ፡ ይዞ ፡ ተጫወተ
2. መታ. He plays the drum. ከበሮ ፡ ይመታል
He plays the violin very well. ማሲንቆ ፡ ጥሩ ፡ አድርጎ ፡ ይመታል
3. ነፋ. He plays the trumpet. ጥሩምባ ፡ ይነፋል
He plays the flute. ዋሽንት ፡ ይነፋል
4. ደረደረ. He plays the harp. በገና ፡ ይደረድራል
5. ሠራ. He played Othello last night. ትላንትና ፡ ማታ ፡ አቴሎን ፡ ሆኖ ፡ ሠራ
You shouldn't play tricks. ተንኰል ፡ አትሥራ

**play** (vi.)
1. ተጫወተ. The children are playing in the garden. ልጆቹ ፡ ባትክልት ፡ ቦታ ፡ ውስጥ ፡ ይጫወታሉ
The orchestra played brilliantly. የሙዚቃ ፡ ጓዱ ፡ አሳምሮ ፡ ተጫወተ
2. ታየ. What is playing at the movies tonight? ዛሬ ፡ ሲኒማ ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚታየው ፡ ምንድነው ?
A smile played across her face. በፊቷ ፡ ላይ ፡ ፈገግታ ፡ ይታይ ፡ ነበር

**play around** ማገጠ
You have been playing around long enough. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ስትማግጥ ፡ ነበር

**play at** ቀለደ
She is merely playing at being a student. ተማሪ ፡ ሆና ፡ ትቀልዳለች

**play down** አነስተኛ ፡ ግምት ፡ ሰጠ
The newspaper played down the clash. ጋዜጣው ፡ ለግጭቱ ፡ አነስተኛ ፡ ግምት ፡ ሰጠው

**play fair** እንደሚገባው ፡ አየ
He doesn't play fair with anyone. ማንንም ፡ ሰው ፡ እንደሚገባው ፡ አያይም

**play for time** ጊዜ ፡ ለማግኘት
Their maneuvering at the conference was a play for time. በስብሰባው ፡ ጊዜ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ማለታቸው ፡ ጊዜ ፡ ለማግኘት ፡ ነው

**play (a) great role** ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥረት ፡ አደረገ
The director played a great role in improving education. ትምህርትን ፡ ለማሻሻል ፡ ሥራ ፡ መሪው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥረት ፡ አድርገዋል

**play into (one's) hands**
*The candidate play into his opponent's hands. እጩው ፡ በተወዳዳሪው ፡ እጅ ፡ ላይ ፡ የሚጥለውን ፡ ተግባር ፡ ፈጸመ

**play off** አጋጨ
The director plays off his secretaries against each other. ሥራ ፡ መሪው ፡ ጸሐፊዎቹን ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ያጋጫቸዋል

**play out** ጨረሰ
Let's play out this game! ይህንን ፡ ጨዋታ ፡ እንጨርስ

**play up** በማጋነን + verb
The newspapers played up the incident as something serious. ጋዜጦች ፡ የተደረገውን ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ከባድ ፡ ነገር ፡ በማጋነን ፡ ጻፉት

**play with the idea** አወጣ ፡ አወረደ
He was playing with the idea of going to Ethiopia. ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለመሄድ ፡ ሲያወጣ ፡ ሲያወርድ ፡ ነበር
[See also 'havoc, joke, part, trick']

**play** (n.)
1. ጨዋታ. The children are completely absorbed in their play. ልጆቹ ፡ በጨዋታቸው ፡ በፍጹም ፡ ተመስጠዋል
2. ቲያትር. Are there any good plays in town? ከተማው ፡ ውስጥ ፡ ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ ቲያትሮች ፡ አሉ ?
3. ቀልድ. He just said it in play. ያለው ፡ እንዲያው ፡ ለቀልድ ፡ ነው
*It's your play next. ያንተ ፡ ተራ ፡ ነው

**play on words** ሰምና ፡ ወርቅ ፤ ባማርኛ ፡ መናገር
This poem is mostly a play on words. ይህ ፡ ግጥም ፡ የተጻፈው ፡ በይበልጥ ፡ በሰምና ፡ ወርቅ ፡ ነው
Some people are fond of plays on words. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ባማርኛ ፡ መናገር ፡ ይወዳሉ

**be brought into play** ቀረበ
New evidence has been brought into play in this trial. በዚህ ፡ ነገር ፡ አዲስ ፡ ማስረጃ ፡ ቀርቧል

**come into play** በየጊዜው ፡ ተነሣ
Certain forces come into play to complicate the situation even more. ሁኔታውን ፡ የባሰ ፡ አስቸጋሪ ፡ ለማድረግ ፡ አንዳንድ ፡ ነገሮች ፡ በየጊዜው ፡ ይነሣሉ

**put on a play** ቲያትር ፡ አሳየ
The students are putting on a play. ተማሪዎቹ ፡ ቲያትር ፡ ያሳያሉ
[See also 'dirty, foul, word']

**player** ተጫዋች
One of the players got hurt during the game. ከተጫዋቾቹ ፡ አንዱ ፡ በጨዋታው ፡ ጊዜ ፡ ተጐዳ
[See also 'harp']

**playful** ተጫዋች
The children laughed at the playful puppy. ልጆቹ ፡ በተጫዋቹ ፡ ቡችላ ፡ ሣቁ

**playground** የመጫወቻ ፡ ስፍራ
There are no playgrounds in this city. በዚህ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ የመጫወቻ ፡ ስፍራዎች ፡ የሉም

**playing card** የመጫወቻ ፡ ካርታ
I don't have any playing cards. ምንም ፡ የመጫወቻ ፡ ካርታ ፡ የለኝም

**playmate** ጓደኛ
My child and his are playmates. ልጄና ፡ ልጁ ፡ ጓደኞች ፡ ናቸው

**plaything** መጫወቻ
The child left its playthings scattered about. ልጁ ፡ መጫወቻዎቹን ፡ እንደ ፡ ተበታተኑ ፡ ተዋቸው

**playwright** የቲያትር ፡ ደራሲ
The playwright received no money for his play. የቲያትሩ ፡ ደራሲ ፡ ለቲያትሩ ፡ ገንዘብ ፡ አልተቀበለም

**plea**
1. ልመና. He ignored my plea. ልመናዬን ፡ ችላ ፡ አለ
2. ጥያቄ. The judge rejected his plea for a stay. ቀጠሮው ፡ እንዲራዘምለት ፡ ያቀረበውን ፡ ጥያቄ ፡ ዳኛው ፡ አልተቀበሉትም
3. ምክንያት. Illness was his plea for being absent. ለመቅረቱ ፡ ምክንያት ፡ አድርጎ ፡ የሰጠው ፡ መታመሙን ፡ ነበር

**enter a plea**
*He entered a plea of guilty. ጥፋተኛ ፡ ነኝ ፡ አለ

*He entered a plea of bankruptcy. መክሰሩን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስታወቀ

**make a plea** ለመነ
The mother made a fervent plea to the judge to spare her son. እናቲቱ ፡ ዳኛው ፡ ልጇን ፡ እንዲያተርፍላት ፡ ልብ ፡ በሚነካ ፡ ሁኔታ ፡ ለመነች

## plead
1. ተሟገተ. He pleaded his case without a lawyer. ጠበቃ ፡ ሳያቆም ፡ ተሟገተ
2. ለመነ. When the rent was due, the poor man pleaded for more time. ኪራይ ፡ መክፈያው ፡ ጊዜ ፡ ሲደርስ ፡ ድኻው ፡ ሰው ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሰጠው ፡ ለመነ
3. ልመና ፡ አቀረበ ፤ አቤቱታ ፡ አቀረበ. The prisoner pleaded for his liberty. እስረኛው ፡ በነጻ ፡ እንዲለቀቅ ፡ ልመና ፡ (አቤቱታ) ፡ አቀረበ
4. እንደ ፡ ምክንያት ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ አቀረበ. The criminal pleaded insanity. ወንጀለኛው ፡ አንጐሉ ፡ መታወኩን ፡ እንደ ፡ ምክንያት ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ አቀረበ
5. ምክንያት ፡ ሰጠ. He pleaded poverty when caught stealing. ሲሰርቅ ፡ ቢያዝ ፡ በድኽነት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ምክንያት ፡ ሰጠ

**plead guilty** ጥፋተኛነትን ፡ አመነ
Do you plead guilty to the charge of murder? በነፍስ ፡ ገዳይነት ፡ ለቀረበብህ ፡ ክስ ፡ ጥፋተኛ ነትህን ፡ ታምናለህ ?

**plead with** ለመነ
She pleaded with him not to go. እንዳይሄድ ፡ ለመነችው

## pleasant
1. ደስ ፡ የሚል. She is a pleasant person. ደስ ፡ የምትል ፡ ሰው ፡ ነች
2. የሚያስደስት. After a long march, soaking one's foot in warm water is a very pleasant sensation. ከረዥም ፡ ጉዞ ፡ በኋላ ፡ እግርን ፡ ሙቅ ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ መዘፍዘፍ ፡ በጣም ፡ የሚያስደስት ፡ ስሜት ፡ ይሰጣል
*Goodbye, have a pleasant trip! ደኅና ፡ ግባ ፡ (or, መንገዱን ፡ ጨርቅ ፡ ያድርግልህ)

**be pleasant for** ደስ ፡ አለው
It will be pleasant for her to have news of her family. ስለ ፡ ቤተሰቦቿ ፡ ወሬ ፡ ብትሰማ ፡ ደስ ፡ ይላታል

## pleasantry
(pleasantries) የቀልድ ፡ አነጋገር
The workers smiled at the minister's pleasantries. በሚኒስትሩ ፡ የቀልድ ፡ አነጋገር ፡ ሠራተኞቹ ፡ ፈገግ ፡ አሉ

## please (vt.)
1. አስደሰተ ፤ ደስ ፡ አሰኘ. You can't please everybody. ሁሉንም ፡ ማስደሰት ፡ (ደስ ፡ ማሰኘት) ፡ አይቻልም
2. የ - - መልካም ፡ ፈቃድ ፡ ነበር. It pleased the king to go. መሄድ ፡ የንጉሡ ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፡ ነበር
*Go where you please! እፈለግህበት ፡ ሂድ
*Take as many cookies as you please! የፈለግኸውን ፡ ያህል ፡ ብስኩት ፡ ውሰድ

**please!**
1. እባክህ. Please shut the door! እባክህ ፡ መዝጊያውን ፡ ዝጋ
2. (jussive). Come in, please! ይግቡ

**be pleased** ደስ ፡ አለ(ው)
+I am pleased to see he is working again. እንደገና ፡ ሥራ ፡ በመግባቱ ፡ ደስ ፡ አለኝ

**as I (you, he) please**
1. የፈለግሁትን. I shall do as I please with my money. በገንዘቤ ፡ የፈለግሁትን ፡ አደርጋለሁ
2. እንደልቡ. You may come in and go out as you please. እንደልብህ ፡ ልትገባና ፡ ልትወጣ ፡ ትችላለህ

**do as you please** እንዳሰኘህ ፤ እንደተመቸህ
Should I come tomorrow or the day after tomorrow? Do as you please. ነገ ፡ ልምጣ ፡ ተነገ ፡ ወዲያ ? እንዳሰኘህ ፡ (እንደተመቸህ)

**if you please** ፈቃድህ ፡ ቢሆን
And now, if you please, I will read you the contract. አሁን ፡ ፈቃድህ ፡ ቢሆን ፡ ውሉን ፡ አነብልሃለሁ

**look pleased** ደስ ፡ የተሰኘ ፡ መስሎ ፡ ታየ
He looked very pleased with himself when he got the award. ሽልማቱን ፡ ሲያገኝ ፡ በራሱ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ የተሰኘ ፡ መስሎ ፡ ታየ

## pleasing
የሚያስደስት
She has a very pleasing voice. በጣም ፡ የሚያስደስት ፡ ድምፅ ፡ አላት

**be pleasing** አስደሰተ
The flowery meadow was pleasing to the eye. በአበባ ፡ ያሸበረቀው ፡ መስክ ፡ ለዓይን ፡ ያስደስት ፡ ነበር

## pleasure (v.)
ደስ ፡ አለ(ው)
+I pleasure in your company. ካንተ ፡ ጋር ፡ መሆን ፡ ደስ ፡ ይለኛል

## pleasure (n.)
1. ደስታ. He never combines business with pleasure. እሱ ፡ ከቶ ፡ ሥራን ፡ ከደስታ ፡ ጋር ፡ አያጣምርም

2. መደሰት. He alternates work with pleasure. መሥራትና ፡ መደሰትን ፡ ያፈራርቃል

3. የሚያስደስት ፡ ነገር. It is a pleasure to hear her sing. ስትዘፍን ፡ መስማት ፡ የሚያስደስት ፡ ነገር ፡ ነው

4. መልካም ፡ ፈቃድ. Is it your pleasure to go now? አሁን ፡ ለመሄድ ፡ መልካም ፡ ፈቃድዎ ፡ ነው ?

*For dessert, what is your pleasure? ለማጣጣሚያ ፡ ምን ፡ ትፈቅዳለህ ?

**afford pleasure** ደስ ፡ አሰኘ

The movie afforded pleasure to all who saw it. ፊልሙ ፡ ያየውን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ አሰኘ

**find pleasure** ደስ ፡ አለ(ው)

Do you find much pleasure in farming? በማብርና ፡ ብዙ ፡ ደስ ፡ ይልሃል ?

**take pleasure** ተደሰተ

Some boys take pleasure in teasing their sisters. አንዳንድ ፡ ልጆች ፡ በእኅቶቻቸው ፡ በማሾፍ ፡ ይደሰታሉ

**pleat** (v.) ሸነሸነ

It takes a lot of effort to pleat a skirt properly. ጉርድ ፡ ቀሚስን ፡ በሚገባ ፡ ለመሸንሸን ፡ ብዙ ፡ ጥረት ፡ ይጠይቃል

**pleat** (n.) ሽንሽን

Her skirt has many pleats in it. ቀሚሷ ፡ ብዙ ፡ ሽንሽን ፡ አለው

**pledge** (v.)

1. ቃል ፡ ገባ. He pledged $100 in the campaign to raise money for the new church. ላዲሱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገንዘብ ፡ ለመሰብሰብ ፡ ለሚደረገው ፡ ጥረት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ለመስጠት ፡ ቃል ፡ ገባ

We pledge loyalty to our country. ለሀገራችን ፡ ታማኝ ፡ ለመሆን ፡ ቃል ፡ ገብተናል

2. ቃል ፡ አስገባ. The speaker pledged the hearers to secrecy. ተናጋሪው ፡ አዳማጮቹ ፡ ንግግሩን ፡ በምስጢር ፡ እንዲይዙ ፡ ቃል ፡ አስገባቸው

**pledge allegiance** የመሐላ ፡ ቃል ፡ ገባ ፤ ታማኝነትን ፡ ገለጸ

In America, students pledge allegiance to the flag every morning. የአሜሪካ ፡ ተማሪዎች ፡ ጧት ፡ ጧት ፡ ለሰንደቅ ፡ ዓላማቸው ፡ የመሐላ ፡ ቃል ፡ ይገባሉ ፡ (ያላቸውን ፡ ታማኝነት ፡ ይገልጻሉ)

**pledge as a security** መያዣ ፡ አደረገ

He pledged his house as a security for the loan. ቤቱን ፡ ለብድሩ ፡ መያዣ ፡ አደረገው

**pledge** (n.)

1. ቃል ፡ መግባት. Their pledge not to wage war was not believed by anyone. ጦር ፡ እናነሣም ፡ ሲሉ ፡ ቃል ፡ መግባታቸውን ፡ ማንም ፡ አላመነም

2. ማስታወሻ. He gave her a ring as a pledge of his love. ለፍቅሩ ፡ ማስታወሻ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ቀለበት ፡ ሰጣት

3. ማረጋገጫ. We shook hands as a pledge of friendship. ለጓደኝነታችን ፡ ማረጋገጫ ፡ እጅ ፡ ለእጅ ፡ ተጨባበጥን

4. መያዣ. He left his mule as pledge for the borrowed horse. ለተዋሰው ፡ ፈረስ ፡ መያዣ ፡ እንድትሆን ፡ በቅሎውን ፡ ሰጠ

**pledge of allegiance** ቃለ ፡ መሐላ

The new recruits recited the pledge of allegiance. አዲስ ፡ ቅጥሮቹ ፡ ቃለ ፡ መሐላ ፡ ገቡ

**be under the pledge** ቃል ፡ ገባ ፤ ግዴታ ፡ አለበት

He is under the pledge of secrecy as long as he works for the government. በመንግሥት ፡ አገልግሎት ፡ ውስጥ ፡ እስካለ ፡ ድረስ ፡ ምስጢር ፡ ላያወጣ ፡ ቃል ፡ ገብቷል ፡ (ግዴታ ፡ አለበት)

**take the pledge** ቃል ፡ ገባ

The President takes a pledge to defend the constitution. ፕሬዚዳንቱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ ለመጠበቅ ፡ ቃል ፡ ይገባል

**sign a pledge** በፊርማ ፡ ቃል ፡ ገባ

Mr. Parker signed a pledge to give $50 to charity. ሚስተር ፡ ፓርከር ፡ አምሳ ፡ ብር ፡ ችሮታ ፡ ለመስጠት ፡ በፊርማ ፡ ቃል ፡ ገባ

**plenary** ሙሉ

In America, the parliament has plenary power. በአሜሪካ ፡ ምክር ፡ ቤቱ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አለው

**plenary session**

*The parliament is in plenary session. የምክር ፡ ቤቱ ፡ ሙሉ ፡ ስብሰባ ፡ ሁሉም ፡ እንደራሴዎች ፡ በተገኙበት ፡ ተደረገ

**plenipotentiary** (plenipotentiaries) ባለሙሉ ፡ ሥልጣን

He was minister and envoy plenipotentiary to Sweden in 1908. በ፲፱፻፩ ፡ ዓ. ም. በስዊድን ፡ ሀገር ፡ ሚኒስትርና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ መልእክተኛ ፡ ነበሩ

**plenitude** መዓት

There is a plenitude of flies in the market. ገበያው ፡ ውስጥ ፡ የዝምብ ፡ መዓት ፡ አለ

**plenteous** (= n.) መብዛት

A plenteous crop means happiness for the farmers. የሰብል ፡ መብዛት ፡ ለገበሬዎች ፡ ደስታ ፡ ነው

**plenteous supply of** በብዛት
There is usually a plenteous supply of raw materials. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ጥሬ ፡ እቃ ፡ በብዛት ፡ ይገኛል

**plentiful, ~ supply of** ብዙ
We have a plentiful supply of grain. ብዙ ፡ እህል ፡ አለን

**be plentiful** ሞላ
Deer are plentiful in this area. በዚህ ፡ ቀበሌ ፡ አጋዘን ፡ ሞልቷል

**plenty** ጥጋብ
These are years of peace and plenty. እነዚህ ፡ የሰላምና ፡ የጥጋብ ፡ ዓመታት ፡ ናቸው

**plenty of** ብዙ ፤ በብዛት
There was plenty of food and drink at the party. በግብዣው ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ምግብና ፡ መጠጥ ፡ ነበር
We have plenty of time before the plane leaves. አውሮፕላኑ ፡ ከመነሣቱ ፡ በፊት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አለን
She has plenty of dresses. ልብስ ፡ በብዛት ፡ አላት

**be plenty** በቃ
Six potatoes will be plenty. ስድስት ፡ ድንች ፡ ይበቃል

**have plenty** ሞላ(ው)
+We had plenty to eat. የሚበላ ፡ ሞልቶን ፡ ነበር

**in plenty of time** ቀደም ፡ ብሎ
We must get to the station in plenty of time. እጣቢያው ፡ ቀደም ፡ ብለን ፡ መድረስ ፡ አለብን

**pleurisy** የሳምባ ፡ በሽታ
He has pleurisy and doesn't leave the house. የሳምባ ፡ በሽታ ፡ ስለያዘው ፡ ከቤት ፡ አይወጣም

**pliable** ሊተጣጠፍ ፡ የሚችል
This wire is pliable. ይህ ፡ ሽቦ ፡ ሊተጣጠፍ ፡ የሚችል ፡ ነው

**pliant**
1. የሚተጣጠፍ. Pliant vines are woven into mats. የሚተጣጠፈው ፡ ሐረግ ፡ ሰሌን ፡ ይሠራበታል
2. ተወዛዋዥ. Children were swinging on the tree's pliant branches. ልጆች ፡ በዛፉ ፡ ተወዛዋዥ ፡ ቅርንጫፎች ፡ ላይ ፡ ይንጠላጠሉ ፡ ነበር
3. ተለማጭ. He manipulated the pliant twig. ተለማጭ ፡ ቅርንጫፍ ፡ እንደልቡ ፡ ያደርገው ፡ ነበር
4. የመስሎ ፡ አደር. His pliant behavior saved him from the soldiers' arrogance. የመስሎ ፡ አደር ፡ ጠባዩ ፡ ከወታደሮች ፡ ትዕቢተኛነት ፡ አዳነው
*He has a pliant nature and does what others tell him. በሰው ፡ ሐሳብ ፡ ስለሚመራ ፡ የነገሩትን ፡ ያደርጋል

**pliers** ጉጠት
I need pliers to take off the bolt. መቀርቀሪያውን ፡ ለመንቀል ፡ ጉጠት ፡ ያስፈልገኛል

**plight** መከራ
The plight of the refugees was sad to see. የስደተኞቹን ፡ መከራ ፡ ማየት ፡ አሳዛኝ ፡ ነበር

**plod** (plodded), **~ along**
1. አዘገመ. The weary soldier was plodding along the side of the road. የደከመው ፡ ወታደር ፡ የመንገዱን ፡ ዳር ፡ ይዞ ፡ ያዘግም ፡ ነበር
2. ለገመ. He just plods along at his job. በሥራው ፡ ላይ ፡ ይለግማል

**plod away** መላልሶ ፡ አጠና
He plods away at his lessons until he learns them. ትምህርቱ ፡ እስኪገባው ፡ ድረስ ፡ መላልሶ ፡ ያጠናል

**plod past** እያዘገመ ፡ አለፈ
The prisoners plodded past. እስረኞቹ ፡ እያዘገሙ ፡ አለፉ

**plot** (plotted), v. አደመ ፤ አሤረ
They plotted against the director of the prison. በእስር ፡ ቤት ፡ አለቃው ፡ ላይ ፡ አደሙ
The imperialists are plotting against him. ኢምፔሪያሊስቶች ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ ያሤራሉ

**plot** (n.)
1. አድማ. He was involved in a plot to kill the director. ዲሬክተሩን ፡ ለመግደል ፡ በተደረገው ፡ አድማ ፡ ገብቶ ፡ ነበር
2. ቁራጭ. He bought a plot of land in the city. ከከተማው ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ቁራጭ ፡ መሬት ፡ ገዛ
3. ታሪክ. The film has an interesting plot. የፊልሙ ፡ ታሪክ ፡ አስደናቂ ፡ ነው

**plotter** ሤረኛ ፤ አድመኛ
The plotter was executed by the soldiers. ሤረኛው ፡ (አድመኛው) ፡ በወታደሮች ፡ ተገደለ

**plow** (vt.) አረሰ
I will need all day to plow this field. ይህን ፡ ማሳ ፡ ለማረስ ፡ ሙሉ ፡ ቀን ፡ ይፈጅብኛል

**plow through** ሰንጥቆ ፡ ተጓዘ
The ship plowed through the rough seas. መርከቡ ፡ ማዕበሉን ፡ ሰንጥቆ ፡ ተጓዘ

**plow (one's) way** እየተጋፋ ፡ አለፈ
He plowed his way through the crowd. በሕዝብ ፡ መካከል ፡ እየተጋፋ ፡ አለፈ

**plow** (n.) ማረሻ
The farmer's plow broke on a stone. የገበሬውን ፡ ማረሻ ፡ ድንጋይ ፡ ሰበረበት

**pluck**
1. ነጨ. Did you pluck the chickens yet ? ዶሮዎቹን ፡ ነጭተሻቸዋል ?
2. ቀጠፈ. He plucked an apple from a tree. ከዛፍ ፡ ላይ ፡ ቱፋ ፡ ቀጠፈ
3. ነቀለ. She spent the day plucking weeds. ቀኑን ፡ ያሳለፈችው ፡ አረም ፡ በመንቀል ፡ ነው
4. መታ. He plucked the strings of the harp to test the sound. ድምፁን ፡ ለመፈተን ፡ የበገናውን ፡ አውታር ፡ መታ

**pluck at** ሳብ ፡ ሳብ ፡ አደረገ
He plucked at my sleeve to get my attention. ወደ ፡ እሱ ፡ ዞር ፡ እንድል ፡ የኰቴን ፡ እጅጌ ፡ ሳብ ፡ ሳብ ፡ አደረገው
[See also 'string']

**plug** (plugged), v.
1. ወተፈ. He plugged the leak with a rag. የሚያፈሰውን ፡ ቀዳዳ ፡ ጨርቅ ፡ ወተፈው
2. ሰካ. Plug the lamp into the socket! መብራቱን ፡ መሰኪያው ፡ ውስጥ ፡ ሰካው

**plug in** ሰካ
Where is an outlet so I can plug in the radio? ሬዲዮኑን ፡ እንድሰካው ፡ የኮረንቲ ፡ መሰኪያው ፡ የት ፡ ነው ?

**plug up** ደፈነ
Give me some plaster to plug up this crevice! ይህን ፡ የግድግዳውን ፡ ስንጥቅ ፡ የምደፍንበት ፡ ጭቃ ፡ ስጠኝ

**plug** (n.)
1. ውታፍ. He took the plug out of the tub. ከመታጠቢያው ፡ ገንዳ ፡ ውስጥ ፡ ውታፉን ፡ ነቀለው
2. የኮረንቲ ፡ መሰኪያ. The radio went off because you pulled the plug out. የኮረንቲውን ፡ መሰኪያ ፡ ስለነቀልከው ፡ ሬዲዮኑ ፡ ጠፋ

**plumb** (v.) ገመድ ፡ ሰደደ
They plumbed the depths of the lake to find out how deep it was. የሐይቁን ፡ ጥልቀት ፡ ለመለካት ፡ ገመድ ፡ ሰደዱ

**plumb** (n.), ~ **line** ቱንቢ
The mason used a plumb line to keep the wall straight. ግንበኛው ፡ ግድግዳውን ፡ ቀጥ ፡ አድርጎ ፡ ለመሥራት ፡ በቱንቢ ፡ ተጠቀመ

**be out of plumb** ዘመመ
The wall is out of plumb. ግድግዳው ፡ ዘሟል

**plumber** ቧምቧ ፡ ሠራተኛ
Call the plumber; the water is leaking from the pipe. ቧምቧው ፡ ውኃ ፡ ስለሚያፈስ ፡ ቧምቧ ፡ ሠራተኛውን ፡ ጥራ

**plumbing** የቧምቧ ፡ ሥራ
The plumbing of the new house is up-to-date. ያዲሱ ፡ ቤት ፡ የቧምቧ ፡ ሥራ ፡ ዘመናዊ ፡ ነው

**plummet**
1. [ገመድ ፡ ወይም ፡ ሽቦ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ታስሮ ፡ የባሕር ፡ ርቀት ፡ የሚለካበት ፡ የብረት ፡ አሎሎ]
2. ቱንቢ. The mason measured the right angle of the wall with a plummet. ግንበኛው ፡ የግድግዳውን ፡ ቀጥተኛ ፡ ማእዘን ፡ በቱንቢ ፡ ለካ

**plump down** እንዘፍ ፡ አደረገ
She plumped down the heavy bag on the table. ከባዱን ፡ ከረጢት ፡ ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ እንዘፍ ፡ አደረገች

**plump oneself down** ረብ ፡ አለ
He plumped himself down on the bed. አልጋው ፡ ላይ ፡ ረብ ፡ አለ

**plump** (adj.) የፋፋ
Your baby is very plump. ሕፃኗ ፡ ልጅሽ ፡ በጣም ፡ የፋፋች ፡ ናት

**plunder** (v.) ዘረፈ
The bandits plundered the village. ሽፍቶቹ ፡ መንደሩን ፡ ዘረፉት

**plunder** (n.) የዘረፈው ፤ ዘረፋ
The army fled leaving its plunder behind. ጦሩ ፡ የዘረፈውን ፡ ጥሎ ፡ ሸሸ
The plunder consisted of livestock and goods. ዘረፋው ፡ የተፈጸመው ፡ በከብቶችና ፡ በንብረት ፡ ላይ ፡ ነበር

**plunge** (vt.)
1. ጣለ. His policies plunged the country into war. አመራሩ ፡ አገሪቷን ፡ ጦርነት ፡ ላይ ፡ ጣላት
2. ሰካ. He plunged the dagger into his enemy's heart. ጠላቱን ፡ ደረቱ ፡ ላይ ፡ ጩቤ ፡ ሰካበት
3. ነከረ. He plunged his burnt arm into the water. የተቃጠለውን ፡ ክንዱን ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ነከረው

**plunge** (vi.)
1. ጥልቅ ፡ አለ. He plunged into the midst of the crowd and separated the fighting boys. ሕዝቡ ፡ መሀል ፡ ጥልቅ ፡ ብሎ ፡ የሚጣሉትን ፡ ልጆች ፡ ገላገለ
2. ዘሎ ፡ ገባ. He plunged into the water. ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ዘሎ ፡ ገባ

**plunge into** ተያያዘ
We plunged into our work. ሥራችንን ፡ ተያያዝ ነው

**plunge through** ሰንጥቆ ፡ አለፈ
The ship plunged through the waves. መርከብ ፡ ሞገዱን ፡ ሰንጥቆ ፡ አለፈ
[See also 'headlong']

**plunk** (vt.) መታ
He plunked his guitar. ጊታሩን ፡ መታ

**plunk** (vi.) በርጩቅ ፡ አለ
The stone plunked into the water. ድንጋዩ ፡ ውኃው ፡ ውስጥ ፡ በርጩቅ ፡ አለ

**plunk down** በኀይል ፡ ጣለ
He plunked his book down on the desk. መጽሐፉን ፡ ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ በኀይል ፡ ጣለ

**plural** የብዙ ፡ ቁጥር
The Amharic plural has a special ending. ባማርኛ ፡ የብዙ ፡ ቁጥር ፡ የተለየ ፡ ቅጥያ ፡ አለው

**plurality** ብልጫ
He received a plurality of all votes cast. በተደረገው ፡ ውድድር ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ አገኘ

**plus** (adj.) የመደመር
The plus sign resembles a cross. የመደመር ፡ ምልክት ፡ መስቀል ፡ ይመስላል

**plus** (prep.)
1. ሲደመር. Five plus seven is twelve. አምስትና ፡ ሰባት ፡ ሲደመር ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ይሆናል
2. ከ --- ሌላ. It costs $10 plus tax. ከታክስ ፡ ሌላ ፡ ዐሥር ፡ ብር ፡ ያወጣል
3. ከ --- ጋር. He received a salary plus gratuities. ደሞዙን ፡ ከጉርሻ ፡ ጋር ፡ ተቀበለ

**ply** (plied), vt.
1. ሠራ. He plied the trade of carpenter for many years. ባናጢነት ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ሠራ
2. ቀዘፈ. We plied the water with our oars. ባሕሩን ፡ በመቅዘፊያ ፡ ቀዘፍን
3. በ --- ተጠቀመ. The dressmaker plies her needle. ልብስ ፡ ሰፊዋ ፡ በመርፌ ፡ ትጠቀማለች

**ply** (vi.) ተመላለሰ
Boats ply among the islands of Lake Tana carrying food and passengers. ጀልባዎች ፡ ምግብና ፡ ተሳፋሪዎች ፡ ይዘው ፡ በጣና ፡ ደሴቶች ፡ መካከል ፡ ይመላለሳሉ

**ply with** አትረፈረፈ(ለት)
Our host plied us with food. ጋባዣችን ፡ ምግብ ፡ አትረፈረፈልን

**ply with questions** አዋከበ
The enemy plied our messenger with questions to make him divulge his mission. ጠላት ፡ መልእክተኛችንን ፡ መልእክቱን ፡ እንዲነግር ፡ አዋከበው

**ply** (plies), n. **two-ply** ዕጥፍ ፡ ውፍረት ፡ ያለው
A two-ply tire is safer than an ordinary tire. ዕጥፍ ፡ ውፍረት ፡ ያለው ፡ ጎማ ፡ ከተራው ፡ ጎማ ፡ ይልቅ ፡ ከአደጋ ፡ ይጠብቃል

**pneumonia** የሳምባ ፡ ምች
He caught pneumonia last year. ባለፈው ፡ ዓመት ፡ የሳምባ ፡ ምች ፡ መታው

**poach** ያለ ፡ ፈቃድ ፡ አደነ
He poached on his neighbor's land. በጐረቤቱ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ያለፈቃድ ፡ አደነ

**pocket** (v.)
1. እኪሱ ፡ አደረገ. He pocketed the money without saying a word. አንዲት ፡ ቃል ፡ ሳይናገር ፡ ገንዘቡን ፡ እኪሱ ፡ አደረገ
2. ሰርቆ ፡ ወሰደ. His partner pocketed all the profits. ሸሪኩ ፡ ትርፉን ፡ በሙሉ ፡ ሰርቆ ፡ ወሰደ
3. ዋጥ ፡ አደረገ. He pocketed his pride and begged for help. ኵራቱን ፡ ዋጥ ፡ አድርጎ ፡ እርዳታ ፡ ለመነ

**pocket** (n.) ኪስ
Put this in your pocket! ይህንን ፡ ኪስህ ፡ ውስጥ ፡ ክተት

**pocket** (adj.) የኪስ
I bought a pocket radio. የኪስ ፡ ሬዲዮ ፡ ገዛሁ
[See also 'pickpocket']

**pocketbook** ቦርሳ
She lost her pocketbook. ቦርሳዋ ፡ ጠፋባት

**pocketknife** ሰንጢ
May I borrow your pocketknife? ሰንጢህን ፡ ታውሰኝ ?

**pod** ፍልፋይ
She threw out the pods with the garbage. ፍልፋዩን ፡ ከቆሻሻ ፡ ጋር ፡ ጣለችው

**podium** መድረክ
The podium was too high for the audience to see the speaker. መድረኩ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስለነበረ ፡ አድማጮቹ ፡ ተናጋሪውን ፡ ለማየት ፡ አልቻሉም

**poem** ግጥም
This book contains all his poems. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ የሱን ፡ ግጥሞች ፡ በሙሉ ፡ ይይዛል

**poet** ባለቅኔ
He is the chief poet of our time. በጊዜያችን ፡ ታላቁ ፡ ባለቅኔ ፡ እሱ ፡ ነው